# ምዕራፍ ፡ ፫ ፡፡

## ጠላት ፡ የሐሰት ፡ ፕሮፖጋንዳ ፡ ስለመበተኑ ፡፡

በዚህ ፡ ታሪክ ፡ በምዕራፍ ፡ ፲፩ ፡ እንደገለጽሁት ፡ ኢጣልያኖች ፡ በጦር ፡ ኃይላቸው ፡ ብቻ ፡ የጊዜውን ፡ ድል ፡ ማግኘት ፡ አይችሉም ፡ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ በአገሩ ውስጥ ፡ በየምክንያቱ ፡ በላኳቸው ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ሠራተኞቻቸውና ፡ በየሀገሩ ፡ ገብተው ፡ በነበሩበት ፡ የሃይማኖት ፡ ሚሲዮኖቻቸው ፡ አማካይነት ፡ አስመስሎ ፡ በመስበክ ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ ፍቅር ፡ እንድናጣና ፡ እንዲቀነስ ፡ በማድረጋቸው ፡ ነበር ፤

አሁንም ፡ ኢጣልያኖች ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ቆይተው ፡ በመጨረሻ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ሥላሴ፡ ብርቱ ፡ መሪነትና ፡ በአርበኞቻቸው ፡ ተጋዳይነት ፡ በወዳጅ ፡ መንግሥታት ፡ እርዳታም ፡ ድል ፡ ተነስተው ፡ የሚለቁ ፡ መሆናቸውን ፡ ሲአውቁ ፤ አብረዋቸው ፡ ያሉትንና ፡ በስደት ፡ ቆይተው ፡ አሁን ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ ጋር ፡ ጠላትን ፡ አጥቅቶ ፡ አገርን ፡ ለማስለቀቅና ፡ ነጻነትን ፡ ከቦታዋ ፡ ለመመለስ ፡ የሚጋደሉትን ፡ የአርበኞቻቸውን ፡ ልብ ፡ አሻክሮ ፡ ለማጣላት ፡ አስበው ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ የአዋጅ ፡ ቃል ፡ በማስመስል ፡ ብዙ ፡ ጽሑፎች ፡ በአይሮፕላን ፡ በያገሩ ፡ ይበትኑ ፡ ነበር ፡፡

ይህ ፡ የሐሰት ፡ ፕሮፖጋንዳ ፡ በተበተነበት ፡ ጊዜ ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳሚ ፡ መልክተኛ ፡ በመሆን ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ መጥተን ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ገብተን ፡ ስለነበረ ፤ ለሥራ ፡ መሪ ፡ እንዲሆን ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ከተሰጠን ፡ ማስታወሻ ፡ ልዩነት ፡ ያለው ፡ በመሆኑ ፡ እንደዚሁም ፡ በልማዱ ፡ ሁሉ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተምና ፡ ፊርማ ፡ በደብዳቤው ፡ ላይ ፡ ከአርዕስቱ ፡ ላይ ፡ እንጂ ፡ ከጽሑፉ ፡ መጨረሻ ፡ እንደሌላው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ እንደሌላው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በግርጌ ፡ ማኅተምና ፡ መፈረም ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አግባብ ፡ አለመሆኑን ፡ በመግለጥና ፡ በማስተባበል ፡ ለየአርበኞቹና ፡ ለየገዳማቱ ፡ በየጊዜው ፡ ከተጻፉት ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጽሑፎች ፡ ጋር ፡ እንዲአስተያዩትና ፡ የሐሰት ፡ ፕሮፖጋንዳ ፡ መሆኑን ፡ እንዲረዱ ፡ ለሌላውም ፡ እንዲአስረዱ ፡ ስለጻፍንላቸው ፡ ሐሰተኛ ፡ ጽሑፍ ፡ መሆኑ ፡ ወዲያው ፡ ተገለጠ ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ጠላት ፡ መናቅን ፡ አተረፈ ፡ እንጂ ፡ የሐሰት ፡ ፕሮፖጋንዳው ፡ ምንም ፡ ሳይሰራለት ፡ ቀርቷል ፡፡



ይህንኑም ፡ ጽሑፍ ፡ አንባቢዎች ፡ እንዲረዱት ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሆነ ፡ በጊዜው ፡ ላይ ፡ በሐሰት ፡ እየተጻፈ ፡ ከተበተኑት ፡ የጠላት ፡ የሐሰት ፡ ፕሮፖጋንዳዎች ፡ ጥቂቶችን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ ጽፈናልና ፡ የጠላትን ፡ አስመስሎ ፡ ማታለል ፡ እንድትመለከቱትና ፡ ለመጨውም ፡ ቢሆን ፡ እንድታስቡበት ፡ እንድትጠንቀቁበትም ፡ እናስታውሳለን ፡፡

## ኢጣሊያኖች ፡ በሐሰት ፡ ፕሮፖጋንዳ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አርበኛና ፡ ሕዝብ ፡ የበተኑት ፡ የሐሰት ፡ ጽሑፍ ፡፡

ኢትዮጵያ ፡ እጇቿን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትዘረጋለች ፡፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡

### አ ዋ ጅ ፤

### የሸዋ ፡ ሕዝብ ፤

በኢጣልያኖች ፡ ላይ ፡ የምትነሱበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሷል ፡ እንግሊዞች ፡ እንረዳሃለን ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ ሰጥተውኛል ፤ እንደምታውቁትም ፡ ወረቀቱን ፡ የሚያደርሱላችሁ ፡ የእንግሊዝ ፡ አውሮፕላኖች ፡ ናቸው ፤ ምናልባት ፡ እናንተ ፡ ይህንን ፡ እንግሊዞች ፡ እንረዳችኋለን ፡ ብለው ፡ የሰጡትን ፡ ቃል ፡ አታምኑትም ፡ ይሆናል ፤ አሁን ፡ ግን ፡ በውነት ፡ እንዲረዱን ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡፡

እንግሊዝ ፡ ከኢጣልያኖች ፡ ጋር ፡ የምታደርገው ፡ ጦርነት ፡ ለጊዜው ፡ የጠነከረ ፡ መሆኑ ፡ እውነት ፡ ነው ፡፡ ኢጣልያኖች ፡ ባደረጉት ፡ ድል ፡ ይመኩሉ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ ድል ፡ የእንግሊዝ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡፡

እስከ ፡ ጥቂት ፡ ወራት ፡ ድረስ ፡ ቢዘገይም ፡ ከሚመጣው ፡ ክረምት ፡ በኋላ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የሚያደርግልን ፡ እርዳታ ፡ ሲፈጸም ፡ ታያላችሁ ፡፡ ስለዚህ ፡ ጥርጥር ፡ ሳታገቡ ፡ በትዕግሥት ፡ ጠብቁ ፡፡ ከእንግሊዞች ፡ ጋራ ፡ በመሆኔ ፡ በሃይማኖቴም ፡ ጸረ ፡ ማርያም ፡ የሆንኩ ፡ አይምሰላችሁ ፡ የኔ ፡ ሃይማኖት ፡ የተዋህዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጥቅም ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ለባዕድ ፡ የሚያገለግሉት ፡ ለራስ ፡ ኃይሉ ፤ ለራስ ፡ ሥዩም ፤ ለራስ ፡ ጌታቸው ፤ ለራስ ፡ ከበደ ፤ ለራስ ፡ ገብረሕይወት ፤ ለደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ብሩ ፤ ለደጃዝማች ፡ አመዴ ፡ አሊ ፤ ለደጃዝማች ፡ አያሌው ፡ ብሩ ፡ ለደጃዝማች ፡ ኃብተ ፡ ሚካኤል ፤ ለደጃዝማች ፡ አምባቸው ፡ ገሠሠ ፤ ለደጃዝማች ፡ መስፍንና ፡ እነሱንም ፡ ለመሰሉት ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ ርኅራኄ ፡ የተገባቸውን ፡ ቅጣት ፡ እንሰጣቸዋለን ፡፡

ስለኢትዮጵያ ፡ ጥቅም ፡ ነው ፡ የሚሉትስ ፡ ንጉሡዋን ፡ ካጣች ፡ በኋላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ምን ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ልትችል ፡ ነው ። በፈረንሣይ ፡ ድል ፡ መሆን ፡ ተስፋችሁን ፡ አትቁረጡ ። ፈረንሳይ ፡ ምን ፡ጊዜም ቢሆን ፡ ጠላታችን ፡ መሆኗን ፡ ሁላችሁም ፡ ታውቃላችሁ ። እኛ ፡ አለን ፡ ብለን ፡ በሙሉ ፡ የምንተማመንበት ፡ እንግሊዝ ፡ ነው ፤ ራስ ፡ ካሣና ፡ ፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ ይህን ፡ አሁን ፡ ከኢጣልያኖች ፡ ጋር ፡ የምናደርገውን ፡ ጦርነት ፡ ፈቃዳቸው ፡ ሆኖ ፡ አልተቀበሉትም ፡ ተብሎ ፡ የተወራው ፡ ውሸት ፡ ነው ፤ እንዲሁም ፡ ለኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ ሊገቡ ፡ በምስጢር ፡ የመሐላ ፡ ቃላቸውን ፡ አቅርበዋል ፡ የተባለው ፡ ውሸት ፡ ነው ።

ራስ ፡ ሥዩም ፡ ራስ ፡ ጌታቸውና ፡ ሌሎችም ፡ አንዳንድ ፡ መኳንንቶች ፡ የሰጡዋቸውን ፡ ክፉ ፡ ምክር ፡ ተከትለው ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ ለመግባት ፡ አስበው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሃሳባቸውን ፡ አልፈጸሙትም ።

ኅዳር ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ለዘላዓለም ፡ ትኑር ፡
ታላቂቱ ፡ ብሪታንያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ፡

ኢትዮጵያ ፡ እጆቿን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትዘረጋለች ።
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡

## አ ዋ ጅ ፤

### ለጎጃም ፡ ሕዝብ ፡

እውነተኛነቱንና ፡ ቃሌም ፡ የማይታበል ፡ መሆኑን ፡ ታውቃላችሁ ። በኢጣልያኖች ፡ ላይ ፡ የምትነሱበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሷል ።

ይኸውም ፡ እንግዲህ ፡ ታላቂቱ ፡ እንግሊዝ ፡ እርዳታዋን ፡ ልታደርግልን ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በትዕግሥት ፡ ጠብቁ ፤ ኃይላችንንም ፡ ከሚመጣው ፡ ክረምት ፡ በፊት ፡ ታዩታላችሁ ። እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በጀግንነት ፡ ሲመራችሁ ፡ የቆየውን ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬን ፡ አሁን ፡ ለጊዜው ፡ ራስ ፡ ብለን ፡ ሾመነዋል ። ኢጣልያኖችንም ፡ ድል ፡ ካደረግን ፡ በኋላ ፡ ዘውድ ፡ ሰጥተን ፡ በሙሉ ፡ ጎጃም ፡ ላይ ፡ እናነግሠዋለን ።

ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ፡
ታላቂቱ ፡ ብሪታንያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ፡
ኅዳር ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡



ኢትዮጵያ ፡ እጆቿን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትዘረጋለች ።
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡

## አ ዋ ጅ ፤

### ለጎጃም ፡ ሕዝብ ፡

ታኅሣሥ ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ በጎጃም ፡ ላይ ፡ የተጣለው ፡ አዋጅ ፡ በስህተት ፡ የተደረገ ፡ ነው ፡ ጠላት ፡ የሚናገረውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አትመኑ ፡ እኛ ፡ ድል ፡ ለማድረግ ፡ የሚአስፈልገንን ፡ እናዘጋጃለን ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ኢጣልያና ፡ ጀርመን ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ በያለበት ፡ ስለሚወጉን ፡ ድሉ ፡በቶሎ፡ ሊፈጸም ፡ አይችልም ።

የፈረንሳይ ፡ መውደቅ ፡ ለኛ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ሆኖብናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ኢጣልያና ፡ ጀርመን ፡ ኃይላቸውን ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡ አድርገው ፡ ቢቃወሙን ፡ እኛ ፡ ድል ፡ ለማድረግ ፡ እንደምንችል ፡ ስለምናውቅ ፡ ጦርነቱን ፡ ያለማቋረጥ ፡ እንቀጥላለን ።

ዕድላችን ፡ ከእንግሊዝ ፡ ዕድል ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ስለሆነ ፡ የእንግሊዝ ፡ ጠባቂነት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸጥታ ፡ ምልክት ፡ ነው ፤ እንግሊዝ ፡ በሥልጣኔና ፡ በመልካም ፡ አኗኗር ፡ ጎዳና ፡ ትመራለች ፡ የመጀመሪያው ፡ እርዳታ ፡ ተልኮልናል ። ስለዚህ ፡ እንግሊዞች ፡ ጉዳት ፡ ያደርጉብናል ፡ ብላችሁ ፡ መስጋት ፡ አይገባችሁም ። በሱዳን ፡ ወታደሮችና ፡ በደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ግጭት ፡ በጣም ፡ ቀላል ፡ ነው ።

እንደዚሁም ፡ ወደፊት ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ሌላ ፡ ጉዳት ፡ ቢያገኛችሁ ፡ ካሣችሁን ፡ እንደምትአገኙ ፡ እኔ ፡ አረጋግጥላችኋለሁ ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ ደርቡሽ ፡ ወታደሮች ፡ እርዳታ ፡ ምንም ፡ ለመሥራት ፡ አይቻለንም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ እኔን ፡ ሃይማኖቱን ፡ ለውጧል ፡ ብሎ ፡ ማሰብ ፡ አለማስተዋል ፡ ይሆናል ፤ እንግሊዞች ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥተውናል ፤ ስለዚህ ፡ ወደፊት ፡ በኛ ፡ ምክንያት ፡ ጉዳት ፡ ለሚያገኘው ፡ ሁሉ ፡ ካሣውን ፡ እንሰጣለን ።

ደግሞ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ ግባት ፡ የገቡትን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እንግሊዞች ፡ መሣሪያ ፡ እየሰጡ ፡ በግድ ፡ ያዋጉዋቸዋል ፡ ተብሎ ፡ የተወራው ፡ ወሬ ፡ ውሸት ፡ ነውና ፡ አትመኑ ፤ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ መዋጋታቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ ለወደፊቱ ፡ ግን ፡ አስፈላጊ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ የገቡት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ በጦርነቱ ፡ አይገቡም ።

የኛ ፡ አውሮፕላኖችና ፡ የጀርመን ፡ አውሮፕላኖች ፡ የሎንደንን ፡ ከተማ ፡ በጭራሽ ፡ አጥፍተውታል ፡ እያሉ ፡ ኢጣልያኖች ፡ የሚያወሩ ላችሁን ፡ ወሬ ፡ አትስሙ ። እርግጥ ፡ ነው ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ያገኘን ፡ ጉዳት ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ያገኘን ፡ ጉዳት ፡ ጦርነቱን ፡ ለመቀጠል ፡ የሚከለክለን ፡ አይደለም ።

## የሐሰት ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ መሆኑን ፡ በማስረዳት ፡ ስለጻፍሁዋቸው ፡ ደብዳቤዎች ።

እነሆ ፡ ጠላታችን ፡ ኢጣልያ ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ የአዋጅ ፡ ቃል ፡ በማስመሰል ፡ ከበተናቸው ፡ የሐሰት ፡ ጽሑፎች ፡ አንዳንዶቹን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ተመልክታችኋል ። ይህንንም ፡ በማስተባበል ፡ ለአርበኞች ፡ መሪ ዎች ፡ ከጻፍሁዋቸው ፡ ቃሎች ፡ ጥቂቶቹን ፡ በሚከተለው ፡ እገልጻለሁ ።

## ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ።

እንደምን ፡ ሰንብተዋል ፡ እኔ ፡ አምላክ ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ። ከእኛ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ራቅ ፡ ካለው ፡ ቦታ ፡ በእርስዎና ፡ በልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ክፍል ፡ በምሥራቅ ፡ ጎጃም ፡ መሪዎቹና ፡ አርበኞቹም ፡ በመተባበርና ፡ በአንድነት ፡ ሆናችሁ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ስምምነት ፡ ማድረጋችሁን ፡ ጠላት ፡ ስለሰማ ፡ ልባችሁን ፡ አሻክሮ ፡ አንድነታችሁን ፡ እንዲያፈርስ ፡ ለማድረግ ፡ በግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ቃልና ፡ ማኅተም ፡ አስመስሎ ፡ ማውራትና ፡ ያዋጅም ፡ ወረቀት ፡ በሌሊት ፡ መጣል ፡ ጀምሮአል ፡ ማለትን ፡ ሰማን ። ስለዚህ ፡ ይኸ ፡ ነገር ፡ በፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ። ሕዝቡ ፡ እንዲአውቀው ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ ገልጻችሁ ፡ በየጊዜው ፡ አዋጅ እንዲነገር ።

ሁለተኛም ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ ይኸን ፡ ወረቀት ፡ ወድቆ ፡ አገኘሁ ፡ እያለ ፡ ሲአብል ፡ የሕዝብ ፡ ልብ ፡ የሚከፋፍል ፡ ሰው ፡ ቢገኝ ፡ ተይዞ ፡ ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ መቀበል ፡ የሚአስፈልገው ፡ ነውና ፡ እየተያዘ ፡ የሚቀጣበትን ፡ አኳኋን ፡ እንዳስታውቃችሁ ፡ በተያዘ ፡ ጊዜ ፡ እንድትጠይቁን ።
በምሥራቁ ፡ ጎጃም ፡ ስላለው ፡ ባንዳ ፡ መኳንንት ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፍ ልኝ ፡ ብለውኝ ፡ እንደጻፍኩልዎ ፡ ሳይሠሩበት ፡ ቀርተው ፡ ተቀደሙ ። አሁንም ፡ በውስጥዎ ፡ እንዲህ ፡ እንዳይሆን ፡ ያስቡበት ።

ታኅሣሥ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
አባቶ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ።



ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፤

እጅጉን ፡ እንደምን ፡ ሰንብተዋል ፤ እኔ ፡ አምላክ ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ። ከግርማዊ ፡ ንጉሡ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ተልከን ፡ የጦር ፡ መሪዎች ፡ የሆ ናችሁ ፡ ሁሉ ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ በመተባበር ፡ እየተላላካችሁ ፡ ጠላት ፡ እንዲጠቃ ፤ ግርማዊ ፡ እስኪደርሱ ፡ ባያያዛችሁ ፡ እንድትጸኑ ፡ የተላከውን፡ ነግሬአችሁ ፡ ፈቃዳችሁ ፡ ሆኖ ፡ በዚሁ ፡ ልትሠሩ ፡ መተባበራችሁን ፡ የሰማ ፡ ጠላት ፡ ያልተደረገውንና ፡ ያልታሰበውን ፡ የሐሰት ፡ ስብከት ፡ በግርማዊ ፡ ቃል ፡ አስመስሎ ፡ ሠርቶ ፡ በርስዎና ፡ በልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ አገር ፡ በምሥራቁ ፡ ጎጃም ፡ የሐሰት ፡ አዋጅ ፡ የኛ ፡ ያይደለ ፡ ከጠላት ፡ የተፈጠረ ፡ በአይሮፕላን ፡ ወደቀ ፡ ማለትን ፡ ሰማን ። ስለዚህ ፡ እናንተ ፡ መሪዎቹ ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ አውቃችሁ ፡ ለሕዝቡ ፡ እውነት ፡ እንዳይመስለው ፡ የጠላት ፡ ተንኰል ፡ መሆኑን ፡ በየገባያው ፡ በአዋጅ ፡ እንዲነገር ፡ በማክበር ፡ አስታውቅዎታለሁ ።

ፈረሶችና ፡ መልክተኛ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ማድረጋችን ፡ ይኸን ፡ የመ ሰለ ፡ የሐሰት ፡ ስብከት ፡ በመራቃችን ፡ በመሐከላችን ፡ እንዳይፈጠርና ፡ ወሬ ፡ በማጣት ፡ እውነት ፡ እንዳይመስል ፡ ነውና ፡ የመልክተኞቹና ፡ የፈ ረሶቹ ፡ ድርጅት ፡ ሥራው ፡ በቶሎ ፡ አልቆ ፡ ሳናቋርጥ ፡ በመላላክ ፡ ሥራ ችንን ፡ እንድንጀምር ።

ታኅሣሥ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጻፈ ፡
አባቶ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ።

ይድረስ ፡ ካቶ ፡ እንግዳ ፤ ካቶ ፡ መኰንን ፡

እንደምን ፡ ሰንብታችኋል ፡ እኛ ፡ አምላክ ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነን ። ከፈረስ ፡ ቤትና ፡ እነሴ ፡ ካሉ ፡ ሠራተኞቻችን ፡ ዘንድ ፡ ኢጣልያኖች ፡ ያደ ረጉት ፡ የፕሮፓጋንዳ ፡ ደብዳቤ ፡ ደረሰን ። ይኸንንም ፡ ማድረጋቸው ፡ መሪ ፡ የሆኑትን ፡ አርበኞች ፡ ልብ ፡ የሚከፍልና ፡ የሚአሻክር ፡ ሥራ ፡ መሥራታቸው ፡ ነው ።

የዚህ ፡ ተቃዋሚነቱ ፡ እኛ ፡ ለምንሠራው ፡ ያንድነታችንና ፡ የመተ ባበርን ፡ የሚአፋልስ ፡ ስለሆነ ፡ በነገሩ ፡ እንድታስቡበትና ፡ አዋጅ ፡ እን ዲደረግ ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ጽፌአለሁና ፡ በትጋት ፡ አስታውሳ ችሁ ፡ የኢጣልያን ፡ ደብዳቤ ፡ ቃል ፡ በፍጹም ፡ ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ የሚገ ልጽ ፡ ያዋጅ ፡ ቃል ፡ በየገባያው ፡ እንዲነገር ፡ አድርጉ ።

እናንተም ፡ ዲማም ፡ ያለው ፡ ማኅበር ፡ ለዚህ ፡ ተቃዋሚ ፡ ሆናችሁ ፡ ለሕዝቡና ፡ ለየክፍሉ ፡ ላለው ፡ አርበኛ ፡ ሁሉ ፡ አስረዱ ። እናንተስ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ጥፋት ፡ የሚሆን ፡ ነገር ፡ ስትሰሙ ፡ ለምን ፡ አትጽፉል ንም ። በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ መልክተኞች ፡ ተሰናድተው ፡ ሥራቸውን ፡ ሳያ

ቋርጡ ፡ ይሠራሉ ። በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ እስካሁን ፡ ባለመጀመሩ ፡ በጣም ፡ አዝንናል ። አሁንም ፡ በቶሎ ፡ እንዲቋቋም ፡ ድከሙ ። ስለ ፡ ሸዋ ፡ የሰማ ችሁት ፡ ቢኖር ፡ ጻፉልኝ ። ስለ ፡ አቶ ፡ ተገኝስ ፡ ምን ፡ ሰማችሁ? ሁሉ ንም ፡ አጣሩና ፡ ጻፉልኝ ።

ታኅሣሥ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ።

## ላገር ፡ ማስረጃ ።

ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬን ፡ ራስ ፡ ብለን ፡ ሹመነዋል ፡ ኢጣ ልያኖችን ፡ ድል ፡ ካደረግን ፡ በኋላ ፡ ዘውድ ፡ ሰጥተን ፡ በሙሉ ፡ ጎጃም ፡ እናነግሠዋለን ፡ የሚለውን ፡ የላኩልኝ ፡ የስብከት ፡ ወረቀት ፡ ደረሰኝ ። ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ዛሬ ፡ ይኸን ፡ እንደማያደርጉ ፡ ስለማውቅ ፡ ወድያው ፡ ስመለከተው ፡ ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ ተረዳሁት ።

ሁለተኛም ፡ ይኸ ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ አለ መምጣቱን ፡ የሚአስረዳ ፡ ያዋጅ ፡ ቃል ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ተብሎ ፡ የዚህ ፡ የላካችሁት ፡ ደብዳቤ ፡ በፊት ፡ ደጃዝማች ፡ የሚለው ፡ የሌላ ፡መሆ ኑን ፡ አስረግጠን ፡ ስለአየን ፡ አንድ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ።

ሶስተኛ ፡ በአዋጅ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ጃንሆይ ፡ ፈርመው ፡ አያው ቁም ።

አራተኛ ፡ የግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ትልቁ ፡ ባለአንበሳ ፡ ማኅተም ፡ ከላይ ፡ እንጂ ፡ በታች ፡ ታትሞ ፡ አያውቅም ።

አምስተኛ ፡ ይኸም ፡ ሁሉ ፡ ሕዝቡ ፡ እንዳይወላውል ፡ ለማድረግ ፡ ትላንትና ፡ ታኅሣሥ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይን ፡ በቴሌግራም ፡ ጠይቂ ፡ በፍጹም ፡ ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ መልስ ፡ ሰጥተው ፡ አረጋግጠ ውልኛል ።

ታኅሣሥ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ።

በየስፍራው ፡ የሚገኙት ፡ አርበኞች ፡ ታማኝነታቸውን ፡ በመግ ለጽ ፡ ደብዳቤ ፡ እየጻፉ ፡ በኔ ፡ በኩል ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ይልኩ ፡ ነበር፡ ለምሳሌም ፡ ያህል ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉትን ፡ ደብዳቤዎች ፡ እገልጻለሁ ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ዕድሜና ፡ ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ እያልኩ ፡ ሰላምታ ዬን ፡ አቀርባለሁ ። እኔ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምላክ ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ፡



ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደሚሰሙት ፡ ለሃገራችንና ፡ ለባንዲራችን ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ስንከራከር ፡ ነበር ፤ ይህንኑም ፡ ሁሉ ፡ በቆረጠ ፡ ልብ ፡ ለነጻነታችን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ነበረ ፡ የምንሠራ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ነጻነት ፡ የመሣሪያ ፡ እርዳታ ፡ በ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከታላ ቂቱ ፡ ብሪታንያ ፡ መንግሥት ፡ ሕዝባችን ፡ መቀበሉን ፡ እየሰማን ፡ በጣም፡ ደስ ፡ አለን ፡ እኛም ፡ በመሣሪያና ፡ በጥይት ፡ ማነስ ፡ የተነሳ ፡ ነው ፡እንጂ ፡ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ ጉልበት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ምሽ ግና ፡ ከተማ ፡ ለማስለቀቅ ፡ ቀላል ፡ ነበር ፤ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የሰደዱልኝ ፡ ወረቀት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ሌላው ፡ ሁሉ ፡ አልደረሰኝም ። እኔም ፡ እበጌምድር ፡ መኳንንትና ፡ አርበኛ ፡ ጋር ፡ ፈርሚ ፡ ልኬብዎ ፡ ነበር ፡ አሁንም ፡ ለበጌምድር ፡ የተሰጠንን ፡ መሣሪያ ፡ እታሰበልን ፡ቦታ ፡ እንድናስነሳ ፡ እናመለክታለን ፤ ሁለተኛ ፡ የሚላክ ፡ መልክተኛ ፡ የተመ ረመረ ፡ ለነጻነቱ ፡ የሚአስብ ፡ ታማኝ ፡ ሰው ፡ እንዲላክልን ፡ እንጂ ፡ያል ሆኑ ፡ መልክተኞች ፡ እየመጡ ፡ የተላከውን ፡ ቃል ፡ ሳያደርሱ ፡ አርበኛ ውን ፡ እርስ ፡ በራሱ ፡ እያጣሉ ፡ ሥራ ፡ እያበላሹ ፡ ለጠላታችን ፡ ረዳት ፡ ሆኑ ፤ በዚህ ፡ ነገር ፡ እንዲጠነቀቁበት ፡ አሳስባለሁ ፤ ለጦርነቱ ፡ ግን ፡ ራዲዮን ፡ በመጣል ፡ በኰሚሲዮን ፡ አውሮፕላን ፡ እየተቀበልን ፡ በፍጥ ነት ፡ ካምቦውን ፡ ለማፍረስ ፡ እንችላለን ፤ ፫ኛ ፡ ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ወረቀት ፡ ሲላክለት ፡ ለኔ ፡ ባለመላኩ ፡ በጣም ፡ አዘንኩ ። እኔ ፡ ግን ፡ የሥራዬንና ፡ የድካሜን ፡ ዋጋ ፡ አገኛለሁ ፡ በምልበት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ በመቅረቱ ፡ አዝ ናለሁ ፡ ይላል ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ጦር ፡ መሪ ፡ የሐንስ ፡ ኢያሱ ፤

ታኅሣሥ ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

ማመልከቻ ፡

ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡

ክቡር ፡ የአዋጅ ፡ ማኅተምዎ ፡ በልጅ ፡ ተገኝ ፡ እጅ ፡ በደረሰን ፡ጊዜ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ የተቀበልነው ፡ ስቃይና ፡ የፈሰሰው ፡ ደማችን ፡ ተረስቶ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ደስታ ፡ ሆነልን ፤ ወደፊትም ፡ ይኸንን ፡ ደስታ ችንን ፡ በፍጥነት ፡ እንዲፈጸምልን ፤ ሁለተኛ ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡በሰላ ድንጋይ ፡ በሞላሌ ፡ እነዚህ ፡ ሶስት ፡ ምሽጎች ፡ መንገድ ፡ ከልካዮች ፡ ስለሆኑ ፡ በፍጥነት ፡ የአይሮፕላን ፡ አደጋ ፡ እንዲወድቅባቸው ፡ ሶስተኛ ፡ የመሣሪያና ፡ የጥይት ፡ ነገር ፡ ችግራችን ፡ ነው ፡ በሚአፋጥን ፡ መሣሪያ ፡ እንዲቀርብልኝ ፡ ይህ ፡ ከሆነልን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ለመግባት ፡ ይቻላል ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ቸርነቱ ፡ እማያልቅበት ፡ አምላክ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ያገናኘን ፡ እያልን ፡ ከመሬት ፡ ወድቀን ፡ እናዝናለን ።

ታኅሣሥ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
አበበ ፡ አውራረስ ፡

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡

መድኃኒ ፡ ዓለም ፡ ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ ብዬ ፡ ከዙፋንዎ ፡ ሥር ፡ ወድቄ ፡ መሬት ፡ እስማለሁ ። አምላክዎ ፡ አልተለየኝም ፡ እኔ ፡ እስካሁን ፡ ደህና ፡ ነኝ ፡

ስለኢትዮጵያ ፡ የድካምዎን ፡ ዋጋ ፡ አገኙትው ፡ ደብዳቤዎ ፡ በደረሰኝ ፡ ጊዜ ፡ ዕለት ፡ ያየሁዎ ፡ መስሎኝ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለኝ ።

የተጀመረውን ፡ ተስፋ ፡ አስፈጽሞ ፡ ያሳየኝ ፡ የማለት ፡ ልቅሶዬን ፡ ወደ ፡ ፈጣሪዬ ፡ አላቋርጥም ።

የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለመልክተኛው ፡ ነግሬዋለሁ ፡ ይጠይቁት ።



በጅሮንድ ፡ ለጥ ፡ ይበሉ ፡ ገብሬ ።

የረገጡትን ፡ መሬት ፡ ለመሳም ፡ ያብቃኝ ።

ታኅሣሥ ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

በጅሮንድ ፡ ለጥ ፡ ይበሉ ፡

## ምዕራፍ ፡ ፷፩ ።

## ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ወሰን ፡ አልፈው ፡ አሜድላ ፡ ላይ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ስለመትከላቸው ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከሱዳን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ ገብተው ፡ ጥር ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አሜድላ ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ተከሉ ። በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ መምጣት ፡ የሚገልጽ ፡ የአዋጅ ፡ ቃል ፡ ታትሞ ፡ በያገሩ ፡ በአውሮፕላን ፡ ስለተበተነ ፡ የአርበኞቻቸው ፡ ልብ ፡ በደስታ ፡ ተሞላ ። ሕዝቡም ፡ ከጠላት ፡ ቀንበር ፡ ወጥቶ ፡ ነጻነቱን ፡ የሚያገኝበትን ፡ ዕለት ፡ በተስፋ ፡ ይጠባበቅ ፡ ጀመር ።

በጥር ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ለሕዝባቸው ፡ ያሰሙት ፡ የአዋጅ ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ፡

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

አዋጅ ።


የአገሬ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡

ስማ ፡

ዳኝነቱ ፡ ለማያዳላ ፡ የኃይለኞችን ፡ ክንድ ፡ ለሚሰብር ፡ ተጠቂዎችን ፡ ለሚያጽናና ፡ አምላክ ፡ ምስጋና ፡ ክብር ፡ ይሁን ።

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ደመኛ ፡ የነበረች ፡ ጠላታችን ፡ ኢጣልያ ፡ ወሰናችንን ፡ ጥሳ ፡ በግፍ ፡ ጦርነት ፡ አገራችንን ፡ ስለወረረች ፡ በተቻለ ፡ ተከላክለን ፡ እርዳታ ፡ ለመጠየቅ ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ሄደን ፡ ሳለ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ሠይፋችሁን ፡ ሳትከቱ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማችሁን ፡ ሳታጥፉ ፡ለባዕድ ፡ አንገዛም ፡ በማለት ፡ በመሣሪያ ፡ ብዛት ፡ ከሚበልጣችሁ ፡ ጨካኝ ፡ ጠላት ፡ የባኅርይ ፡ ጀግንነታችሁን ፡ መሣሪያ ፡ አድርጋችሁ ፡ ቀን ፡ከሌት ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ ስትጋደሉ ፡ ጠብቃችሁን ፡ ይኸው ፡ አሁን ፡ እንደምታዩት ፡ የ፭ ፡ ዓመት ፡ ትግላችሁ ፡ የድካማችሁንና ፡ የመሥዋዕትነታችሁን ፡ ፍሬ ፡ ለማየት ፡ እንድትበቁ ፡ አደረጋችሁ ።

ጠላታችንን ፡ ከአገራችን ፡ ፈጽሞ ፡ ለማስወጣት ፡ ሙሉ ፡ ነጻነታችንን ፡ ለማስመለስ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የገባችልንን ፡ የታላቂቱን ፡ ብሪታኒያ ፡ መንግሥት ፡ እርዳታ ፡ ይገፎልህ ፡ መምጣቴን ፡ ከዚህም ፡ ቀደም ፡ አስታውቄሀለሁ ። ፬ ፡ ዓመት ፡ ከ፰ ፡ ወር ፡ ከተለየሁ ፡ በኋላ ፡ ዛሬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ተመልሼ ፡ ወደ ፡ ተወደደች ፡ አገሬ ፡ መግባቴንና ፡ በናፈትሁህም ፡ ሕዝቤ ፡ መካከል ፡ መገኘቴን ፡ ስነግርህ ፡ ደስታዬ ፡ መጠን ፡ የለውም ።



ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ከአውሮፕላን ፡ ሲወርዱ ።



## የአገሬ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡

መንግሥቴን ፡ ነጻነቴን ፡ አገሩን ፡ ያጣ ፡ ሕዝብ ፡ የሚደርስበትን ፡ መረር ፡ ሕይወት ፡ ሁላችሁም ፡ የምታውቁት ፡ ነው ።

የተወደደች ፡ አገራችንን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በበለጠ ፡ ንቃትና ፡ የጋለ ፡ ጉልበት ፡ በየበኩላችን ፡ የምንጠብቅበትና ፡ የምናገለግልበት ፡ ዘመን ፡ መከፈቱ ፡ ነው ።

ቸር ፡ እግዚአብሔር ፡ የምሕረት ፡ ፊቱን ፡ የመለሰልን ፡ ለሁላችንም ፡ ስለሆነ ፤ በግድም ፡ በውድም ፡ ቢሆን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በኢጣልያኖች ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ ሆነህ ፡ አገርህንና ፡ ንጉሥህን ፡ የበደልህ ፡ ሁሉ ፡ ባለፈው ፡ ጥፋትህ ፡ ምሬሀለሁና ፡ ዘርህን ፡ ለማጥፋት ፡ ርስትህን ፡ ለማቅናት ፡ ስምህን ፡ ለመደምሰስ ፡ ደምህን ፡ ለማርከስ ፡ ቆርጦ ፡ በመጣው ፡ ጠላታችን ፡ ላይ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ክንድህን ፡ አንሳ ። ከኢትዮጵያ ፡ ጠርገህ ፡ አስወጣው ።

ኢጣልያ ፡ በዓየርም ፡ በባሕርም ፡ በምድርም ፡ በታላቂቱ ፡ እንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ ተይዛ ፡ ተጨንቃለች ። በአገራችንም ፡ ያሉት ፡ የኢጣልያ ፡ ወታደሮች ፡ ከምታምንባችሁ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጀግኖች ፡ አያልፉም ።

የታላቂቱ ፡ ብሪታንያ ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ በመረር ፡ ፈተናችን ፡ ጊዜ ፡ ልብ ፡ በሚነካ ፡ አደራረግ ፡ በቸርነት ፡ ስለተቀበሉኝና ፡ ለማይጠፋ ፡ ውለታቸው ፡ በእኔና ፡ በእናንተ ፡ ስም ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ ምስጋናዬን ፡ እገልጻለሁ ።

ኢትዮጵያ ፡ በነጻነት ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ፡
ታላቂቱ ፡ ብሪታንያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ፡
ጥር ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

እኔም ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ መምጣት ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፡ ከልብ ፡ የመነጨ ፡ ደስታዬን ፡ በመግለጽና ፡ በተጨማሪም ፡ የሥራ ፡ ጉዳዮችን ፡ በመዘርዘር ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ጽፌ ፡ ላክሁ ።

ለግርማዊ ፡ ጌታዬ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡

መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ዕድሜ ፡ ከጤና ፡ አስተባብሮ ፡ ይስጥልኝ ፡ እያልኩ ፡ ባሪያዎ ፡ መሬት ፡ እስማለሁ ፤

ግርማዊነትዎ ፡ ከጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ኃይልዎ ፡ ተቀንሶ ፡ ሲረዱት ፡ የተሰደዱላትን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ብዙ ፡ ኃይል ፡ ጨምረው ፡ ከውስጧ፡

መገኘትዎን ፡ ስሰማ ፡ አጥብቆ ፡ ደስ ፡ አለኝ ፤ እንኳን ፡ ለዚህ ፡ አበቃዎ ፡ ለቸርነቱ ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ አምላክ ፡ ፍጻሜውን ፡ አሳምሮ ፡ የተቀደሰ ችዋን ፡ ከተማዎን ፡ ለማየት ፡ ያብቃዎት ፤

ከዚህ ፡ ደስታዬ ፡ በኋላ ፡ የሥራ ፡ ጉዳይ ፡ አመለክታለሁ ፤

፩/ መሥሪያ ፡ ቤታችን ፡ ጥሩ ፡ አልሆነም ፡ በፊትም ፡ ታሞ ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ ጨርሶ ፡ ሊሞት ፡ ነው ፡ ስለዚሁም ፡ ጉዳይ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚአስፈልግ ፡ ለመማከር ፡ ደብዳቤዎቼን ፡ እያከታተልሁ ፡ ጽፌ ፡ ነበር ፤ መልሱን ፡ እስካገኝ ፡ እጠባበቃለሁ ፡ በማስጋሴ ፡ ደርሼ ፡ መመለስ ፡ እችላለሁ ፡

፪/ እስከዚያው ፡ የማመለክተው ፡ በፍጥነት ፡ የሚታሰብበት ፡ የምሥራቅ ፡ ጎጃምን ፡ አኳኋን ፡ ነው ፤ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ብቸና ፡ ላይ ፡ሆነው ፡ በብዙ ፡ ዓይነት ፡ ሰበከት ፡ ስለሆን ፡ የሚሰብኩት ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀና ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ በእርቅ ፡ ምክንያት ፡ መገናኘታቸውን ፡ ባለፈው ፡ ወረቀቴ ፡ አስታውቄ ፡ ስለነበረ ፡ ደርሷል ፡ ስል ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

፫/ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ እንደጻፈልኝ ፡ እርቁ ፡ ከአንገት ፡በላይ ፡ ነው ፡ ቢለንም ፡ ሕዝቡ ፡ ታረቁ ፡ መባሉን ፡ ብቻ ፡ በመስማቱ ፡ ልቡ ፡ ተከፍሏል ፡ የራስ ፡ ኃይሉን ፡ ኃይል ፡ አያስጋውም ፡ የሚያስጋው ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀን ፡ መሣሪያ ፡ አድርገው ፡ ያጠቁናል ፡ በማለት ፡ እገሩ ፡ ሰግቷል ፡ ስለዚህ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚሻል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሃሳብ ፡ ብና ቀርብ ፡ አልተፈጸመም ፡ ለምሥራቁ ፡ ጎጃም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የአውሮፕላን ፡ አደጋ ፡ የደረሰው ። ያውም ፡ ፫ ፡ ቦምብ ፡ ማርቆስ ፡ ላይ ፡ ጥሎ ፡ ነበር ። ከዚያውም ፡ አንድ ፡ ፈንድቶ ፡ ሁለቱ ፡ ሳይፈንዳ ፡ ስለ ቀረ ፡ ለጠላት ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ ረዳት ፡ ሆኖአል ፡

፬/ የምሥራቁ ፡ ጎጃም ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የሚአሰጋ ፡ ስለሆነ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬ ፡ ቤታቸውን ፡ ለቀው ፡ ወደኛ ፡ ቀርበዋል ። ስለመንገዳቸው ፡ ግን ፡ እንዲሄዱ ፡ ይጣደፋሉ ፡ መሣሪያው ፡ ስልአልደ ረሳቸው ፡ ይጠባበቃሉ ፡ እንጂ ፤

፭/ ከበጌምድር ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ መሣሪያ ፡ ለማንሳት ፡ መምጣት ፡ ጀምሯል ፤ ዛሬ ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ በላያ ፡ የፈታውራሪ ፡ በላይ ፡ ተሰማ ፡ ሰዎች ፡ ከስቴ ፡ የመጡ ፡ ፫፻፸ ፡ ሰው ፡ ተነስቷል ፡ አጋፋሪ ፡ ያረጋልም ፡ ደንሳ ፡ ደርሰው ፡ ለዛሬ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ እገባለሁ ፡ ብለው ፡ ጽፈውልኝ ፡ እጠብቃለሁ ። እንደመጡ ፡ ወደዚያው ፡ ልልካቸው ፡ ነው ፡ ከ፫፻፸ ፡ ውስጥ ፡ ለጃንሆይ ፡ ወታደር ፡ የሚሆኑም ፡ አሉበት ፡

፮/ ወደ ፡ ቢጌምድር ፡ ልኬው ፡ የነበረ ፡ አለቃ ፡ ፈጠነ ፡ የሚባለው ፡ እንደነገረኝ ፡ የቢጌምድር ፡ ሕዝብ ፡ በጃንሆይ ፡ መምጣትና ፡ መኖ



ርም ፡ አጥብቆ ፡ ይጠራጠራል ፡ ብሎ ፡ ነውና ፡ የነገረኝ ፡ መሣሪያ ፡ ለማምጣት ፡ የተሰበሰበውን ፡ ሕዝብ ፡ እንዲያዩት ፡ ቢሆን ፡ መልካም ፡ ነው ፤

፯/ ከደጃዝማች ፡ ደስታ ፡ እሸቴ ፡ የደረሰው ፡ ወሬ ፡ ዓባይን ፡ ተሻግረው ፡ እወሊጋው ፡ መሬት ፡ ከደረሱ ፡ በኋላ ፡ አጋምሳ ፡ የሚባለው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ተጣግተው ፡ ኃይል ፡ ስለአነሳቸው ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ አፈግፍገው ፡ መሣሪያ ፡ ለማንሳት ፡ የላኩት ፡ ሰዎቻቸው ፡ እስኪሄድ ፡ ይጠብቃሉ ፡ በጦሩም ፡ ላይ ፡ ከጠላት ፡ ፯ ፡ ሰዎች ፡ የሞቱ ፡ ፲ ፡ የቆሰሉ ፤ ከኛ ፡ ወገን ፡ የሞቱ ፡ ፯ ፡ የጠፉ ፡ ፯ ፡ አኳኋኑ ፡ ገና ፡ ያልታወቀ ፡ ነው ፡ በአምሩና በጉድሩ ፡ ያለውን ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ለቀምት ፡ ያለው ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ለርዳታ ፡ ጠርቶት ፡ ሄደ ፡ ይባላል ።

ከበጌምድር ፡ ከመጡ ፡ ሰዎች ፡ የሰማሁት ፡ ከዋድላ ፡ እስከ ፡ ጨጨሆ የጠላት ፡ ጦር ፡ ሰፍሮ ፡ ወደበጌምድር ፡ ይገዛል ፡ ይላሉ ፡ ስለዚህ ፡ የሚመጣውን ፡ የበጌምድር ፡ ጦር ፡ በቶሎ ፡ እንዲፋጠን ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነውና ፡ ይታሰብበት ። ጥር ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

ከበደ ፡ ተሰማ ፡

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ በየሥፍራው ፡ ያሉት ፡ የአርበኞች ፡ መሪዎች ፡በየ ክፍላቸው ፡ የተሠሩትን ፡ የሥራዎች ፡ አኳኋን ፡ በመግለጽ ፡ የጻፉልኝ ፡ ደብዳቤዎች ፡ በየጊዜው ፡ ይደርሰኝ ፡ ነበር ። ከእነርሱም ፡ አንዳንዶቹ ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

ይድረስ ፡ ከክቡር ፡ ጌታዬ ፡ አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

መድኃኒ ፡ ዓለም ፡ ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ ስል ፡ እጅ ፡ እነሳለሁ ፤ ካሁን ፡ ቀደም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጽፌልዎ ፡ ነበር ፡ መድረሱንና ፡ አለመድረሱን ፡ ልኩን ፡ አላወቅሁም ፤

ልዑል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ብቸና ፡ ከገቡ ፡ ጀምረው ፡ ክቡር ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ጦራቸውን ፡ አስከትተው ፡ አፋፍ ፡ ወጥተው ፡ ከብቸናና ፡ ከአፋፍ ፡ መካከል ፡ ላይ ፡ ጦሩ ፡ በየቦሩ ፡ እየተሰለፈ ፡ ሰንብቶ ፡ ነበር ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ እንታረቅ ፡ ብለው ፡ ሽማግሌዎች ፡ እየመላለሱ፡ ላገሬው፡ ሁሉ ፡ እየሰበኩ ፡ ብዙ ፡ አርበኛ ፡ ይልቁንም ፡ አሽከሮቻቸው ፡ የነበሩት ፡ የከዳው ፡ ከዳ ፡ ያልከዳው ም ፡ ፈጽሞ ፡ ልቡ ፡ ወደርሳቸው ፡ ሆነ ፤ ክቡር ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ግን ፡ አልታረቅም ፡ ስላሉ ፡ እራስ ፡ ኃይሉ ፡ ከርሳቸው ፡ ጦር ፡ በስተቀር ፡ ካባይ ፡ ማዶ ፡ የሚቃታ ፡ ቦረና ፡ የደራ ፡ የወሎም ፡ ይባላል ፡ እየሳቡ ፡ አባይ ፡ ድረስ ፡ አስመጥተውት ፡ ነበር ። ልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለውም ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ለኢጣልያ ፡ ሆነው ፡ ከመጡብህ ፡ እንረዳሀለን ፡ ብለአቸው ፡ ሊዋጉ ፡ ተዘጋጅተው ፡ ነበር ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ የሚረዳቸው ፡ ጦር ፡ ስላጡ ፡ በዙሪያቸው ፡ ያለ ፡ ሁሉ ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ስለከ

በበን ፡ አስታራቂዎች ፡ ሽማግሌዎች ፡ ከመመላለስ ፡ አላቋረጡም ፡ነበር ፤ አልታረቅም ፡ ብለው ፡ የነበሩትን ፡ እረዳት ፡ የሚአገኝ ፡ መስሎአቸው ፡ ዛሬ ፡ ነገ ፡ ሲሉ ፡ ሰንብተው ፡ ጥር ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ የቀኃን ፡ ከሚባለው ፡ አገር ፡ ከጥቂት ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ አለንበት ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ ተገናኙ ፡ እኔም ፡ አብሬ ፡ ነበርኩ ፡ ክቡር ፡ ልጅ ፡ በላይ ዘለቀ፡ ግን ፡ እረዳት ፡ ስላጡ ፡ ለጊዜው ፡ በማታለል ፡ አገሬን ፡ ለማቆየት ፡ነው ፡ እውነተኛ ፡ እርቅ ፡ አይደለም ፡ በሽማግሌዎች ፡ በኩል ፡ አንዱ ፡ ንግግራቸው ፡ ብቻና ፡ ኢጣልያ ፡ ሲለቅ ፡ ብቻ ፡ነን ፡ ለልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ለመስጠት ፡ ነው ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ በንግግራቸውና ፡ የስዎቻቸውም ፡ ሃሳብ ፡ ብስልላቸው ፡ ኢጣልያኖች ፡ ጐጃምን ፡ ሲለቁ ፡ መሳሪያቸውን ፡ ተቀብለን ፡ እኛ ፡ ባላባቶች ፡ ጎጃምን ፡ እንገዛለን ፡ ነው ፡ የሚሉ ፤

ክቡር ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ፈረንጁ ፡ ብቻና ፡ ይልቀቅልን ፡እንጂ ፡ ለንጉሡ ፡ ነገሥታችን ፡ ነው ፡ እምንረዳ ፡ ብለው ፡ ለመኳንንቶቻቸውና ፡ ለብዙ ፡ አርበኛ ፡ ሃሳባቸውን ፡ ገልጸዋል ፤ ይልቁንም ፡ ግራዝማች ፡ አሻግሬ ፡ እናንተ ፡ ዘንድ ፡ ደርሰው ፡ ከመጡ ፡ ወዲህ ፡ አርበኞች ፡ ደስታቸው ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ሆኖዋል ።

የብቻና ፡ በጦሎኒ ፡ እንዲሽዝም ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ አራት ፡ ካሚዮን ፡ ቀርቦለት ፡ ከካምቦው ፡ ጥቂት ፡ ሳጥን ፡ ጥቂት ፡ ብረት ፡ ቡናና ፡ ጨው ፡ ለራስ ፡ ኃይሉ ፡ አስረክቦ ፡ ጥር ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ማርቆስ ፡ ዕቃውን ፡ በመኪና ፡ አድርገው ፡ ወታደሩ ፡ በእግሩ ፡ ተጓዘ ፤ ሳይነሱ ፡ አስቀድሞ ፡ የጦሩ ፡ አለቃ ፡ ጦሩን ፡ ሰብስቦ ፡ የድሮ ፡ ንጉሣችሁ ፡ መጥታለችና ፡ እስዋን ፡ ልንወጋ ፡ እንሄዳለን ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ራስ ፡ ኃይሉ ፡ በስብከት ፡ ሕዝቡን ፡ እንዳያታልሉት ፡ ነገሩ ፡ ቢፋጠን ፡ መልካም ፡ ይመስለኛል ።

ጥር ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡
ይላሉ ፡ እንግዳ ፡ መኰንን ።

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

ለጤናዎ ፡ እንደምን ፡ሰነበቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ እኔ ፡ ደህና ፡ ነኝ ። አንድ ፡ ነገር ፡ አመለክትዋለሁ ፤ ይኸውና ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ወደኔ ፡ ወረቀት ፡ ሲጽፍልኝ ፤ ከዚህም ፡ ጎጃም ፡ ቢከዳኝ ፡ በማዶም ፡ በየመልካውና ፡ በየበሩ ብከበብ ፡ ከራስ ፡ ኃይሉ ፡ ጋር ፡ ታረቅሁ ፡ ሲል ፡ ጻፈልኝ ። እኔ ፡ ማንተሙን ፡ ይገርአለሁ ፡ ጦቻም ፡ ከርሳቸው ፡ እርቅ ፡ ከሆነ ፡ ጥል ፡ ወደኔ ፡ ማሰቡ ፡ አይቀርምና ፡ በተነሳብኝ ፡ ጊዜ ፡ ወረቀት ፡ እጽፋለሁ ፤ ጦር ፡ እንዲረዳኝ ፡ ቀደም ፡ አድርገው ፡ ለዳሞት ፡



እንዲያስታውቁት ፡ እርስዎም ፡ እንዲአስቡበትና ፡ እንዲጠነቀቁበት ፡ ከዚህም ፡ ቀደም ፡ የእኔንና ፡ የራስ ፡ ኃይሉን ፡ የልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀን ፡ነገር ፡ ያውቁታል ፤ ለሁለቱም ፡ ጠበኛ ፡ መሆኔን ፡ ለኔም ፡ ካለ ፡ መንግሥት ፡ አሳቢና ፡ ዘመድ ፡ የለኝም ፡ ስለመግሪያም ፡ የመጣው ፡ ሰው ፡ በቶሎ ፡ እንዲመጣልኝ ።

ጥር ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡
ኃይሉ ፡ በለው ፡

ይድረስ ፤ ለክቡር ፡ ጌታችን ፡ አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፤ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ እያልን ፡ ለክቡርነትዎ ፡ የተገባ ፡ ሰላምታችንን ፡ እናቀርባለን ፡ ጥር ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ የተጻፈ ፡ የላኩልን ፡ ወረቀት ፡ ከዋጀ ፡ ቃል ፡ ጋር ፡ ደረሰን ፡ በዚሁም ፡ ላይ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ በጎጃም ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ መገኘታቸውን ፡ በሰማን ፡ ጊዜ ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ደስታ ፡ ፈነቃቀለን ፤እኛኑ ፡ የሚመስል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አብዝቶ ፡ ደስ፡አለው ፤ ሁለተኛ ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ መምጣታቸው ፡ የሕዝቡን ፡ ልብ ፡ ባጉል ፡ ስብከት ፡ ይከፍሉብናል ፡ አውሮፕላን ፡ መጥቶ ፡ ቦንብ ፡ ቢጥልና ፡ ሌላም ፡ የርዳታ ፡ ምልክት ፡ ቢደረግ ፡ ሕዝቡ ፡ ይጽናናል ፡ ብለን ፡ ጽፈንልዎ ፡ ነበር ፤ ሶስተኛ ፡ እራስ ፡ ኃይሉ ፡ ከልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ የጦር ፡ ሰልፍ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፤ ድሮ ፡ የጦር ፡ አርበኛ ፡ ሆኖ ፡ ለአገሩ ፡ ሲረዳ ፡ የነበረው ፡ ሕዝብ ፡ በራስ ፡ ኃይሉ ፡ ስብከት ፡ ተሰብኮ ፡ ገባ ፤ ቢገባም ፡ አብረውኝ ፡ ያሉትን ፡ አሽከሮቼን ፡ ይገፍ ፡ እዋጋለሁ ፡ ብለው ፡ ለነሴና ፡ ለጉንቻ ፡ እርዱኝ ፡ ብለው ፡ ቢጽፉ ፡ ለጊዜው ፡ መልካም ፡ ነው ፡ እንረዳለን ፡ እያሉ ፡ ሳይቀርቡላቸው ፡ ስለቀሩ ፡ ደግሞ ፡ የወሎና ፡ የደራ ፡ ባንዳ ፡ ደንቆሮ ፡ መልካ ፡ ከሚባለው ፡ እስከ ፡ ጃርሶ ፡ መልካ ፡ ድረስ ፡ ስለከበባቸው ፡ እራስ ፡ ኃይሉ ፡ እንታረቅ ፡ ቢሉ ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀም ፡ የሚታረቁበትን ፡ ሃሳብ ፡ ቢጠይቋቸው ፡ እኔ ፡ አባት ፡ እሆንሃለሁ ፤ አንተም ፡ ልጅ ፡ ሁነኝ ፡ ብለው ፡ መለሱላቸው ፡ እንግዲያወ ስ ፡ ልጅ ፡ ካደረጉኝ ፡ ከጠላት ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ የሐገርዎን ፡ ባንዲራ ፡ ከልወጉና ፡ ከኢጣልያኖች ፡ ከወጡ ፡ እቀበልዎታለሁ ፡ አሏቸው ፤ እሳቸውም ፡ ሐገሬንም ፡ አልወጋ ፡ አሳቢም ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዓይን ፡ ላይን ፡ እንገናኝ ፡ ተባብለው ፡ የርቁን ፡ ድርድር ፡ ተጻጽፈው ፡ ጥር ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ለምጨን ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ተገናኙ ።

የታረቁበትም ፡ ውሉን ፡ ወደ ፡ እርስዎ ፡ እንዲላክ ፡ አሳስበን ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ልከነዋል ፤ ውሉንም ፡ ይዩት ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ከታረቁ ፡ በኋላ ፡ የወሎ ፡ ጦር ፡ ተሻግሮ ፡ እንዳይመጣ ፡ ወንድሞቻችሁን ፡ ልከው ፡ ተዋግተው ፡ አቁመውታል ። አሁንም ፡ ሃሳባቸው ፡ የወሎ ፡ ጦር ፡ ተሻግሮ ፡ ጎጃም ፡ ላይ ፡ ረዳት ፡ እንዳይሆነው ፡ ቁርጥ ፡ ጦርነት ፡ ለማድረግ ፡ ተነስተዋል ። ሲሆን ፡ ወታደር ፡ ወደዚህ ፡ ቢረዳቸው ፡ እንኳ

ንስ ፡ በዚህ ፡ በፊታቸው ፡ በኩል ፡ ማዶም ፡ ተሻግረው ፡ ለመውጋት ፡ ያስባሉ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ እርዳታ ፡ ሁሉ ፡ በቶሎ ፡ እንዲሆንላቸውና ፡ በትጋት ፡ እንዲሠራ ፡ ይሁን ፡ ስንል ፡ እናመለክትዎታለን ።

ደግሞ ፡ ከበጌምድር ፡ የመጣ ፡ ወረቀት ፡ የልጅ ፡ የሐንስ ፡ ኢያሱ ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀና ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ የተጻፈው ፡ በሚከተለው ፡ ወረቀታችን ፡ ላይ ፡ እንልክልዎታለን ፡ በጣሙን ፡ እንዲመለከቱት ፡ ስንል ፡ ሃሳባችንን ፡ እንገልጣለን ፡ ይላሉ ፡ ታዛገሮችዎ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ።

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ እንደምን ፡ ሰንብተዋል ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ፡ የጻፉልኝ ፡ ደብዳቤ ፡ ጥር ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ደረሰኝ ፡ ማርቆስ ፡ የወደቀው ፡ ፫ ፡ በምብ ፡ አንዱ ፡ ፈነዳ ፡ ፪ኛው ፡ አድሮ ፡ በነጋው ፡ በወደቀበት ፡ ሰዓት ፡ ፈነዳ ፡ አንዱ ፡ ግን ፡ ስለአልፈነዳ ፡ ዋርድያ ፡ ነሎ ፡ ቆሞ ፡ ይጠብቀዋል ። አወዳደቁም ፡ ከካምቦው ፡ ላይ ፡ አይደለም ፡ በኳህን ፡ ሠፈር ፡ ነው ፡ በውጭ ፡ ሰውም ፡ ከብትም ፡ አልጎዳም ፡ ለወደፊቱ ፡ ቢደጋገም ፡ መልካም ፡ ነበር ፡ ለኛ ፡ ባይረዳ ፡ እንኳን ፡ ለራሱ ፡ ሲፈራ ፡ ሕዝቡ ፡ ከተማውን ፡ ቢለቀው ፡ እነሱ ፡ ምንም ፡ የሚሠሩት ፡ የለም ። ፪ኛ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ከእንግሊዝም ፡ ታርቄ ፡ አለሁ ፡ ማባ ፡ ብለው ፡ ስለጻፉላቸው ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀም ፡ ገቡ ፡ ሕዝቡም ፡ የተቃለለላቸው ፡ ይህንኑ ፡ በምስጢር ፡ ስለሰበኩት ፡ ነው ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ደሚን ፡ ሳፈስ ፡ ኑሬ ፡ እርግጡን ፡ እኛን ፡ መምሰላቸውንና ፡ ለነጻነታቸው ፡ መከራከራቸውን ፡ ከርስዎ ፡ ሳላገኝ ፡ አልከድም ፡ በማለት ፡ ተቀምጫለሁ ፡ እርሳቸውም ፡ ማባ ፡ እያሉ ፡ በየጊዜው ፡ ይልካሉ ። እርግጥ ፡ እኛን ፡ መምሰላቸው ፡ ያስታውቁኝና ፡ ሃገሬና ፡ ዘመዴ ፡ እንዳይበደል ፡ እርሳቸውን ፡ መስዬ ፡ ልቆይ ፡ የሐሰት ፡ ነገር ፡ እንደሆነ ፡ ያስታውቁኝና ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ ሆኘ ፡ በሀገራችን ፡ ላይ ፡ የሚያረገውን ፡ልኩን ፡ ላስታውቅዎ ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀም ፡ ለመገናኘት ፡ ከእንግዲህ ፡ እፈራለሁ ፡ አልከድም ፡ ይህንኑም ፡ ቃል ፡ በኛ ፡ ክፍል ፡ ካለው ፡ የጦር ፡ አርበኛ ፡ ፩ ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ መቅረቴን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ እንዲያስታውቁልኝና ፡ በየጊዜው ፡ የሚሠራውንና ፡ የጃንሆይን ፡ መቅረብ ፡ እንዲጽፉልኝ ፡ ስል ፡ በማክበር ፡ አስታውቃለሁ ፤ ፫ኛ ፡ አጋሰስ ፡ የሚገዛ ፡ ይገኛል ፤ ኪራይ ፡ ግን ፡ አይገኝም ፡ የሚገዛ ፡ ታማኝ ፡ ሰው ፡ የከብቱን ፡ ልክ ፡ የሚአውቅ ፡ ቢሰዱ ፡ ገዝቼ ፡ እሰዳለሁ ።

ጥር ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ም ፡
ልጅ ፡ አያሌው ፡ ደስታ ፡



እኔም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ራፖር ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ አስተላለፍሁ ።

ለግርማዊ ፡ ጌታዬ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ዕድሜ ፡ ከጤና ፡ አስተባብሮ ፡ ይስጥልኝ ፡ እያልኩ ፡ ባሪያዎ ፡ መሬት ፡ እስማለሁ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ፤ ወደነራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፡ የተጻፈ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ደብዳቤ ፡ በኅዳር ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ የተጻፈ ፡ በጥር ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ዛሬ ፡ ደረሰኝ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የላክሁት ፡ ሰው ፡ ተመልሶ ፡ ስለመጣና ፡ ባላምባራስ ፡ ተድላ ፡ መኰንንና ፡ ፀሐዩ ፡ እንቁ ፡ ሥላሴ ፡ በቅርብ ፡ እንሳሮ ፡ መሆናቸውን ፡ ስለሰማሁ ፡ አሥር ፡ ብረት ፡ የያዙ ፡ መልክተኞች ፡ ጨምሬ ፡ የግርማዊነትዎን ፡ አዲሱን ፡ ያዋጅ ፡ ቃል ፡ አስይዤ ፡ ላክሁ ፤ መልክተኛም ፡ ከዚህ ፡ የተነሱት ፡ በጥር ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ነው ።እኔም ፡ በደብዳቤ ፡ ላይ ፡ የግርማዊነትዎን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወስጥ ፡ መሆን ፡ እየገለጽኩ ፡ ጽፌ ፡ ሳለሁ ፤ ተድላ ፡ መኰንንና ፡ ፀሐዩን ፡ ወዲህ ፡ እንዲመጡ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፌላቸዋለሁ ። በቅርብ ፡ ቀን ፡ ይመጣሉ ፡ የማለት ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ፤ አሁን ፡ ግን ፡ የደረሰኝን ፡ ደብዳቤ ፡ ለመላክ ፡ ተዘጋጅቼ ፡ ያልተጻፈላቸውና ፡ ቅር ፡ የሚላቸው ፡ ሰዎች ፡ ስለአሉ ፤ እስቲላክልኝ ፡ እጠብቃለሁ ፤ የሚላክላቸው ም ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ማመልከቻ ፡ ከዚህ ፡ ደብዳቤዬ ፡ ጋር ፡ ይገኛል ፡ መልክተኞችንም ፡ ደርሶ ፡ ለጻፍንላቸው ፡መልስ ፡ የጻፉልንንም ፡ ደብዳቤ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ልከንዋል ፤

ወደ ፡ በጌምድርም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተጻጽፌ ፡ አጋፋሪ ፡ ያረጋል ፡ ልምጣ ፡ ብለው ፡ ጽፈውልኝ ፡ በቶሎ ፡ ይምጡ ፡ ብዬ ፡ ጽፌላቸው ፡አሁን፡ ከዚህ ፡ ሰሞን ፡ ይገባሉ ፡ በማለት ፡ ተስፋ ፡ እጠባበቃለሁ ፤ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬ ፡ መሣሪያው ፡ ስለአልደረሳቸው ፡ ገና ፡ ናቸው ፡ አልሄዱም።

ከራስ ፡ ኃይሉ ፡ መጻጻፍ ፡ ጀምሬአለሁ ፡ ለጊዜው ፡ የጻፉልኝና ፡ እኔም ፡ ጽፌላቸው ፡ የነበረውን ፡ ቃል ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ልኬአለሁ ፤ ደጃች ፡ ይመር ፡ ኅሹ ፡ ወደ ፡ ጃንሆይ ፡ ለሙምጣት ፡ ፈቃድ ፡ ለመጠየቅ ፡ የጻፉትን ፡ ደብዳቤ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ልኬአለሁ ፡ እሳቸው ፡ ግን ፡ ባንዳ ፡ ነበሩ ፡ ከጠላት ፡ የተለዩ ፡ በጥቅምት ፡ ወር ፡ አውሮፕላን ፡ መጣል ፡ ሲጀምር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚአወቅ ፡ ሰው ፡ ስለነገረኝ ፡ ታውቆ ፡ መልስ ፡ እንዲጻፍላቸው ፡ አመለክታለሁ ።

ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ብቻና ፡ ደረሰ ፡ ቀርበው ፡ ማባ ፡ ቢሉት ፡ እምቢ ፡ ብሎ ፡ ከላኩት ፡ ጦር ፡ ቃሬሩን ፡ ገጥሞ ፡ ፲፰ ፡ ብረት ፡ ማርኰ ፡ መለሰባቸው ፡ እሳቸውም ፡ ወደማርቆስ ፡ ተመልሰው ፡ ሄደው ፡

ነበር ፡ ደግሞ ፡ አሁን ፡ ወደብቸና ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ ደግሞ ፡ ከደራ ፡ ጦር ፡ ታዞ ፡ ከበው ፡ ሊወጉት ፡ ነወና ፡ ብቸና ፡ ላይ ፡ አውሮፕላን ፡ እርዳታ ፡ ይደረግልኝ ፡ ብሎ ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ጠይቋል ፡ ብለው በሱ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ያስቀመጥናቸው ፡ ሠራተኞቻችን ፡ ጽፈውልናል ። የልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀን ፡ ጦር ፡ ለማደርጀት ፡ ማርቆስና ፡ ብቸና ፡ ላይ ፡ ቦንብ ፡ እንዲጣል ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ የማርቆስና ፡ የብቸና ፡ ቦምብም ፡ መመታት ፡ ጥቅሙ ፡ ለጎጃም ፡ ጦር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለሸዋም ፡ ይሰማዋልና ፡ አጥብቆ ፡ የሚታሰብበት ፡ ነው ፤

ግርማዊነትዎ ፡ እንኳን ፡ በቅርቡ ፡ መጥተው ፤ ካርቱም ፡ ድረስ ፡ እንድመጣና ፡ የአገሩንና ፡ የአስፈላጊውን ፡ ሥራ ፡ አኳኋን ፡ ለመመካከር ፡ ጠይቄ ፡ ነበር ። እስካሁን ፡ መልስ ፡ አላገኘሁምና ፡ ምናልባት ፡ እኔ ፡ ወደዚያ ፡ ለመምጣት ፡ የማይፈቀድልኝ ፤ ቢሆን ፡ ከመምጣትዎ ፡ በፊት ፡ ሃሳቤን ፡ እንድጽፍ ፡ መልሱ ፡ እንዲጻፍልኝ ፡ እለምናለሁ ።

ጥር ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጻፈ ፡
ያለሕኪት ፡ ባሪያዎ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ፡

የሚፈጥን ፡ ማመልከቻ ።

ለግርማዊ ፡ ጌታዬ ፤

በምስራቁ ፡ ጎጃም ፡ የራስ ፡ ኃይሉ ፡ ስብከት ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ሊአበላሽብን ፡ ነወና ፡ አጥብቆ ፡ ይታሰብበት ፤ ይታሰብበትም ፡ ብዬ ፡ የማስታወቀው ፡ ብቸና ፡ ማርቆስ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ቦምብ ፡ እንዲወድቅበት ፡ ካልተደረገ ፡ በራስ ፡ ኃይሉ ፡ ስብከት ፡ ብዙው ፡ አገር ፡ ተበላሽቶ ፡ ወደሸዋም ፡ መላላኪያ ፡ መንገድ ፡ ማጣታችን ፡ ነው ። በተለይ ፡ ብርቱ ፡ ቦምብ ፡ ብዬ ፡ መጻፌ ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ ማርቆስ ፡ ላይ ፡ የረዳቶቻችን ፡ አይሮፕላን ፡ መጥቶ ፡ ጥሎ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የጣለው ፡ ቦምብ ፡ ሶስት ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ የወደቀበትም ፡ ሥፍራ ፡ እሚዳ ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ የፈነዳው ፡ ሁለት ሆኖ ፡ አንዱ ፡ ሳይፈነዳ ፡ ስለቀረ ፡ ለጠላት ፡ መስበኪያ ፡ ሆኖአልና ፡ እንደዚያ ፡ እንዳይሆን ፡ ስል ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ፡ ከምሥራቅ ፡ ጎጃም ፡ የደረሱን ፡ ደብዳቤዎች ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ልኬአቸዋለሁ ፤ ነገሩ ፡ ቀላል ፡ መስሎ ፡ አልታየኝምና ፡ ስለዚህ ፡ እየደጋገምኩ ፡ አጥብቆ ፡ እንዲታሰብበት ፡ ስል ፡ አስታውሳለሁ ፤ እኔም ፡ ማንኛውንም ፡ ሥራ ፡ መጥቼ ፡ ብማከርና ፡ ብመለስ ፡ ክፉ ፡ አልነበረም ። ነገር ፡ ግን ፡ ለማስታወሻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የመምጣቴን ፡ አኳኋን ፡ ማንሳቱ ፡ ሁሉንም ፡ በፊተኛው ፡ ማመልከቻዬ ፡ ላይ ፡ ጽፌዋለሁ ።



አሁን ፡ በዚህ ፡ ሰሞን ፡ ከቢጌምድር ፡ አርበኞች ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ መማሪያ ፡ ለመቀበል ፡ መምጣት ፡ ጀምረዋል ። ለጊዜው ፡ እነ ፡ አጋፋሪ ፡ ያረጋል ፡ እስኪመጡ ፡ እያልን ፡ አቆይተናቸዋል ።

ከምሥራቁ ፡ ጎጃም ፡ የደረሱን ፡ ደብዳቤዎች ፡ ማስታወቂያ ፤

፩/ ደብዳቤ ፡ ከልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ለኔ ፡ የተላከ ፡

፪/ ደብዳቤዎች ፡ በልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ በኩል ፡ ካሉ ፡ ሠራተኞቻችን ፡ የደረሰን ፤

፫/ ደብዳቤ ፡ የልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀና ፡ የራስ ፡ ኃይሉ ፡ እርቅ ፡ ማልባቸው ፤

፬/ ደብዳቤ ፡ ከልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ የደረሰኝ ፡ ደብዳቤ ፡

፭/ ደብዳቤ ፡ ከአዛዥ ፡ ደስታ ፡ ልጅ ፡ ከልጅ ፡ አያሌው ፡ ወደኔ ፡ የተጻፈ ፡

እነዚህ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ላይ ፡ የሚነበበው ፡ ቃል ፡ ለምሥራቁ ፡ ጎጃም ፡ ወደፊት ፡ ለሚደረገው ፡ ዋዜማ ፡ ማለት ፡ ነው ።

የካቲት ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከበላያ ፡ በመተከል ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ሲጓዙ ፡ ፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ (ራስ) ፡ በዳንግላ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ዳርና ፡ ቢጌምድር ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ መምሪያ ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀብለው ፡ ሄዱ ። ከሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ታዘው ፡ አብረው ፡ የሄዱ ፤

፩ ፤ አቶ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ (ቀኛዝማች) ፤
፪ ፤ ልጅ ፡ መንበረ ፡ ያየህ ፡ ይራድ ፤
፫ ፤ ልጅ ፡ የማነ ፡ ሐሰን ፡ (ደጃዝማች) ፡
፬ ፤ ልጅ ፡ ደበበ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ (ሜጀር ፡ ጄኔራል) ፡
፭ ፤ ቀኛዝማች ፡ አንበርብር ፡ መኩሪያ ፤
፮ ፤ አቶ ፡ አየለ ፡ ጀርመን ፤
፯ ፤ አቶ ፡ ፊጤ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፤
፰ ፤ ባሻ ፡ ገድሉ ፤
፱ ፤ አቶ ፡ እንዳሻው ፡ ካሣ ፤
፲ ፤ የአምሳ ፡ አለቃ ፡ መታፈሪያ ፡ አብዬ ፤
፲፩ ፤ » » ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፤



አቶ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ (ቀኛዝማች) ፡




ልጅ ፡ መንበረ ፡ ያየህ ፡ ይራድ ፡





ልጅ ፡ የማነ ፡ ሐሰን ፡ (ደጃዝማች) ፡



ራስ ፡ ብሩ ፡ ከበጌምድር ፡ መኳንንቶች ፡ ጋራ ፡

፲፪ ፤ » » ጃንበሩ ፡ ሙላት ፤
፲፫ ፤ » » ዓለማየሁ ፡ ኃይሉ ፤
፲፬ ፤ » » ሙሉጌታ ፡ ተገኜ ፤
፲፭ ፤ አቶ ፡ ብዙነህ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፤
፲፮ ፤ » ብዙነህ ፡ ከልክሌ ፤
፲፯ ፤ » ዘውዴ ፡ ሁነኛው ፤
፲፰ ፤ » ደጉ ፡ ዳባ ፤



ልጅ ፡ ደበበ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ (ሜጀር ፡ ጄኔራል) ፡

፲፱ ፤ ከቤገምድር ፡ መሣሪያ ፡ ለማንሳት ፡ ከነ ፡ አዛዥ ፡ ቦጋለ ፡ ገብረ ፡ ወልድና ፡ ከነቀኛዝማች ፡ አባተ ፡ ደረሰ ፡ ጋራ ፡ የመጡትንና ፡ እንደ



ዚሁም ፡ ለየብቻቸው ፡ የመጡት ፡ ሁሉ ፡ መሣሪያው ፡ እየተሰጣቸው ፡ ከእሳቸው ፡ ጋራ ፡ እንዲሄዱ ፡ ተደርጎ ፡ አብረው ፡ ሄደዋል ።

የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ መኰንኖችም ፡ ከጥቂት ፡ የሱዳን ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ አብረው ፡ እንዲሄዱ ፡ ተደርጓል ፤ ስማቸውም ፤

፩ ፤ ሜጀር ፡ ወልስ ፤ ፪ ፤ ካፒቴን ፡ ማይክል ፤
፫ ፤ ሳርጀንት ፡ ሞሮ ፡ ፬ ፤ ሳርጀንት ፡ ዶየልድ ፡ የሚባሉ ፡ ናቸው ።

ለጊዜው ፡ ስማቸውን ፡ ያላወቅሁት ፡ የሱዳን ፡ ተወላጅ ፡ መኰንኖችም ፡ ከወታደሩ ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ።



አዛዥ ፡ ቦጋለ ፡ ገብረ ፡ ወልድ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

# ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የተላኩልኝ ፡ የሥራ ፡ መምሪያ ፡ ደብዳቤዎችና ፡ ትእዛዞች ።

በየካቲት ፡ ወር ፡ መጀመሪያ ፡ ሳምንት ፡ ላይ ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የተላኩልኝ ፡ ደብዳቤዎችና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ትእዛዞች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፉት ፡ ናቸው ።

የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ፡

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ፡ ከአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና ፡ ነን ። በታኅሣሥ ፡ ፳፮ ፡ እና ፡ በጥር ፡ ፲፱ ፡ የተጻፉ ፡ ደብዳቤዎችህ ፡ አብረው ፡ ከተላኩት ፡ ከሌሎች ፡ ደብዳቤዎች ፡ ጋራ ፡ ደረሱን ። እኛም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ በታሰበው ፡ ቦታ ፡ ደርሰናል ። እኛ ፡ ስንመጣ ፡ ለየአገሩ ፡ ከአዋጅ ፡ ጋራ ፡ የላክነው ፡ ማስታወቂያ ፡ መልካም ፡ ነው ። ደብዳቤም ፡ ለላኩት ፡ ሹማምንቶችና ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ምላሹን ፡ ልከንልሀልና ፡ እንዲደርሳቸው ፡ አድርግ ።

በቤጌምድር ፡ በኩል ፡ ስለተደረገው ፡ በማመልከቻህ ፡ ስለጻፍከው ፡ ጦርነት ፡ አርበኞቻችን ፡ መጠንከራቸውን ፡ ስለሰማን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ። ስለምርኮኞቹ ፡ ኢጣልያኖች ፡ በተያዙ ፡ ቁጥር ፡ አጥብቆ ፡ መጠበቅና ፡ የተቻለ ፡ ያህል ፡ ቁጥራቸውን ፡ ማብዛት ፡ የሚጠቅም ፡ ነውና ፡ ከአርበኞቻችን ፡ ለቀረበው ፡ በቃል ፡ ለራቀው ፡ በማስታወሻ ፡ ማስጠንቀቅ ፡ ነው ። ኢጣልያኖች ፡ እንዲመልሱ ፡ ለሚጠየቁት ፡ ነገር ፡ መለወጫ ፡ የሚሆኑ ፡ የኢጣልያ ፡ ምርኮኞች ፡ ብዙ ፡ በእጃችን ፡ የተገኙ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

ጠላት ፡ በሐሰት ፡ የእኛን ፡ ፎቶግራፍ ፡ አስመስሎ ፡ ስላወጣው ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ሥዕል ፡ አድርጎ ፡ የሠራው ፡ በመሆኑ ፡ ሐሰተኛነቱ ፡ ለማንም ፡ ቢሆን ፡ በግልጥ ፡ የሚታይ ፡ ነውና ፡ እያቀለለው ፡



የሚሄድ ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ። በእኛ ፡ ማኅተም ፡ አስመስሎ ፡ ያወጣው ም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። ስለሌላው ፡ ጉዳይ ፡ በማስታወሻ ፡ በተለይ ፡ ተልኮልሃል ።

የካቲት ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጻፈ ፡

ማስታወሻ ፡

ለአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

መቼም ፡ እንደምታውቀው ፡ ስንቅ ፡ ካልተሰናዳ ፡ ወታደር ፡ ማግኘት ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ መሥራት ፡ አይገኝም ። እንደ ፡ ድሮው ፡ ከአገር ፡ ዘርፎ ፡ መብላት ፡ ሁለት ፡ ጠላት ፡ በማምባር ፡ ማስቀመጥ ፡ መሆኑ የታወቀ ፡ ነው ፡ በእኛ ፡ ተስፋ ፡ እስካሁን ፡ ብዙ ፡ እህል ፡ ተሸምቶ ፡ ዱቄት ፡ የሚቆይ ፡ መስሎን ፡ ነበር ፡ ይህም ፡ ሳይሆን ፡ የቀረው ፡ በእናንተ ፡ አለመትጋት ፡ አለመሆኑን ፡ በገንዘብ ፡ ተቸግራችሁ ፡ እንደነበረ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡ አስረዳኝ ፡ አሁን ፡ የገንዘብ ፡ ችግር ፡ እንዳይባል ፡ ገንዘቡ ፡ መጥቷል ፡ በአንድ ፡ ወገንም ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ከአገር ፡ ላይ ፡ ለማስወጣት ፡ የቀረጠ ፡ መሆኑን ፡ ሰማሁ ። ለማድረግ ፡ የሚችል ፡ ከሆነ ፡ እህሉን ፡ ሲያስገዛ ፡ ስለ ፡ እህሉ ፡ ዋጋ ፡ ፋንታ ፡ እህሉን ፡ የሚያመጣው ፡ እየፈጨ ፡ ያምጣና ፡ የፈጨበትን ፡ ይቀበል ፡ ይህንንም ፡ ብቻ ፡ ተስፋ ፡ ከማድረግ ፡ በእናንተ ፡ በኩል ፡ መሸመትንም ፡ ማስፈጨትንም ፡ አለመተው ፡ ነው ፡ ማርም ፡ በብዙ ፡ እንኳ ፡ ባይሆን ፡ ለብርዝ ፡ እንዲገባ ፡ ማድረግ ፡ ነው ፡ ይህንንም ፡ ሥራ ፡ ለማከናወን ፡ ለአንተ ፡ ሥራ ፡ ስለሚበዛብህ ፡ ረዳት ፡ የሚሆኑህ ፡ ሰዎች ፡ ግራዝማች ፡ አበበ ፡ አስረስንና ፡ አዛዥ ፡ ሙሉሰውን ፡ ልኬልሃለሁ ።

ሁለተኛ ፡ ስለእንሰሳና ፡ ስለኩርቻ ፡ ከብት ፡ ወደ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻና ፡ ወደ ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ይኸው ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፈናልና ፡ ኩርቻ ፡ ቢገኝ ፡ ከነኩርቻና ፡ መደላድል ፡ ይህም ፡ ባይገኝ ፡ ጫኝውንና ፡ በቅሎውን ፡ አሰናድተው ፡ በቶሎ ፡ እንዲልኩ ፡ አትጋቸው ። የጦር ፡ ጊዜ ፡ ትእዛዝ ፡ በነገ ፡ ሰልስት ፡ የሚቆይ ፡ አለመሆኑን ፡ ታውቀዋለህ ።

ሶስተኛ ፡ ሁነኛ ፡ መላክተኛ ፡ አሁን ፡ እንደጀመርከው ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ ልከህ ፡ እነ ፡ አጋፋሪ ፡ ያረጋልና ፡ እነ ፡ ነገደ ፡ ዘገዬ ፡ ቆለጭ ፡ እነርሱንም ፡ የመሰሉት ፡ ሲመጡ ፡ ብረት ፡ አንስተው ፡ ስልፍ ፡ የሚያስተምራቸው ፡ ሰው ፡ ተደርጎ ፡ ለእኔ ፡ ዘበኛ ፡ እንዲሆኑ ፡ አውቀው ት ፡ እንዲመጡ ፡ የታመነ ፡ ሰው ፡ አገሥግሠህ ፡ ላክ ፡ ቀለቡም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ መሣሪያውም ፡ ጥሩ ፡ የሆነ ፡ ይዘውላችሁ ፡ መጥተዋል ፡ እያልክ ፡ ግለጽላቸው ።

የካቲት ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

## የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ፡፡

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡
ይድረስ ፡ ከአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

እንደምን ፡ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና ፡ ነን ፡ በጥር ፡ ፳፱ና ፡ በየካቲት ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ የጻፍካቸው ፡ ደብዳቤዎች ፡ ደረሱኝ ፡፡


ደጃዝማች ፡ ፀሐዩ ፡


ጀኔራል ፡ ተድላ ፡ መኰንን ፡፡

በጥር ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ከጻፍከው ፡ ጋራ ፡ ከሸዋ ፡ የመጡት ፡ ደብዳቤዎች ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አሰኙን ፡ የራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፡ ደብዳቤ ፡ ብቻ ፡ ሳይደርሰን ፡ በመቅረቱ ፡ ለልባችን ፡ እንቅፋት ፡ ሳይሆን ፡ አልቀረም ፤ ተድላ ፡



መኰንንና ፡ ፀሐዩ ፡ እንዲመጡ ፡ በማድረግህ ፡ መልካም ፡ ሃሳብ ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ እንዳስታወስከው ፡ ወደነርሱ ፡ የሚላከውን ፡ ደብዳቤ ፡ ልክንልሀል ፤ አሁን ፡ እኛው ፡ ራሳችን ፡ ወደዚያው ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ በቶሎ ፡ ለመምጣት ፡ ስላሰብን ፡ ወደዚህ ፡ እንዳንጠራህ ፡ ያደረግነው ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡፡ በመጣልህ ፡ ደብዳቤ ፡ ላይ ፡ እንዳየነው ፡ የባላምባራስ ፡ ተድላ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ተልኮ ፡ ሌላው ፡ ቀርቷልና ፡ አሁን ፡ በቶሎ ፡ እንድትልክልን ፤ ለወደፊቱ ፡ ከበጌምድርም ፡ ከጥግ ፡ ከላስታም ፡ ምናልባት ፡ እኛ ፡ ሳንደርስ ፡ መላክተኛ ፡ የመጣ ፡ እንደሆነ ፡ ይልቁንም ፡ የምናውቃቸው ፡ ሰዎች ፡ ስታገኝ ፡ ሰው ፡ ይዘው ፡ እንዲመጡ ፡ መጻፍህን ፡ አታቋርጥ ፤ ለራስ ፡ ኃይሉ ፡ የጻፍክላቸውንና ፡ የመለሱልህንም ፡ አየነው ፡ ይልቁንም ፡ ቀጥሎ ፡ ከበላይ ፡ ዘለቀ ፡ ጋራ ፡ ያደረጉት ፡ የርቅ ፡ ድርድር ፡ ያንኑ ፡ የጻፉልህን ፡ ቃላቸውን ፡ የሚያጸና ፡ ይመስላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ተስፋ ፡ ለመቁረጥና ፡ ፈጽሞ ፡ ለማስጨረስ ፡ የተጻፈላቸውን ፡ የእኛን ፡ ደብዳቤ ፡ ልክንልሀልና ፡ ላክላቸው ፤ እስካሁን ፡ በተደከመበት ፡ በጎጃም ፡ ላይ ፡ የራስ ፡ ኃይሉ ፡ ሰብከት ፡ ጉዳይ ፡ ይሠራል ፡ ብለን ፡ አንሰጋበትም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ስብከታቸው ፡ ኃይል ፡ የሚያገኘው ፡ በባንዳ ፡ እያስፈራሩ ፡ ከሆነ ፡ የእኛም ፡ ሰው ፡ መሣሪያና ፡ የአውሮፕላን ፡ እርዳታ ፡ ከጎደለው ፡ ሳይወድ ፡ በግድ ፡ ባፉ ፡ ማመኑ ፡ የማይቀር ፡ ነው ፤ አሁን ፡ ከራስ ፡ ኃይሉ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ መገናኘቱን ፡ የጻፍክልንን ፡ ጠቅሰን ፡ ለጠቅላይ ፡ ገኔራል ፡ብርቱ፡ ቃል ፡ በራዲዮ ፡ አሳልፈናል ፤ በራዲዮም ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ያለፈውን ፡ አንተ ፡ የጻፍከውን ፡ የሚያረጋግጠውን ፡ ቃል ፡ አየሁት ፤ አንተ ፡ ከእኛ ፡ እንድትገናኝ ፡ የምንቸኩለው ፡ እኛ ፡ ነን ፤ በየጊዜው ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ከዚያ ፡ የምትልከው ፡ ይበልጣል ፡ ብለን ፡ አስበን ፡ ነውና ፡ ሳታቋርጥ ፡ ጻፍልን ፤ እንደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ እንደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ከሁሉቱ ፡ ዘንድ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ በቅሎዎች ፡ እንልካለን ፡ ላሉት ፡ ወደ ፡ ሔድኳርተር ፡ያሳለፍከውን ፡ ቴሌግራም ፡ አየነው ፤ ለአንድ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ በርግጥ ፡ የሚገኝ ፡ ከሆነ ፡ ደህና ፡ ተስፋ ፡ የሚሰጥ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ባንዳ ፡ ሆነው ፡ ከወጡት ፡ አጠገብህ ፡ ካሉት ፡ ሰዎች ፡ እርድ ፡ ውስጥ ፡ ካሉት ፡ ተላልኮ ፡ የሚያስከዳ ፡ ሰው ፡ቢገኝ ፡ አሁን ፡ የእኛን ፡ መምጣት ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ የማስከዳትና ፡ የሚነባበሉን ፡ ሥራ ፡ አለማቋረጥ ፡ ነው ፤ ሲወጣ ፡ ባላገር፡ ስለሚገፈው ፡ በእርግጥ ፡ ለመውጣት ፡ ቃሉን ፡ በሰጠበት ፡ ቦታ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ከራሱ ፡ ከሚያምናቸው ፡ ዘበኞች ፡ ተቀባይ ፡ ሁነኛ ፡ ጨምሮ ፡ እንዲሰድ ፡ መነጋገር ፡ ነ ፤ ይኸውና ፡ አሁን ፡ ለራስ ፡ ኃይሉ ፡ ስብከት ፡ መቃወሚያ ፡ በአውሮፕላን ፡ የሚጣለው ፡ አዋጅ ፡ ግልባጩን ፡ ልክንልሀልና ፡ ታትሞ ፡ በአውሮፕላን ፡ እስኪጣል ፡ ድረስ ፡ እዚያ ፡ባለው፡ መግለጫ ፡ እንጊታሁን ፡ ተሰማ ፡ በብዙ ፡ ላይ ፡ ጽፈው ፡ ለዋና ፡ ለዋና ፡ ቦታ ፡ አድርሰው ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ሸዋም ፡ ወደ ፡ ጎጃምም ፡ በሚቻልህ ፡ ቦታ ፡ እያፋጠንህ ፡ የምትልከው ፡ ባንዲራችን ፡ የሚለውን ፡ ማስታወ

ቂያ ፡ ልክንልህል  እዚህ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ ካለው ፡ ከእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ተከታዮችን ፡ ከሆነው ፡ እንደተነጋገርነው ፡ በታመነ ፡ መላክተ ኛዎ ፡ በኩል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ሰፈር ፡ አድርገው ፡ የሚኖሩበት ፡ ቦታ ፡ በግልጥ ፡ የታወቀ ፡ እንደሆነ ፡ አንድ ፡ የታመነ ፡ ሰው ፡ ምልክት ፡ እንዲ ሰጥ ፡ ተደርጎ ፡ በቦምብ ፡ ለማስመታት ፡ ይቻላል ፡ ተብሎ ፡ ታስቢልና ፡ ከአሁን ፡ ጀምሮህ ፡ አስበህበት ፡ ደብዳቢያችን ፡ ከደረሳችው ፡ በኋላ ፡ አገር ፡ ለመበደል ፡ የሕዝባችንን ፡ ነጻነት ፡ ለማጥፋት ፡ አሁን ፡ በሚሠ ሩት ፡ ሥራ ፡ የጸኑ ፡ እንደሆነ ፡ ይህን ፡ አሳብ ፡ እንድንከታተልና ፡ እንድ ንፈጽመው ፡ ካሁን ፡ ጀምሮህ ፡ እንድትሰናዳ ፡ ነው ።

የካቲት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጻፈ ፡

እኔም ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ የሥራ ፡ መግለጫ ፡ራፖር ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ላክሁ ፡

## ማመልከቻ ።

በግርማዊነትዎ ፡ ግንባር ፡ ኃያም ፡ ያለው ፡ ምሽግ ፡ ሁሉ ፡ ሲለቀቅ ፡ አቅቶ ፡ ሳይደፈር ፡ የቀረውን ፡ የዳንግላን ፡ ምሽግ ፡ የካቲት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ አር በኞችዎ ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ስለያዙ ፡ ደስ ፡ ስላለን ፡ ለየክፍሉ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ለጊዜው ፡ ማስታወቂያ ፡ ያወጣነውን ፡ ቃል ፡ ግርማዊነትዎ ፡ እንዲመለከቱት ፡ ልኬዋለሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ በመጀመሪያው ፡ላይ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ድል ፡ ከተገኘ ፡ ሌላው ፡ ሥፍራ ፡ ሁሉ ፡ በቶሎ ፡ ይጠ ቃል ፡ የማለት ፡ ታላቅ ፡ ተስፋ ፡ አለን ፡ እየደጋገምኩ ፡ የማስታውሰው ፡ ግን ፡ ብቻናና ፡ ምጣ ፡ ማርቆስ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረገው ፡ ቦምብ ፡ ነው ።

የካቲት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጻፈ ፡
ያለሐኬት ፡ ባሪያዎ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

ለግርማዊ ፡ ጌታዬ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ዕድሜ ፡ ከጤና ፡ አስተባብሮ ፡ ይስጥልኝ ፡ እያ ልኩ ፡ ባሪያዎ ፡ መሬት ፡ እስማለሁ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ፡ በበጌምድር ፡ አውራጃ ፡ ያሉ ፡ አርበኞች ፡ ያመነ ታሉ ፡ አላመኑም ፡ ማለትን ፡ ስለሰማሁ ፡ ግራዝማች ፡ አባተን ፡ ፲፯ ፡ጠመ ንጃ ፡ ያህል ፡ አስይዤ ፡ ስለላክኋቸው ፡ የቢጌምድር ፡ አርበኛ ፡ ልቡ ፡ ረግ ቷል ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ጦር ፡ ዙሪያውን ፡ አካቦት ፡ ከዚህ ፡ የሚመለሰውን ፡ የጦር ፡ መሳሪያ ፡ እስኪደርሰው ፡ ነው ፡ የሚጠብቀው ፡ አገሩ ፡ ጦር ፡ ለማ



ድረግና ፡ በቶሎ ፡ እያገኘ ፡ እንዲመለስ ፡ ብለው ፡ ምክር ፡ ስለአቀረቡልኝ ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ተገናኝተው ፡ ከተነጋገሩ ፡ በኋላ ፡ በቶሎ ፡ ተመልሰው ፡ እንዲሠሩ ፡ ቢሆን ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ስል ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ አመለክ ታለሁ ።

የካቲት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
ያለሐኬት ፡ ባሪያዎ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የምጽፈውም ፡ በየካቲት ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ለማሕል ፡ ጎጃም ፡ ሕዝብና ፡ ለአርበኞች ፡ በአውሮፕላን ፡ የተበተነውን ፡ የግርማዊ ፡ ጃንሆይን ፡ የአዋጅ ፡ ቃል ፡ ነው ።

## አንበሳ ፡

አዋጅ ፡

የማሐል ፡ ጎጃም ፡ ሕዝብ ።

ስማ ።

የእንግሊዝን ፡ መንግሥት ፡ እርዳታ ፡ ይዤ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ወደ ፡ አገሬ ፡ መመለሴን ፡ አስታወቅሀለሁ ። ላገራቸው ፡ ነጻ ነት ፡ ለንጉሣቸው ፡ ክብር ፡ ብለው ፡ ሳያቋርጡ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ከተ ዋጉት ፡ አርበኞቼ ፡ መርጬ ፡ መጀመሪያ ፡ ገብቼ ፡ የነጻነት ፡ ባንዲራች ንን ፡ የተከልኩበት ፡ አገር ፡ ጎጃም ፡ ነው ፤ ስትቸገር ፡ ስትሰቃይ ፡ ያልረ ሩልህ ፡ ያላዘኑልህ ፡ አሁን ፡ መምጣቴን ፡ ሰምተው ፡ አንድነትህን ፡ ጠብ ቀህ ፡ ነጻነትህንና ፡ ሰላም ፡ የምታገኝበት ፡ ሰዓት ፡ በፊትህ ፡ ስለቀረበ ፡ ይህን ፡ እድል ፡ ለማሳጣት ፡ የጠላታችን ፡ የኢጣልያ ፡ መግሪያ ፡ የሆኑት ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ ወገንህ ፡ መስለው ፡ በመካከልህ ፡ እንደ ፡ ተኩላ ፡ ገብተዋል ። የተበደልክበትን ፡ ምክንያት ፡ ሁሉ ፡ አትርሳ ። የፈረንጅ ፡ መልክ ፡ አላሳይህም ፡ ከእንግሊዝም ፡ ታርቄአለሁ ፡ ብለው ፡ የሚሰብ ኩህ ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ እርሳቸው ፡ ስልክ ፤ ተናጋሪው ፡ ግን ፡ ኢጣልያኖች ፡ መሆናቸውን ፡ ብትረሳ ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ መታለልህ ፡ ነው ። ራስ ፡ ኃይሉስ ፡ ቢሆን ፡ ጎጃምን ፡ ለመግዛት ፡ የበቁት ፡ በእኛ ፡ ጊዜ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ኢጣሊያኖችማ ፡ ከገቡ ፡ የቁም ፡ እሥር ፤ የድንጋይ ፡ ጦር ፡ አድ ርገው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ላይ ፡ ሲጫወቱባቸው ፡ አልነበሩምን? ላም ፡ በን ፍላ ፡ እንደምትታለብ ፡ ራስ ፡ ኃይሉን ፡ በፊት ፡ እያስቀደመ ፡ የተንኰል ፡ ወጥመዱን ፡ በሚዘራው ፡ በጠላታችን ፡ በኢጣልያን ፡ እጅ ፡ እንደገና ፡ እንዳትወድቁ ፡ አደራ ፡ እላችኋለሁ ። ስለኢጣልያኖች ፡ ወይም ፡ ለነርሱ ፡ መግሪያ ፡ ከሚሆኑት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ጠላት ፡ እንደሌለን ፡ እወቅ ፤

ኢጣልያኖች ፡ በአልባኒያ ፡ በሊቢያ ፤ በኤርትራ ፤ በኢትዮጵያም ፡ በየክፍሉ ፡ ጦራቸው ፡ ድል ፡ እየሆነ ፡ ስለተበተነ ፡ ራሳቸው ፡ የሮባቸው ፡

መጥፋታችን ፡ ከሆነ ፡ ይህም ፡ ሕዝብ ፡ አብሮ ፡ ይጥፋ ፡ በማለት ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ ለማፋጀት ፡ የወጠኑት ፡ ሃሳብ ፡ ነውና ፡ ተጠንቀቅ ፤ በያለህ በት ፡ እርጋ ፡ እኔም ፡ ራሴ ፡ ከትብብርህ ፡ ጋር ፡ ፍርድና ፡ ሰላም ፡ ይገሬ ፡ ደርሻለሁ ።

የካቲት ፡ ፲፱ ፡

## አንበሳ ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ።
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡
የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ሆይ ፤

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሁከት ፡ ስለተነሳ ፡ የእንግሊዝ ፡ ወታደሮችም ፡ በሱዳን ፡ በኩል ፡ ስለተጫኑአቸው ፡ ጣሊያኖች ፡ ወሰኑን ፡ መልቀቅ ፡ ሆኖባቸዋል ።

የእንግሊዝ ፡ ወታደርም ፡ ይከታተላቸዋል ። እስከ ፡ ዛሬም ፡ ከሰላን ፡ ሰብደራትን ፡ ተሰኔን ፡ ይዞባቸዋል ።

በግራዚያኒ ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ አሳፋሪ ፡ ድል ፡ ኢጣሊያኖችን ፡ራሳቸውን ፡ አዞሮታል ። ግራዚያኒ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በሊቢያ ፡ ታላቁን ፡ ምሽግ ፡ ባርዲያን ፡ ለእንግሊዞች ፡ አስረክቦአል ። ዘጠና ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ የጣሊያን ፡ ወታደር ፡ ተማርኮአል ፡ ወይም ፡ ሞቶአል ። ከነዚህም ፡ውስጥ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ጄኔራሎች ፡ አሉባቸው ። ካምስት ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡በላይ ፡ መድፍ ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ በላይ ፡ ታንክ ፡ ተማርኮአል ፡ የኢጣልያኖች ፡ ዋና ፡ ተስፋ ፡ ግራዚያኒ ፡ ስንቅና ፡ መጣሪያ ፡ የሚያገኝበትን ፡ ዋናውን ፡ በሩን ፡ ቶብሩክ ፡ የተባለውን ፡ የወደብ ፡ ከተማ ፡ እንግሊዞች ፡ እንዲይዙት ፡ ለቆት ፡ ወደ ፡ ትሪፖሊ ፡ ይሸሻል ።

ከጥቂት ፡ ጊዜም ፡ በኋላ ፡ ግራዚያኒ ፡ ድል ፡ ያደረገው ፡ የእንግሊዝ ፡ ወታደር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ጣሊያን ፡ ድምጥማጡን ፡ ያጠፋዋል ። ስለዚህ ፡ እየወጣችሁ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ወታደር ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ ከኛ ፡ ታማኞች ፡ ጋራ ፡ ተቀላቀሉ ። እነዚህም ፡ በወንድምነት ፡ ይቀበሉአችኋል ። ወይም ፡ ወደየቤታችሁ ፡ ተመልሳችሁ ፡ ሚስቶቻችሁን ፤ ልጆቻችሁን ፡ ርስታችሁንም ፡ ጠብቁ ። እኔ ፡ ራሴ ፡ አገር ፡ ለማረጋጋት ፡ሕግና መልካም ፡ አስተዳደር ፡ ለማቆም ፡ መጥቻለሁ ።

የካቲት ፡ ፲፱ ፡



## አንበሳ ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡

ሱዳን ፡ ያለው ፡ የእንግሊዝ ፡ ወታደር ፡ ስለሚከታተለውና ፡ ግራዚያኒም ፡ በሊቢያ ፡ ድል ፡ በመሆኑ ፡ ስለተሸበረ ፡ ጣሊያን ፡ በኤርትራ ፡ ወሰን ፡ ዳር ፡ ያለውን ፡ ወታደሩን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መመለስ ፡ ጀምሮአል ። በሊቢያ ፡ ድል ፡ ያደረገው ፡ የእንግሊዝ ፡ ወታደር ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ ደፍሮ ፡ መጠበቅ ፡ አቃተው ።

ለጎጃም ፡ አውራጃ ፡ ሕዝቤ ፡ ጣሊያን ፡ ሥቃይ ፡ ሊያጸናበት ፡ መሞከሩን ፡ እሰማለሁ ። ባንዳ ፡ የሚለውን ፡ በገንዘብ ፡ ያባበለውን ፡ ወታደር ፡ አገር ፡ እንዲዘርፍ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲያቃጥል ፡ ይነዳዋል ።

ጣሊያኖች ፡ በሚወጡበት ፡ ጊዜና ፡ እኔም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሰላምና ፡ መልካም ፡ አስተዳደር ፡ በሚቋቋምበት ፡ ጊዜ ፡ መካከል ፡ሁከት ፡ እንዳይሆን ፡ ባንዳ ፡ የሆንክ ፡ የጣሊያ ፡ መጣሪያ ፡ ሆነህ ፡ ባገርህ ፡ ነጻነትና ፡ በገዛ ፡ ወንድምህ ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሥራ ፡ አትሥራ ።

የጎጃም ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፤ ተባበር ፤ ተፋቀር ፤ ጣሊያን ፡ ለራሱ ፡ጥቅም ፡ ሲል ፡ በመካከልህ ፡ መለያየትን ፡ እንዳይነዛ ፡ ተጠንቀቅ ፤ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ድር ፡ ቢያብር ፡ አንበሳ ፡ ያሥር ፡ ያልነህን ፡ አትዘንጋ ።

ኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ሆነው ፡ ስለመምጣታቸው ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የምጽፈው ፡ ኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ በኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ምትክ ፡ ስለመምጣታቸውና ፡ እንዲሁም ፡ ሌፍትናንት ፡ ፊሎ ፡ ለሥራ ፡ በኛ ፡ በኩል ፡ ስለመታዘዛቸው ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተጻፈልኝን ፡ ትእዛዞች ፡ ነው ።

### የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡
ይድረስ ፡ ከአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና ፡ ነን ። የወዳጃችን ፡ የባለቃል ፡ ኪዳኖችን ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡

የጦር ፡ አለቃ ፡ በጎጃም ፡ ለጦራችን ፡ በምክርም ፡ በሥራም ፡ እንዲረዱ ፡ አስቀድሞ ፡ ተልከው ፡ የነበሩት ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ በእኛ ፡ አጠገብ ፡ ሆነው ፡ እንዲሠሩ ፡ ስለተቆረጠ ፡ በርሳቸው ፡ ምትክ ፡ ኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ መጥተዋልና ፡ ከጦር ፡ አለቅነታቸው ፡ በቀር ፡ ለእኛም ፡ ለኢትዮጵያም ፡ ወዳጅ ፡ ስለሆኑ ፡ በተቻለህ ፡ ሁሉ ፡ እየረዳሃቸው ፡ አብረህ ፡ እንድትሠራ ፡ ይሁን ።

የካቲት ፡ ፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡



ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ከኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ ጋራ ፡ የጦር ፡ ጥላን ፡ ሲያዩ ።

ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ ከደረሰኝ ፡ በኋላ ፡ ተኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ ጋር ፡ተገናኝተን ፡ ስለሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ስንነጋገር ፡ ከእርሳቸው ፡ ያገኘሁት ፡ ያሠራር ፡ ዘዴ ፡ አመራር ፡ ተኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ሃሳብ ፡ በጣም ፡ የተራራቀ ፡ ነበር ።

የተራራቀ ፡ ነበር ፡ የምለውም ፡ የኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ድካምና ፡ ተጋድሎአቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቢሆንም ፡ ሥራቸው ፡ ጥርት ፡ ያለ ፡ ሳይሆን ፡ በፖለቲካ ፡ የተሸፈነ ፡ ነበር ። ኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ ግን ፡ ጠላት ፡ የሚጠቃበትንና ፡ ድል ፡ የሚሆንበትን ፡ ብቻ ፡ ማሰብ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ የፖለ



ቲካ ፡ ጉዳይ ፡ በእሳቸው ፡ ዘንድ ፡ አይታይም ፡ ነበር ። ተኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ ጋር ፡ ከተገናኘን ፡ በኋላ ፡ የተሰማራንበትን ፡ የሥራ ፡ አካሄድ ፡ በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ እገልጠዋለሁ ።

ስለ ፡ ሌፍትናንት ፡ ፊሉ ፡ የተጻፈልኝም ፡ ትእዛዝ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡
ይድረስ ፡ ከአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

እንደምን ፡ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና ፡ ነን ፤ ሌፍትናንት ፡ ፊሎ ፡ ወደ ፡ ጎጃም ፡ የመጣው ፡ በጠላታችን ፡ ላይ ፡ የፕሮፓጋንዳ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ ፈቅደንለት ፡ ነውና ፡ ሥራው ፡ እንዲቃናለት ፡ በተቻለህ ፡ ሁሉ ፡ እንድትረዳው ፡ ይሁን ፤ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡ ከዚህ ፡ቀደም ፡ በዚህ ፡ ሥራ ፡ ይደክምበት ፡ ስለነበረ ፡ ከሌላው ፡ ሥራው ፡ በሚተርፈው ፡ ጊዜው ፡ አሳብ ፡ በመስጠት ፡ ሊረዳው ፡ ይችላል ።

የካቲት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጻፈ ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተላከልኝ ፡ ነው ።

የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡
ይድረስ ፡ ከአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና፡ ነን ።

የካቲት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ የተጻፈ ፡ ደብዳቤህ ፡ አብረው ፡ ከተላኩት ፡ ከበጌምድር ፡ ከመጡት ፡ ደብዳቤዎች ፡ ጋር ፡ ደርሰውናል ፤ ወደዚህ ፡ ስለመድረሳችን ፡ የገለጥህልን ፡ ደስታ ፡ ልብህን ፡ የምናውቀው ፡ ስለሆነ ፡ በበለጠ ፡ እንገምተዋለን ፤ እንኳን ፡ ሁላችንም ፡ ደስ ፡ ያለን ፤ ለፍጻሜውም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ላደረገው ፡ ቸርነት ፡ በሰጠን ፡ አእምሮና ፡ ኃይል ፡ በመሥራት ፡ ሁላችንም ፡ መርዳት ፡ አለብን ።

ስለሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ወደዚህ ፡ እንድትመጣ ፡ ስለጠየቅህ ፡ ባለፈው ፡ በጻፍንልህ ፡ ደብዳቤ ፡ እኛው ፡ ራሳችን ፡ መቃረባችን ፡ ስለሆነ ፡ እንገናኛለን ፡ በማለት ፡ መቆየትህ ፡ የሚጠቅምህ ፡ መሆኑን ፡ ጽፈንልሃል ። ይልቁንም ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ በኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ምትክ ፡ ምንም ፡ ወዳጃችን ፡ ቢሆን ፡ ከሰው ፡ ገና ፡ ያልተላመደ ፡ አዲስ ፡ ሰው ፡ ኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ ለሥራ ፡ ወደዚያ ፡ ስለመጣ ፡ የአንተን ፡ እርዳታ ፡ በብዙ ፡ የሚያስፈልገው ፡ በመሆኑ ፡ አብረህ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ በዚያው ፡ መገኘትህ ፡ የበለጠ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ታይቶናል ፤ ከደጃዝማች ፡ መንገሻና ፡ ከደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ለማገናኘት ፡ የሥራውን ፡ ፕላን ፡ አውቀኸው ፡ እስኪደቀን ፡ ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እኛ ፡ ተዚህ ፡ ሆነን ፡ በምንገምተው ፡ ዓይነት ፡ በዚያ ፡ መቆየትህ ፡ ጠቃሚነቱ ፡ ስለታየን ፡ ነውና ፡ አንተ ፡ በዚያ ፡ ሆነህ ፡ እንደምታስበው ፡ መጥተህ ፡ ተነጋግረህ ፡ በቶሎ ፡ ብትመለስ ፡ የሚበልጥ ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ሥራ ፡ የማይሰናከል ፡ መሆኑን ፡ ከተረዳኸው ፡ እንድትመጣ ፡ ፈቃዳችን ፡ ነው ።

ስለ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ የጻፍከውን ፡ ተመልክተነዋል ፡ ይህ ፡ የዛሬው ፡ ወረቀትህ ፡ ሳይደርስ ፡ ከላክንልህ ፡ ደብዳቤ ፡ አሳብ ፡ በቀር ፡ ለጊዜው ፡ የተሻለ ፡ የሚገኝ ፡ አልሆነም ። ይህም ፡ መልካም ፡ ፍጻሜ ፡ ባይሰጥ ፡ ደግሞ ፡ እየቀረብን ፡ የተሻለ ፡ ይታሰብበታል ፤ ስለሆነ ፡ አስቀድሞ ፡ የላክነውን ፡ ሃሳብ ፡ በዚያው ፡ ሆኖ ፡ ተከታታይና ፡ ለዝርዝሩ ፡ አፈጻጸም ፡ ተመልካች ፡ ያስፈልገዋል ።

ስለ ፡ አውሮፕላን ፡ እርዳታ ፡ በብርቱ ፡ የጠየቅነውን ፡ ጽፈንልሃል ። አሁን ፡ በአንተ ፡ ዘንድ ፡ የሚገኘው ፡ ኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ ለአውሮፕላን ፡ እርዳታ ፡ የበረታ ፡ ቃል ፡ ተቀብሎ ፡ የመጣ ፡ ስለሆነ ፡ በዚህም ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ አረጋግጦ ፡ አስታውቆናልና ፡ ልትነጋገረው ፡ ትችላለህ ።

ስለ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬ ፡ መሣሪያው ፡ አለመድረሱ ፡ የሚያሳዝን ፡ ሆኖዋል ፤ የተቻለ ፡ ያህል ፡ እንዲጣደፍ ፡ ጠይቀናል ፤ አጋፋሪ ፡ ያረጋል ፡ መምጣቱን ፡ ስለጻፍክልን ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ እንደደረሰ ፡ በቶሎ ፡ ከሰዎቹ ፡ ጋራ ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ አለንበት ፡ እንዲመጣ ፡ እንድታስታውቀው ፡ ይሁን ። ባለፈው ፡ ፖስታ ፡ ይህንኑ ፡ የጻፍንለት ፡ ደብዳቤ ፡ ሳይደርስህ ፡ አልቀረም ፤

ከበጌምድር ፡ የመጣውንም ፡ ሰው ፡ እንዳሳሰብከው ፡ ሁሉንም ፡ አቅርበን ፡ እናየዋለን ፤ ደጃዝማች ፡ ደስታ ፡ እሸቴ ፡ የደረሰበትን ፡ አየነው ። ወደ ፡ ወለጋም ፡ ደግሞ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ለመላክ ፡ አስበናል ። ስለ ፡ ጣልያኖች ፡ የጦር ፡ ቦታ ፡ መለዋወጥ ፡ የጻፍከውንም ፡ ለጦር ፡ አለቆች ፡ አስታውቀናቸዋል ።



ሜጫ ፡ ውስጥ ፡ የሚሠራው ፡ አበረ ፡ በጣም ፡ ጀግና ፡ መሆኑንና ፡ ከዚህም ፡ ቀደም ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ሆኖ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻን ፡



ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬ ፡

ለመውጋት ፡ ተነስቷል ፡ ማለትን ፡ ሰምተን ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፈንለት ፡ ነበር ። አሁንም ፡ ለሥራው ፡ እንዲያበረታው ፡ ጽፈንለታልና ፡ እንዲደርስለት ፡ አድርግ ፤

የሐንስ ፡ ለጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ ምላሹን ፡ ወደ ፡ ጎጃም ፡ እንዲመጣ ፡ ጽፌንለታል ። በዚያ ፡ ካየነው ፡ በኋላ ፡ ከደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አበዩ ፡ ጋራም ፡ ቢሠራ ፡ እናስብበታለን ።

የዳንግላንና ፡ የእንጅባራን ፡ መለቀቅ ፡ ሳትሰማ ፡ አልቀረህም ፡ ይህም ፡ እኛ ፡ በተቃረብንበት ፡ ጊዜ ፡ በመሆኑ ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ ነው ፡ ደህና ፡ ደህና ፡ በቅሎዎችና ፡ አጋሰሶች ፡ በእንግሊዞች ፡ በኩል ፡ ከሚደራጀው ፡ በቀር ፡ በተለይ ፡ መርጠህ ፡ እንድትገዛ ፡ ይሁን ።

ለዮሐንስ ፡ የተጻፈውን ፡ ደብዳቤ ፡ ልከንልሃል ። ወረቀቱን ፡ የሚወስደው ፡ ሰው ፡ ዮሐንስ ፡ መጥቶ ፡ ከኛ ፡ ተገናኝቶ ፡ ቢመለስ ፡ የሚሻል ፡ መሆኑን ፡ እንዲያስረዳው ፡ በቃል ፡ በአንተም ፡ ስም ፡ ንገረው ።

የካቲት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጻፈ ።

## ከኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ ጋር ፡ ስለፈጸምነው ፡ የጦር ፡ ሥራ ፡ ተግባር ።

ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በየጊዜው ፡ የተጻፉትን ፡ የሥራ ፡ መምሪያ ፡ ደብዳቤዎችና ፡ አዋጆች ፡ አንባቢ ፡ እንዲመለከታቸው ፡ ካደረግሁ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጦሩ ፡ ሥራ ፡ ተግባር ፡ እመለሳለሁ ። ከፍ ፡ ብሎ ፡ በዚሁ ፡ የታሪክ ፡ ማስታወሻ ፡ እንደተገለጸው ፡ በመጀመሪያ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ታዘው ፡ ቀድመው ፡ የመጡት ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ትእዛዝ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰው ፡ በምትካቸው ፡ የተላኩት ፡ ኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ ተተክተው ፡ እንዲሠሩ ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ የካቲት ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ደርሶኝ ፡ በትእዛዙ ፡ መሠረት ፡ ከኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ ጋር ፡ የፈጸምናቸውን ፡ የጦር ፡ ሥራዎች ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ መስመር ፡ እገልጻለሁ ።

ከኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ ጋር ፡ አብረን ፡ በተሰማራንበት ፡ ጊዜ ፡ የነበረውን ፡ የጦር ፡ አቅድ ፡ እንዲሁ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ለመዘርዘርና ፡ በሙሉ ፡ ለመጻፍ ፡ አስቸጋሪ ፡ ቢሆንም ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ሁናቴውን ፡ ለመግለጽ ፡ ያህል ፡ እሞክራለሁ ።

በአንደኛው ፡ ቀን ፡ ስለጦርነቱ ፡ አመራር ፡ ከሻለቃ ፡ ዊንጌት ፡ (በኋላ ፡ ጀኔራል) ፡ ጋር ፡ ስንነጋገር ፡ አርበኞች ፡ ሁሉ ፡ ለምንድነው ፡ በየምሽጉ ፡ እየቀረቡ ፡ የማይዋጉት ፡ ሲሉ ፡ ጠየቁኝ ፡ እኔም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ቀደም ፡ አድርጊ ፡ ከአርበኞች ፡ መሪዎች ፡ ጋር ፡ ተነጋግሬበት ፡ ስለነበረ ፡ መሪዎቹ ፡ ያሉኝን ፡ የአርበኞቹ ፡ ሃሳብ ፡ ጠላት ፡ ከምሽጉ ፡ ወጥቶ ፡ የሚገጥመን ፡ ቢሆን ፡ የማንንም ፡ እርዳታ ፡ ሳንጠይቅ ፡ እኛው ፡



እንበቃዋለን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንዳይጥ ፡ እካብ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የተደበቀውን ፡ ለመቀስቀስ ፡ የመድፍና ፡ የአይሮፕላን ፡ እርዳታ ፡ ያስፈልጋልና ፡ ለምን ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ አይረዱንም ፡ ነው ፡ የሚሉት ፡ ብዬ ፡ ስመልስላቸው ፡ ከሻለቃ ፡ ዊንጌት ፡ ያገኘሁት ፡ መልስ ፡ የመድፍና ፡ የአይሮፕላን ፡ እርዳታ ፡ በቅድሚያ ፡ የሚሰጠው ፡ በሐረር ፡ በኩል ፡ ለሚመጣው ፡ በቀጥታ ፡ በእንግሊዞች ፡ ለሚመራው ፡ ጦር ፡ ነው ፡ ምክንያቱ ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ በቅድሚያ ፡ ለመያዝ ፡ የታሰበው ፡ በእንግሊዞች ፡ በቅድሚያ ፡ መግባት ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ የአይሮፕላንና ፡ የመድፍ ፡ እርዳታ ፡ ሳንጠብቅ ፡ ይህ ፡ በጃንሆይ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የሚመራው ፡ ጦር ፡ በቅድሚያ ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ ለመያዝ ፡ እንዲችል ፡ አጥርተን ፡ እየጠረግን ፡ ባንሄድም ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ እንዳይገናኝ ፡ እየቆረጥን ፡ ክብ ፡ እያደረግን ፡ እያለፍነው ፡ እንድንሄድ ፡ የማጥራቱ ፡ ጉዳይ ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ ከያዝን ፡ አስቸጋሪ ፡ አይሆንም ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ እንዲሠሩ ፡ ተነጋገሩበት ፡ ሲሉ ፡ አስረዱኝ ። እኛም ፡ ከዚህ ፡ ንግግር ፡ በኋላ ፡ እንደምክሩ ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ እንዳለን ፡ ጠላትም ፡ በበኩሉ ፡ ተቋርጦ ፡ መቅረቱን ፡ አስቦ ፡ ኖሮ ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ በአገውና ፡ በዳሞት ፡ የነበረውን ፡ ጦር ፡ አንድነት ፡ ማቀላቀል ፡ ጀምሮ ፡ ዳንግላ ፡ የነበረውን ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ ካለው ፡ ጋር ፡ እንጅባራ ፡ ያለውን ፡ ከቡሬ ፡ ዳሞት ፡ ካለው ፡ ጋር ፡ ቀላቀለና ፡ ዋንና ፡ ማንኩሳ ፡ ጅጋ ፡ ያለውን ፡ ጦር ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡ እያቀላቀለ ፡ በኃይል ፡ እየተዋጋ ፡ ወደ ፡ ደንበጫና ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ መስመር ፡ እንደገለጥኩት ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ካለው ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ለማቀላቀል ፡ ሲገሰግስ ፡ የጨረቃ ፡ በተባለው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ቀድሞ ፡ ይጠባበቅ ፡ ከነበረው ፡ ከእኛ ፡ ጦር ፡ ላይ ፡ በድንገት ፡ ስለደረሰ ፡ በሁለቱም ፡ በኩል ፡ በድንገት ፡ የተጋጠሙ ፡ ስለሆነ ፡ የጨበጣ ፡ ጦርነት ፡ ነው ፡ የተዋጉት ። ሆኖም ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ ይመራ ፡ የነበረው ፡ ልጅ ፡ ማሞ ፡ ኃይለሚካኤል ፡ የተባለው ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ስለነበረ ፡ የኛ ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ የማይበገር ፡ መሆኑን ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ መንገድ ፡ አሳብሮ ፡ ዋናውን ፡ ጎዳና ፡ ለቆ ፡ ወደ ፡ ባላገር ፡ ገብቶ ፡ በመዘዋወር ፡ ደንበጫ ፡ ደርሶ ፡ ደንበጫ ፡ ያለውንም ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ አስወጥቶ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ወስዶ ፡ ቀላቀለው ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በድጋሚ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ገልጨ ፡ የጻፍኩት ፡ ሻለቃ ፡ ዊንጌት ፡ ስለጦርነቱ ፡ ይሰጡን ፡ የነበረውን ፡ ግልጥ ፡ ያለ ፡ ምክርና ፡ ወዳጅነታቸውም ፡ የማይዘነጋ ፡ መሆኑን ፡ ለማስታወስ ፡ ነው ።

አዲሱ ፡ የጦር ፡ ባልደረባ ፡ ኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ በቡሶልና ፡ በካርታ ፡ ብቻ ፡ የሚመራ ፡ እንጂ ፡ ጠላት ፡ ያለበት ፡ የት ፡ ነው ፡ መግቢያ ፡ መውጫውስ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ለማጥቃትስ ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ ቢሠራ ፡ ይጠቅማል ፡ ብሎ ፡ ከሰው ፡ የማይጠይቅ ፡ ስለነበረ ፡ አብረነው ፡ የምን

ገኘውን ፡ ሁሉ ፡ እየወሰደ ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ባለበት ፡ ምሽግ ፡ ላይ ፡ ማጋፊጥ ፡ ነበር ። ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከእንጅባራ ፡ ወደ ፡ ቡሬ ፡ ሄደን ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ጦር ፡ አደጋ ፡ ለመጣል ፡ ማታ ፡ ከእንጅባራ ፡ ስንነሳ ፡ ለጦሩ ፡ አቅራቢያ ፡ በሆነ ፡ ቦታ ፡ ስንደርስ ፡ እንድንቆምና ፡ ሃሳብ ፡ ለሃሳብ ፡ ተለዋውጠን ፡ አደጋ ፡ እንጥላለን ፡ በማለት ፡ ስንነጋገር ፡ የመቆሚያውን ፡ ቦታ ፡ የሚአመለክት ፡ ጦር ፡ የቀደመ ፡ መሆኑ ፡ ተነገረንና ፡ እቀደመው ፡ ጦር ፡ ዘንድ ፡ ስንደርስ ፡ ምልክት ፡ እንድናገኝ ፡ ለቀደመው ፡ ጦር ፡ የተነገረውን ፡ ምልክት ፡ ነግሮን ፡ ጉዞአችንን ፡ ቀጠልን ። እኛም ፡ ተጉዘን ፡ በመንገዳችን ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ሳናገኝ ፡ ረጅም ፡ ጉዞ ፡ አድርገን ፡ በመጨረሻ ፡ የእሳት ፡ ውጋጋን ፡ ስለአየን ፡ የተባለው ፡ የሚጠብቀን ፡ ጦር ፡ ነው ፡ አልንና ፡ ምልክት ፡ መስጠት ፡ ጀመርን ፡ ያልሰማንም ፡ቢርቀው ፡ ይሆናል ፡ አልንና ፡ ምልክቱን ፡ እያሰማን ፡ በጣም ፡ ቀረብን ።በዚህ፡ ጊዜ ፡ የእኛ ፡ ጦር ፡ መስሎ ፡ የቀረብነው ፡ ጦር ፡ የጠላት ፡ ምሽግ ፡ ኖሮ ፡ የጠላት ፡ ዘብ ፡ ጠባቂ ፡ አደጋ ፡ እንደደረሰበት ፡ ተረዳና ፡ ተሰብሰቡ ፡ ብሎ ፡ የክፍሉን ፡ ወታደሮች ፡ ሰበሰበና ፡ ተኰሰብን ።

እኛም ፡ ያልጠበቅነው ፡ ነገር ፡ ሆኑብን ፤ ያን ፡ ቦታ ፡ በቀን ፡ አላየነውም ፡ ነበርና ፡ ብንታኰስ ፡ መዘዋወሪያችን ፡ ወዴት ፡ እንደሆነ ፡ የጠላትስ ፡ ጦር ፡ በዚያ ፡ ያለው ፡ መጠኑ ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ አላመዛዘንም ፡ ስለዚህ ፡ ለጊዜው ፡ የምናደርገው ፡ መላ ፡ ቸገረን ፡ ኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ በዚያ ፡ አልተገኙም ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ የጠላት ፡ ተኩስ ፡ ጋብ ፡ እስቲል ፡ ምድር ፡ ያዝንና ፡ ፀጥ ፡ ብለን ፡ ቆየን ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ እምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ ተኩሱን ፡ ያለፋታ ፡ መተኰስ ፡ እንጂ ፡ ከምሽግ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ ሁኔታውን ፡ መረዳት ፡ አይችልም ። የእኛ ፡ ፀጥ ፡ ማለት ፡ የሱን ፡ ተኩስ ፡ ሲአቆመው ፡ እኛም ፡ በቀስታ ፡ እርምጃ ፡ ድምጣችንን ፡ አጥፍተን ፡ ወደ ፡ መጣንበት ፡ መመለስ ፡ የተሻለ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ተመለስን ። ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ በጉዞ ፡ ከጨረስነው ፡ በኋላ ፡ በ፲ ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ጐድጐድ ፡ ያለች ፡ ቦታ ፡ ስናገኝ ፡ብዚያች ፡ ቦታ ፡ ጥቂት ፡ እንዳረፍን ፡ ወገግ፡ አለና ፡ ብርሃን ፡ መታየት ፡ ሲጀምር ፡ ያለፍነው ፡ የእኛ ፡ ጦር ፡ ባሻጋሪያችን ፡ ሰፍሮ ፡ እኛን ፡ ጠላት ፡ አለ ፡ ከተባለበት ፡ ግንባር ፡ በኩል ፡ ሲአየን ፡ ጊዜ ፡ ለጦር ፡ ሰልፍ ፡ ይዘጋጁ ፡ ጀመር ። እኛም ፡ ለጊዜው ፡ እነማን ፡ እንደሆኑ ፡ በምልክት ፡ ለማስረዳት ፡ እንጣደፍ ፡ ጀመርን ፡ ሆኖም ፡ ከእኛም ፡ ከነሱም ፡ በኩል ፡ አለመጣደፋችን ፡ ረዳንና ፡ ሳንታኰስ ፡ ተዋወቅንና ፡ ተቀላቀልን ። ስለ ፡ ጉዞአችን ፡ ስንማከር ፡ በቡሶል ፡ የሚመራው ፡ ዊንጌት ፡ ሃሳቡን ፡ ለውጦ ፡ ኖሮ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመለሱ ፡ ብሎ ፡ ላከብን ።

እኛም ፡ ተመለስንና ፡ ፈጣም ፡ ከተባለው ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ አገኘነው ፡ ስንደርስ ፡ በዚህ ፡ አርፈን ፡ ውለን ፡ የምንሄድበትን ፡ እንማከራለን ፡አለን ። እኛም ፡ ተስማማን ፡ በዚያ ፡ ዋልንና ፡ ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ መንገድ ፡ ለወጠና ፡ ጉዞ ፡ ጀመርን ። ስንሄድ ፡ አደርንና ፡ ሊነጋ ፡ ሲል ፡ ጃቢ ፡ ከተባለ ፡ ለቡሬ ፡ አቅራቢያ ፡ በሆነ ፡ በባንዳ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ገባንና ፡ ከባንዳው ፡ ጋር ፡ ተቀላቀልን ፡ ባንዳው ፡ ባላገር ፡ ያላሰበው ፡ ነገር ፡ ሆኖበትና ፡ ፊዞ ፡ ከማየት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አላደረገ ። እኛም ፡ እዚያው ፡ እንዳለን ፡ ኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ እንደተራዛ ፡ ወይም ፡ እንደጦጣ ፡ ልበል ፡ ካንዱ ፡ ዛፍ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ዛፍ ፡ እየወጣ ፡ በመነጽር ፡ ዋንና ፡ ቡሬ ፡ ያለውን ፡ የጠላት ፡ ጦርና ፡ ምሽግ ፡ ሲአጠና ፡ ቆየና ፡ ከቀኑ ፡ ፫ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ዋን ፡ ከተባለው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ላይ ፡ ወሰደና ፡ አጋፈጠን ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ድንገተኛ ፡ ነገር ፡ ስለሆነበትና ፡ የእኛንም ፡ መጠን ፡ ገምቶ ፡ ባለማወቁ ፡ ባለበት ፡ ሆኖ ፡ መከላከልን ፡ ያዘና ፡ ከቡሬ ፡ ጦር ፡ እንዲደርስለት ፡ ልኰ ፡ ኖሮ ፡ የጠላት ፡ጦር ፡ ብዙ ፡ ፈረሰኛ ፡ ሆኖ ፡ ደረሰና ፡ በላያችን ፡ ላይ ፡ ተዘረገፈ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያለነው ፡ ጥቂትም ፡ ብንሆን ፡ መሬት ፡ በመያዛችን ፡ ባለንበት ፡ ሆነን ፡ በሮምታና ፡ አንድ ፡ መትረየስ ፡ በመሐከላችን ፡ ነበርና ፡ ሁሉም ፡ በንብረት ፡ ስለተተኰሰ ፡ ከፈረሰኞቹ ፡ ብዙዎቹን ፡ ከኰርቻው ፡ ላይ ፡መጣል ፡ ስንጀምር ፡ ጌታው ፡ የወደቀበት ፡ ፈረስ ፡ ገሚሱም ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ እየፏለለ ፡ ሲመጣ ፡ ገሚሱም ፡ እርካቡ ፡ ውስጥ ፡ ጫማው ፡ የገባውን ፡ ጌታውን ፡ እየጎተተ ፡ ያልወደቁትን ፡ ፈረሰኞች ፡ ፈረሳቸውን ፡ ሲአስደነብረው ፡ ወደ ፡ መጡበት ፡ ከመመለስ ፡ በስተቀር ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ መግፋታቸውን ፡ አቋረጡ ፡ ፈረሰኞችን ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ አድርጎ ፡ ሊከበን ፡ ከምሽግ ፡ የወጣው ፡ ጦር ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ምሽጉ ፡ ገባ ።

እኛም ፡ ባለንበት ፡ ሆነን ፡ መኖራችንን ፡ ለማስታወቅ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ የጥይት ፡ ተኩስ ፡ ስናሰማው ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ የመትረየስና ፡ የመድፍ ፡ ተኩስ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ይተኩስ ፡ ነበር ፤ አልፎ ፡ አልፎ ፡ የቦንብ ፡ተኩስ ነበር ፡ እኛም ፡ ጥይት ፡ ማስጨረሱም ፡ ቢሆን ፡ ጥቅም ፡ ነው ፡ በማለት ፡ በተኩስም ፡ በድምፅም ፡ እየተጣራን ፡ እንተነኩሰው ፡ ነበር ። ጠላትም ፡ ድምፅ ፡ በሰማበትና ፡ የተኩስ ፡ ድምፅ ፡ ወደ ፡ ተተኰሰበት ፡ የማባት ፡ ተኩሱን ፡ ሲአወርደው ፡ አደረ ።

ከቀኑ ፡ ፫ ፡ ሰዓት ፡ ጀምረን ፡ ከሌሊቱ ፡ እስከ ፡ አሥር ፡ ሰዓት ፡በዚያ፡ ቦታ ፡ ከቆየን ፡ በኋላ ፡ ኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ተመልክቶ ፡ ኖሮ ፡ ያን ፡ ቦታ ፡ እንድንለቅ ፡ አደረገና ፡ ያን ፡ ቦታ ፡ ለቀን ፡ ባንድ ፡ ጫካ ፡ ውስጥ ፡ ተደብቀን ፡ ዋልንና ፡ እንደተለመደው ፡ ምሽቱ ፡ ሲቃረብ ፡ ወደ ፡ አዘጋጀልን ፡ ሁለተኛው ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ አለበት ፡ ምሽግ ፡ ማንኩሳ ፡ ከተባለው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ወስዶ ፡ አጋፈጠን ፡ የዋንም ፡ ሆነ ፡ የማንኩሳ ፡ የቦታው ፡ አቀራረብ ፡ ከጠላት ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ ወጥቶ ፡ እንዲገጥመን ፡ እየተጠራራን ፡ እንነጋገር ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የጦር ፡ መላና ፡ ታክቲክ ፡ ከእንጅባራ ፡ እስከ ፡ ማንኩሳ ፡ ያለውን ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ሳያስበው ፡ ሌሊት ፡ እየደረስን ፡የውሀ መቅጃውን ፡ ቦታና ፡ ምሽጉን ፡ እንዳይወጣ ፡ እየከበብን ፡ ስለአስጨነቅ ነው ፡ ከእንጅባራ ፡ የመጣው ፡ ጦር ፡ ቡሬና ፡ ዋን ፡ ላይ ፡ የነበረውም ፡ አን ድነት ፡ ተደባለቀና ፡ ሁሉም ፡ አንድነት ፡ ተከማችቶ ፡ በአለው ፡ ኃይሉ ፡ ተከላክሎ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ካለው ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ለመቀላቀል ፡ የቆረጠ ፡ ሆኖ ፡ ተነሳ ። ማንኩሳ ፡ የነበረውን ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ እንደከበብን ፡ወገግ ፡ ሲል ፡ ከላይ ፡ በአይሮፕላን ፡ ከታች ፡ በመድፍና ፡ በመትረየስ ፡ በእጅ ፡ ቦንብም ፡ የሞተው ፡ ሞቶ ፡ የዳነው ፡ ይሂድ ፡ በሚአሰኝ ፡ ሁኔታ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነጎድጓዱን ፡ አወረደብን ። መደብቂያና ፡ መከላከያ ፡ የሆኑን ፡ ቅጠ ሎችና ፡ ቁጥቋጦችዎም ፡ መጋረጃነታቸውን ፡ አጡ ፤ የተጠጋንባቸው ፡ ድንጋዮች ፡ የማዳን ፡ ተስፋቸውን ፡ መድፍ ፡ አስለቀቃቸው ፤

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መትረየስ ፡ ተኳሾችም ፡ የሱዳን ፡ ወታደሮች ፡ መት ረየሳቸውን ፡ አንስተው ፡ የሽሽት ፡ መንገድ ፡ ሲጀምሩ ፡ ዊንጌት ፡ ደረ ሰና ፡ በጫማ ፡ እየረገጠ ፡ ቦታቸውን ፡ እንዳይለቁ ፡ አደረገና ፡ እሱም ፡ ዲሞትፈሩን ፡ አንግቦ ፡ ይታኮስ ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ መከላከል ፡ በየቦታው ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ አዘዘና ፡ በቡዕል ፡ የሚመራው ፡ ዊንጌት ፡ ዲሞትፎሩን ፡ አነገተና ፡ ሩጫውን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አመራ ፡ እኛም ፡ እኛን ፡ ተታኩሱ ፡ ብሎ ፡ አዞ ፡ እሱ ፡ ወዲት ፡ ይሸሻል ፡ ብቻውን ፡ ያለመሪስ ፡ ወዴት ፡ ይደርሳል ፡ ብለን ፡ ፈረሱን ፡ የያዘለትን ፡ ወታደር ፡ እንኳ ፡ ሳይ ፈልገው ፡ ብቻውን ፡ በእግሩ ፡ ስለሆነ ፡ የሄደው ፡ እንዲአደርስለት ፡ በሄ ደበት ፡ አቅጣጫ ፡ ፈረስ ፡ የያዘውን ፡ አከታተልነው ፡ እሱ ፡ ግን ፡ ማን ፡ ደርሶበት ፡ እኛም ፡ እስኪተቻለን ፡ ከተከላከልን ፡ በኋላ ፡ ያን ፡ ቦታ ፡ ለቆ ፡ መሸሽ ፡ ግድ ፡ ሆነብንና ፡ መንገድ ፡ ስንጀምር ፡ ወዴት ፡ ብንሄድ ፡ እናመ ልጣለን ፡ እያልን ፡ አመነታታንና ፡ ቢሆንም ፡ ትላንት ፡ ከእኛ ፡ ተከፍሎ ፡ የቀረውን ፡ ጦር ፡ ዊንጌት ፡ ያስማረበትን ፡ አቅጣጫ ፡ ይዞ ፡ መሄድ ፡ ይሻላል ፡ አልንና ፡ ወደዚያው ፡ ሄድን ።

## የጨረቃ ፡ በተባለው ፡ ስፍራ ፡ ስለተደረገው ፡ ጦርነት ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ እዚያ ፡ የነበርነውን ፡ ጦር ፡ ወጭ ፡ አድርጎ ፡ ትላንት ፡ አራፊ ፡ ወደ ፡ አደረገው ፡ ጦር ፡ ኖሮ ፡ ያመራው ፡እዚያ፡ ሳንደርስ ፡ ጦሩን ፡ ቀስቅሶ ፡ በጠላት ፡ ጦር ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ለመጣል ፡ በሚ ቻልበት ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ በሚጓዝበት ፡ ጉዳና ፡ ላይ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ቦታ ፡ ሲአሲዝ ፡ ደረስንና ፡ ተቀላቀልን ። ዊንጌትም ፡ ከእኛ ፡ አስቀድሞ ፡ ለደንበጫ ፡ አቅራቢያ ፡ በሆነው ፡ የጨረቃ ፡ በተባለው ፡ ቦታ ፡ ያዘጋ ጀው ፡ የኛ ፡ ጦር ፡ ነበረና ፡ ወደዚያ ፡ እንዲጠነቀቅ ፡ ለመላክ ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ መንገድ ፡ ይዞ ፡በመሸሽ ፡ የሚገሰግስ ፡ ስለሆነ ፡ መላክተኛ ፡ ለማ ስቀደም ፡ አልተቻለም ።

ስለዚህ ፡ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ቢሆን ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ ሥጋት ፡ እንዳይለየው ፡ እየተከተለ ፡ የተኩስ ፡ ድምፅ ፡ ማስማትን ፡ መረጠ ። በዚ ሁም ፡ ታክቲክ ፡ ተገፋና ፡ አቋራጭ ፡ ቦታ ፡ ሲገኝ ፡ ቀድሞ ፡ ከወደፊቱ ፡ እንደዚሁም ፡ በመከታተል ፡ እንዳይታዩ ፡ እየሆኑ ፡ ተኩስ ፡ የሚአሰሙ ፡ ወታደሮች ፡ አስማራበት ። የጠላትም ፡ ጦር ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የወር ፡ የጭፍኑን ፡ ሲሄድ ፡ የእኛም ፡ ጦር ፡ ሳያስበው ፡ በድንገት ፡ የጨረቃ ፡ እተባለው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ የጨበጣ ፡ ጦርነት ፡ ተዋጉ ። የጠላትም ፡ ጦር ፡ ሳያስበው ፡ ከማንባሩ ፡ የርሳስ ፡ በረዶ ፡ ቢወርድበትም ፡ ወደኋላም ፡ እን ዳያፈገፍግ ፡ እየተኰሰ ፡ የተከተለው ፡ ጦር ፡ መኖሩን ፡ ስለሚአውቅ ፡ ያለቀው ፡ አልቆ ፡ ወደፊት ፡ መሄድን ፡ መረጠና ፡ እየተታኰሰ ፡ ተቀላ ቀለ ። የእኛም ፡ ጦር ፡ ከዚያው ፡ ቦታ ፡ በስተቀር ፡ የማፈግፈጊያ ፡ ቦታ ፡ ያዘጋጀ ፡ ባለመሆኑ ፡ ቦታውን ፡ ይዞ ፡ ሳይነቃነቅ ፡ ይታኰስ ፡ ስለነበረ ፡ ምንም ፡ ከጠላት ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ በጉዞ ፡ ላይ ፡ የነበረ ፡ ሆኖ ፡ ያለ ቀው ፡ የብዛት ፡ ብልጫ ፡ ቢኖረው ፡ በእኛም ፡ በኩል ፡ ብዙ ፡ ጀግኖች ፡ አለቁ ፡ ቆሰሉም ፡ ይህ ፡ የሆነው ፡ የካቲት ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሐሙስ ፡ ነው ።

## በዚህ ፡ ቀን ፡ የጨረቃ ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ ጦርነት ፡ የሞቱ ትና ፡ የቈሰሉት ፡ ስማቸው ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ገጽ ፡ ተጽፏል ።


በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ያች ፡ በር ፡ በሕይወት ፡ የማይታለፍባት ፡ መሆኑን ፡ ሲረዳ ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ ከቡሬ ፡ ይዞ ፡ የመጣው ፡ ማግሮ ፡ ኃይለ ሚካኤል ፡ ስለነበረ ፡ ጎዳናውን ፡ ለቀቀና ፡ ጫካውን ፡ ጥሶ ፡ ወደ ፡ ባላገር ፡ ወ ስጥ ፡ ገባ ። የተረፈውንም ፡ ወታደር ፡ ይዞ ፡ ደንበጫ ፡ ለመድረስ ፡ቻለና፡ ከደንበጫ ፡ ካለው ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ተቀላቀለ ። ወዲያው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ማር ቆስ ፡ ጉዞውን ፡ ቀጠለና ፡ አማኑኤል ፡ ሲደርስ ፡ እንደዚሁ ፡ ከዚያም ፡ ያለውን ፡ ጦር ፡ አስነሳና ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ን ፡ ዙሪያዋን ፡ ይዞ ፡ ሰፈረ ፡ ከጨረቃ ፡ እስከ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ዙሪያ ፡ እስኪሰፍር ፡ ጦር ፡ እንደተ ከተለው ፡ ሆኖ ፡ ሲሸሽ ፡ ነበር ። ሠፈር ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ቢጠይቅ ፡የእኛ ፡ ጦር ፡ ከደንበጫ ፡ ያላለፈ ፡ መሆኑን ፡ ሲረዳ ፡ እንደገና ፡ አስተጋባና ፡ አማ ኑኤልን ፡ ተመልሶ ፡ ያዘ ። ቢሆንም ፡ እጅ ፡ ቀምሷልና ፡ ሥጋቱ ፡ በአማ ኑኤል ፡ ምሽግ ፡ እንዲቆይ ፡ አላደረገውም ። ወዲያው ፡ ለቆ ፡ ተጠቃሎ ፡ በደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ዙሪያ ፡ ጉሊት ፡ የተባለውን ፡ በር ፡ ያዘና ፡ ሰፈረ ፡ የእ ኛም ፡ ጦር ፡ በደንበጫ ፡ ባካባቢዋ ፡ በየጫካው ፡ ተሠገሠገና ፡ ወደፊትም ፡ ወደኋላም ፡ እየተሳለለ ፡ በማጥናት ፡ ላይ ፡ ሆነ ።

የካቲት ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡

## ጐጃም ፡ ዳሞት ፡ ጨረቃ ፡ በተባለው ፡ ቦታ ፡ በተደረገው ፡ ጦርነት ፡ የሞቱ ።

፩ ፡ ግራዝማች ፡ ደበላ ፡
፪ ፡ መንገሻ ፡ ሽብሬ ፡
፫ ፡ ጋሻው ፡ በዛ ፡ ኃይሌ ፡
፬ ፡ ንጋቱ ፡ ዱባለ ፡
፭ ፡ መርሻ ፡ ድቤ ፡
፮ ፡ ስጦታው ፡
፯ ፡ ኃይለ ፡ ሚካኤል ፡ ጋረደው ፡
፰ ፡ የሮም ፡ ሰገድ ፡ ወልዴ ፡ ሥላሴ ፡
፱ ፡ ከበደ ፡ ወልዴ ፡ ጊዮርጊስ ፡

### በዚሁ ፡ ቀን ፡ የቈሰሉ ።



ፊታውራሪ ፡ ጋረደው ፡ ኪዳኔ ፡ (ደጃዝማች) ።

፩ ፡ ፊታውራሪ ፡ ጋረደው ፡ ኪዳኔ ፡ (ደጃዝማች) ፡
፪ ፡ ሻለቃ ፡ አየለ ፡ ኃይሌ ፡
፫ ፡ በቀለ ፡ አደራ ፡



፬ ፡ ደርቤ ፡ ገነት ፡ ይዋሉ ፡
፭ ፡ አስራት ፡ ተገኝ ፡
፮ ፡ ካሣ ፡ ኃይሌ ፡
፯ ፡ ፈለቀ ፡ ወልዴ ፡ ጻድቅ ፡
፰ ፡ ጣሰው ፡ ምንዳ ፡
፱ ፡ በቀለ ፡ ሙሄ ፡
፲ ፡ ውሴን ፡ ጕበና ፡
፲፩ ፡ መኰንን ፡ በሽል ፡
፲፪ ፡ አበበ ፡ ተስፋዬ ፡



አቶ ፡ ፈለቀ ፡ ጃኘ ፡ (ደጃዝማች) ።

ስለታሪኩ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፷ ተመልከት ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

## ወደ ፡ መተከል ፡ ሄጄ ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ እንደተገናኘሁ ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ወደ ፡ አሉበት ፡ ወደ ፡ መተከል ፡ እንድሄድ ፡ ጥሪ ፡ ደረሰኝ ፡ የተጻፈልኝም ፡ የግርማዊነታቸው ፡ ትእዛዝ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ፡ ከአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ።

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና ፡ ነን ፤ ይኸውና ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ አለንበት ፡ እንድትመጣ ፡ ጽፈንልህ ፡ ስለነበረ ፡ ወደመተከል ፡ ለመሄድ ፡ መነሳታችን ፡ ስለሆነ ፡ እዚያው ፡ ድረስ ፡ እንድትመጣ ፡ ይሁን ፡

የካቲት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጻፈ ።

ይህ ፡ ጥሪ ፡ የተጻፈልኝ ፡ በየካቲት ፡ ፲፪ ፡ ሲሆን ፡ ለኔ ፡ የደረሰኝ ፡ ግን ፡ በመጋቢት ፡ ነበር ፡ ምክንያቱም ፡ በብርቱ ፡ የጦር ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ስለነበርሁ ፡ ነው ። በደረሰኝ ፡ ጊዜም ፡ እንደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬ ንና ፡ ከበጌምድር ፡ ከንአዛዥ ፡ ቦጋለ ፡ ጋር ፡ የመጡ ፡ አርበኞች ፡ ስለ ነበሩ ፡ እነርሱንም ፡ ጨምሬ ፡ አንድነት ፡ ሆነን ፡ ወደ ፡ መተከል ፡ ሄድ ንና ፡ መጋቢት ፡ ፲፪ ፡ ዓርብ ፡ ከጃንሆይ ፡ ተገናኝተን ፡ አደርን ። ግርማዊ ነታቸውም ፡ በማግሥቱ ፡ ወደ ፡ ማንባር ፡ ጉዞአቸውን ፡ ቀጠሉና ፡ እንጅ ባራ ፡ ሲደርሱ ፡ እንደዚሁ ፡ ከደጃዝማች ፡ መንገሻና ፡ ከአርበኞቻቸው ፡ ጋር ፡ ተገናኙ ፡ ከዚያም ፡ ወደቡሬ ፡ ጉዞ ፡ ሆኖ ፡ ቡሬ ፡ ሲደርሱ ፡ ደጃዝ ማች ፡ ነጋሽ ፡ ከነአርበኞቻቸው ፡ በሰልፍ ፡ ተገናኙ ፡ በዚያውም ፡ ለቡሬ፡ ከተማ ፡ አቅራቢያ ፡ በሆነ ፡ ዋን ፡ ከተባለ ፡ ቦታ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ሰፈር ፡ ሆነ ። ግርማዊነታቸወ ም ፡ በዚህ ፡ ቦታ ፡ እንዳሉ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ማር ቆስ ፡ ዙሪያ ፡ ከተሰማራው ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ እንድሠራ ፡ ከበ ላይ ፡ ጦር ፡ መሪአችን ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀብዬ ፡ ወደፊት፡ ቀደምኩ ።



ደንበጫን ፡ አለፍ ፡ ስል ፡ ከየጨረቃ ፡ ጦርነት ፡ የተረፈው ፡ በኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ የሚመራው ፡ ጦር ፡ በየጫካው ፡ ተሰግስጎ ፡ ትእዛዝ ፡ ሲጠብቅ ፡ አገኘሁትና ፡ ከተመካከርን ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ዙሪያ ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የታዘዝኩትን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ቀደ ምኩ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የተላከልኝን ፡ የሥራ ፡ መምሪያና ፡ እኔም ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የላክሁትን ፡ የሥራ ፡ መግለጫ ፡ ራፖር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በየተራ ፡ እገልጣለሁ ።

## የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጠቅላይ ፡ መሪ ፡ ማኅተም ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ፡ ከአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና ፡ ነን ። በ፲፮ ፡ አዋቢያ ፡ ሌሊቱን ፡ ብዙ ፡ መድፍ ፡ ተኩስ ፡ በሰፈራችን ፡ ተሰማ ። የዚህ ፡ እርግጠኛው ፡ ወሬ ፡ ምንድነው ። ፪ኛ ፡ አማኑኤልን ፡ ኢጣልያኖች ፡ ከያዙ ፡ ወዲህ ፡ በደንበጫና ፡ በአማኑኤል ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ አሉት ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ አኳሆንና ፡ የደረሰበትን ፡ ቦታ ፤ ስለፊታውራሪ ፡ ኃይለ ፡ ኢየሱስና ፡ ስለ ፡ ቀኛዝማች ፡ ገበየሁ ፡ ምን ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፤ የደብረ ፡ ማርቆስን ፡ ውስጥ ፡ ወሬ ፡ በባንዳዎችም ፡ በታማኞችም ፡ ተሰልሎ ፡ የተገኘውን ፡ ዝርዝር ፡ በፍጥነት ፡ እንድትአስታውቀን ፡ የደንበጫንም ፡ እርድ ፡ አኳኋንና ፡ ወደዚያም፡ በመጣን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ሰፈሩ ፡ አኳኋን ፡ የሚስማማውን ፡ ቦታ ፡ ያየኸውንና ፡ ያሰብኸውን ፡ ጻፍልን ። በእዚያም ፡ በደንበጫ ፡ ዙሪያ ፡ የተሸመተና ፡ የተሰበሰበ ፡ እህል ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይገኛል ፤ አስቀድሞስ ፡ እንደ ፡ አበበ ፡ አስረስ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ መላክ ፡ የሚአስፈልግ ፡ እንደሆነ ፡ እንድት አስታወ ቀን ፡ በደንበጫ ፡ የተማረከ ፡ የኢጣልያኖች ፡ ስንቅ ፡ የተገኘው ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ነው ።

መጋቢት ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
በዋና ፡ ጦር ፡ ሠፈር ፡ ተጻፈ ።

## የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጠቅላይ ፡ መሪ ፡ ማኅተም ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ፡ ከአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ።

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና ፡ ነን ፡ ኰሎኔል ፡ ዊንጌትም ፡ መጥቶ ፡ ተገናኘን ። ለነደጃዝማች ፡ መንገሻና ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ የሚስማሩበትን ፡ ሳያስታውቅ ፡ በመምጣቱ ፡ ደስ ፡ እንዳላለን ፡ ነግሬዋለሁ ። እዚያ ፡ ደርሰህ ፡ እንደ ፡ መረመርኸውና ፡ እንደተመለከትከው ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽና ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻም ፡ ከከዳው ፡ ባንዳ ፡ እንዳይጋጩ ፡ ሁለቱም ፡ ተለያይተው ፡ ቦታ ፡ ቦታቸውን ፡ እንዲይዙ ፡ አመልክታቸው ። ኰሎኔል ፡ ባወ ስቴድ ፡ የሚባለውንም ፡ ያገኘኸው ፡ እንደሆን ፡ አሳብ ፡ እንዲረዳህ ፡ ጠይቀው ። የአውሮፕላን ፡ እርዳታም ፡ በፍጥነት ፡ እንዲደረግ ፡ አዘናል ። እኛም ፡ በዚህ ፡ ሰሞን ፡ ወደዚያው ፡ ለመቅረብ ፡ እንነሳለን ፡ ብለን ፡ ያሰብነውን ፡ ከአንተ ፡ ሙሉ ፡ ራፖር ፡ ባለመድረሱ ፡ መሰናከል ፡ ሆኖአልና ፡ በቶሎ ፡ ጻፍልን ።

መጋቢት ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
በዋና ፡ ጦር ፡ ሠፈር ፡ ተጻፈ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፉት ፡ የሥራ ፡ መምሪያ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ወደእኔ ፡ ከመድረሳቸው ፡ አስቀድሞ ፡ እኔ ፡ በመጋቢት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ዓ ፡ም ጽፌ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የላክሁት ፡ ራፖር ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

ለግርማዊ ፡ ጌታዬ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡

መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ዕድሜ ፡ ከጤና ፡ አስተባብሮ ፡ ይስጥልኝ ፡ እያልኩ ፡ ባሪያዎ ፡ እጅ ፡ እነሳለሁ ።


ግርማዊ ፡ ሆይ ፤

ስለአማኑኤልና ፡ ስለማርቆስ ፡ አከባበብ ፡ የደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጦር ፡ እንዲመጣ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ አልታየኝምና ፤ ግርማዊነትዎ ፡ አስበውበት ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጦራቸውን ፡ አክተው ፡ የባሕር ፡ ዳሩን ፡ ቢወጉ ፡ ይሻላል ፤ ቢአስፈልግም ፡ የዴንሳና ፡ የአቸፈር ፡ ጦር ፡ ብቻ ፡ ቢመጣ ፡ ለሁሉም ፡ ይሻላል ፡ እዚህም ፡ ቢመጡ ፡ ይተፋፈግ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ይረዱ ፡ አይመስለኝም ። እዚህ ፡ እንደተመለከትኩት ፡ ከደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ጋር ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ ያለው ፡ ጦር ፡ ሲጨመር ፡ የሚበቃ ፡ ነው ፡ የመሰለኝ ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ያሉት ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ፩ ልጅ፡ ደምሴ፡ ዓለማየሁ ፡ ፪ ፊታውራሪ ፡ በየነ ፡ ቢሻው ፡ ፊታውራሪ፡ ገበየሁ፡ ወልደማርያም ፡ ከነዚህም ፡ ጋር ፡ አዲስ ፡ የሚወጣው ፡ ባንዳ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀም ፡ ባንድ ፡ ፊት ፡ ይረዳል ። ግርማዊነትዎም ፡ ከቡሬ ፡ ለቀው ፡ ወደዚህ ፡ ሲመጡ ፡ ደምበጫ ፡ ሳይገቡ ፡ እደጋ ፡ ዳሞት ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ በርቀኝና ፡ እናሞራ ፡ እሚባለው ፡ አገር ፡ መሐከል ፡ ጥሩ ፡ መሣፈሪያ ፡ አለና ፡ ነጋድራስ ፡ ክፍሌ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቀድሞ ፡ ቀኛዝማች ፡ ተመስገን ፡ የሚባለውን ፡ የደጃዝማች ፡ ነጋሽን ፡ ሹም ፡ ይዞ ፡ ቢአሰናዳ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ለአደጋም ፡ የማያሰጋና ፡ ለሁለቱም ፡ ወገን ፡ ወሬ ፡ አቅራቢያ ፡ ነው ። ቦታውም ፡ ብዙ ፡ ሜዳና ፡ ትልቅ ፡ ወንዝ ፡ ያለው ፡ ቀጨም ፡ የሚባለው ፡ ነው ፤ ጦርም ፡ ቢበረታ ፡ ከጀርባው ፡ የሚገኘው ፡ አገር ፡ ካንድ ፡ ፊት ፡ በሙሉ ፡ ደጋ ፡ ዳሞት ፡ ነው ። ካንድ ፡ ፊት ፡ የቡሬ ፡

---

፩ ልጅ ፡ ደምሴ ፡ ዓለማየሁ ፡ በደጋ ፡ ዳሞትና ፡ በሞጣ ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ አርበኛ ፡ ነው ። በበላዩ ፡ ማንም ፡ ሳይኖርበት ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ሆኖ ፡ ነው ፡ የአገኘሁት ። በኋላም ፡ ከእኛ ፡ ከተገናኘ ፡ ወዲህ ፡ የሰጠነውን ፡ ምክር ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አውሎታል ። ይኸውም ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከጠላት ፡ ተልከው ፡ እሱ ፡ ባለበት ፡ አቅራቢያ ፡ ቂሮ ፡ በሚባል ፡ ምሽግ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ለማውጣትና ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ከሚገኘው ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ለማቀላቀል ፡ ቢመጡ ፡ ተታኩሶ ፡ ስለመለሳቸው ፡ ለጠላት ፡ ጦር ፡ የሚያደርጉትን ፡ እርዳታ ፡ አቋርጠው ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ገብተው ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ለእርዳታ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ መውጣታቸውን ፡ አቆሙ ።

፪ ፊታውራሪ ፡ በየነ ፡ ቢሻው ፡ በደብረ ፡ ማርቆስና ፡ በደምበጫ ፡ መካከል ፡ ማቻከል ፡ በተባለው ፡ አገር ፡ የነበረ ፡ ከጥሩዎቹ ፡ አርበኞች ፡ አንዱ ፡ ነው ። ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህ ፡ ቡሬ ፡ ዳሞት ፡ ሆነው ፡ እሱ ፡ ባለበት ፡ አገር ፡ ሆኖ ፡ በመላላክ ፡ የደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህን ፡ የበላይነት ፡ አውቆና ፡ ተቀብሎ ፡ ግንኙነት ፡ የነበረው ፡ የፊታውራሪነቱንም ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ የተቀበለው ፡ ከደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ መሆኑን ፡ ተረድቻለሁ ። ይህም ፡ስሙ ፡ የተጠቀሰው ፡ አርበኛ ፡ ከጀግንነቱም ፡ ጋር ፡ የሚታመንም ፡ ስለነበረ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ እንደገቡ ፡ ለከተማው ፡ ጥበቃ ፡ ከአርበኞች ፡ ውስጥ ፡ ተመርጦ ፡ እንዲቀርብ ፡ ተደርጎ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ በሞርሜ ፡ ለደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ከተማ ፡ ጥበቃ ፡ ቀርቦ ፡ ስለነበረ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ለሰዎቹ ፡ መሣሪያ ፡ ተሰጥቶ ፡ ለከተማው ፡ ጥበቅ ፡ ሹምና ፡ ለዘበኝነቱ ፡ አላፊ ፡ ሆኖ ፡ እንዲጠብቅ ፡ ተፈቅዶ ፡ የታዘዘና ፡ አገሩ ፡ በሹም ፡ ሽር ፡ እስቲደላደል ፡ ድረስ ፡ የታዘዘውን ፡ ተግባርና ፡ እምነቱን ፡ ሳያዛድል ፡ የፈጸመ ፡ ጥሩ ፡ አገልጋይ ፡ ነው ።



ነጋድራስ ፡ ክፍሌ ፡ ዳዲ ፡ (ደጃዝማች) ።



ዳሞት ፡ ነው ። ፫ ጣልያ ፡ ቋሪትም ፡ እስከ ፡ ዬንሳ፡ አቅራቢያ፡ ናቸው ። ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀም ፡ ካንድ ፡ የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ከካፒቴን ተሰንጀርና ፡ ከልጅ ፡ መርድ ፡ መንገሻ ፡ ጋር ፡ ተገናኝተው ፡ ሥራውን ፡ በደጀን ፡ ባለው ፡ መንገድ ፡ ሊሠራ ፡ መነሳቱን ፡ እርግጥ ፡ መሆኑን ፡ ሰማሁ ፤ በተረፈ ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ የሠራሁትና ፡ ከአገርም ፡ ውስጥ ፡ ያገኘሁትና ፡ የሰማሁት ፡ አኳኋን ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

መጋቢት ፡ ፲፫ ፡ ቅዳሜ ፡ ለት ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ተሰናብቼ ፡ በ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ቀረር ፡ ምሽጉን ፡ አልፈን ፡ ወንዙን ፡ ተሻግረን፡ ሰፈርን፤ በማግሥቱ ፡ ፲፬ ፡ መጋቢት ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ጉዞ ፡ ጀመርን ፤ ገወቻው ፡ ስንደርስ ፡ በፊት ፡ የሚሄደው ፡ ቃፊር ፡ ከቀረር ፡ ወዲህ ፡ ከጅጋ ፡ ወዲያ ፡ በመሐከል ፡ ሆነው ፡ መንገደኛውን ፡ እያቆሙ ፡ መልክተኛ ፡ አላስተላልፍ ፡ ብለው ፡ የሚያውኩት ፡ ወስላቶች ፡ ተያዙ ፡ ወዲያው ፡ በዋናው ፡ ጎዳና ፡ ስንጓዝ ፡ ፯ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ የጨረቃ ፡ ከሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ የኛ ፡ ሰዎች ፡ ጦርነት ፡ አደረጉበት ፡ ቦታ ፡ ደረስን ፡ ፬ ፡ ባለውሀ ፡ መትረየስ ፡ ተሰባብሮ ፡ ጥሎታል ። ፬ ፡ ታንክ ፡ በኛ ፡ አርበኞች ፡ ጥይት ፡ የተሰባበረውንና ፡ ጠላት ፡ ከፉኛ ፡ ድል ፡ የተመታበትን ፡ አይቼ ፡ ወዲያው ፡ በ፰ ፡ ሰዓት ፡ ደምበጫ ፡ ከተማ ፡ ገባን ። ከደምበጫ ፡ ማታውኑ ፡ የተገኘ ፡ ወሬ ፤ ከማርቆስ ፡ ያለው ፡ ባንዳ ፡ በጭራሽ ፡ ወጥቷል ። ባአካባቢው ፡ ያለውም ፡ ሕዝብ ፡ ከጠላት ፡ ከድቷል ፡ አሉ ፤ ፬ኛ ፡ የኛም ፡ ጦር ፡ ቢቸና ፡ ከተማ ፡ ገብቷል ፡ አሉ ፤ ፫ኛ ፡ ያማኑኤልም ፡ ጠላት ፡ ለቆ ፡ ከሄደ ፡ ወዲህ፡ ተመልሶ ፡ ከአማኑኤል ፡ ወዲህ ፡ የነጭ ፡ ከሚባለው ፡ ቦታ ፡ ሠፈረ ፡ አሉ ፤ ፊታውራሪ ፡ ገበየሁም ፡ ከጠላት ፡ የመለየቱን ፡ ወሬ ፡ አረጋገጡልኝ ፤

መጋቢት ፡ ፲፭ ፡ ሰኞ ፡ እላይ ፡ እንደተጻፈው ፡ በቀረርና ፡ በጅጋ ፡ መሐከል ፡ ያሉትን ፡ ወስላቶች ፡ ጥፋታቸው ፡ ተመርምሮ ፡ ከታወቀ ፡ በኋላ ፡ እዚያው ፡ ደምበጫ ፡ ገበያ ፡ ላይ ፡ ኃይሉ ፡ ወንድም ፤ ጀምበሬ ፡ ወርቅነህ ፡ አማኑ ፡ ክንዴ ፡ እንዳለ ፡ ይማም ፡ የተባሉት ፡ 4ቱንም ፡ ወስላ

---

፫ ቋሪትና ፡ ጣሊያ ፡ በተባሉት ፡ አገሮች ፡ የሚኖረው ፡ ሕዝብ ፡ ለቋሪት ፡ ቀኛዝማች ፡ አድማሱ ፡ ደስታን ፡ (በኋላ ፡ ፊታውራሪ ፡ የተባሉትን) ፡ ለጢጣሊያ ፡ ልጅ ፡ ዘውዴ ፡ መርድን ፡ ፊታውራሪ ፡ መርጦ ፡ የበላይ ፡ ሳይኖርባቸው ፡ በነሱ ፡ መሪነት ፡ ሲሠራ ፡ የቆየ ፡ የአርበኛ ፡ አገር ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ስማቸው ፡ የተጠቀሰው ፡ አርበኞች ፡ የሕዝቡን ፡ ምርጫ ፡ ጠብቀው ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ አገር ፡ ሊያጠቃ ፡ ሲመጣ ፡ ብቻ ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ መጣበት ፡ አገር ፡ እየሄዱ ፡ ጠላትን ፡ ሲያጠቁ ፡ የቆዩ ፡ አርበኞች ፡ ናቸው ። እነም ፡ ዳሞት ፡ ሰከላ ፡ እንደ ፡ ደረሰኩ ፡ እያንዳንዳቸውን ፡ አነጋግሬአቸው ፡ እምነት ፡ የሚጣልባቸው ፡ ሆነው ፡ ነው ፡ የአገኘኋቸው ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ የጦር ፡ ሠፈር ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ ታስቦ ፡ የነበረው ፡ ሰከላ ፡ ወንደ ፡ ገዝ ፡ የተባለው ፡ ቦታ ፡ በእነዚህ ፡ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አገሮች ፡ አቅራቢያ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ስንቅ ፡ ለማደራጀትና ፡ ለስንቅ ፡ የሚደራጀውን ፡ ለመሸመት ፡ ለጥበቃውም ፡ ይሆናሉ ፡ ብለን ፡ የመደብናቸው ፡ እነዚህን ፡ ሁሉቱን ፡ የአርበኛ ፡ መሪዎች ፡ ነበር ።

ታዎች ፡ ሰላሳ ፡ ፴ ፡ ጅራፍ ፡ ተገርፈው ፡ እጃቸውን ፡ ለፊታውራሪ ፡ ኃይለ ፡ ኢየሱስ ፡ ሹም ፡ ተላልፎ ፡ አንዳንድ ፡ ወር ፡ ታሥረው ፡ እንዲለቀቁ ፡ አደረ ግሁ ፡ ከነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ በምርመራ ፡ ያገኘሁት ፡ ወደ ፡ ፊታውራሪ ፡ ኃይለ ፡ ኢየሱስ ፡ የተላከውን ፡ ደብዳቤ ፡ ነጥቆ ፡ የቀደደው ፡ ተፈራ ፡ ብሩ ፡ የሚ ባለው ፡ አገሩ ፡ ብር ፡ ብጥ ፡ ሚካኤል ፡ ጭቃው ፡ አዳሙ ፡ መሸሻ ፡ የጎ በዝ ፡ አለቃው ፡ ዓለሙ ፡ መሸሻ ፡ ያገሩ ፡ ሹም ፡ ፊታውራሪ ፡ ዘለቀ ፡ ደስታ አገር ፡ አሰዋ ፡ ነው ፤ ብለው ፡ እነዚህ ፡ የተገረፉት ፡ ሰዎች ፡ መስክረዋ ልና ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ተፈልጐ ፡ እንዲያዝ ፡ አስታውሳለሁ ። ከዚህ ፡ ወዲ ያም ፡ መንገዳችንን ፡ ቀጠልን ። የመንገዱም ፡ አካሄድ ፡ ማርቆስ ፡ የሚ ሄደውን ፡ ዋናውን ፡ የባቡር ፡ መንገድ ፡ ወደቀኝ ፡ እየተውን ፡ ደግሞ ፡ በሚባለው ፡ አገር ፡ አልፈን ፡ ላይ ፡ ዳሞት ፡ ማርያም ፡ ከሚባለው ፡ ቦታ ፡ በ፰ ፡ ሰዓት ፡ ደርሰን ፡ ሠፈር ፡ ሆነ ፡ ከዚያው ፡ እንደሰፈርን ፡ ጥቂት ፡ ቆይተን ፡ ከአማኑኤል ፡ ወዲህ ፡ ባለው ፡ ጠላት ፡ የኛ ፡ አርበኞች ፡ አደጋ ፡ ጣሉ ፡ ተኩስም ፡ ስንሰማ ፡ በጣም ፡ የተሟሟቀ ፡ ሆነ ። ከምሽቱም ፡ እስከ ፡ ፪ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ሲታኰስ ፡ ቆዩ ። ግን ፡ ሌሊቱን ፡ ተኩሱ ፡ ሳያቋርጥ ፡ አደረ ፡

በማግሥቱ ፡ መጋቢት ፡ ፲፯ ፡ ማክሰኞ ፡ ጧት ፡ ከፊታውራሪ ፡ አቤቶ ፡ ተገናኘሁ ፡ ወዲያው ፡ ጉዞ ፡ አድርገን ፡ ጂብዬ ፡ ከሚባለው ፡ ቦታ ፡ ፊታ ውራሪ ፡ ገበየሁንና ፡ ፊታውራሪ ፡ አከለው ፡ ባለህን ፡ ተገናኘቼ ፡ ያገሩን ፡ አኳኋን ፡ በዝርዝር ፡ ተነጋገርኩ ፡ ከፊታውራሪ ፡ አከለው ፡ ባለህ ፡ የተ ገኘው ፡ ያገር ፡ አኳኋን ፡ ወሬ ፤ ባለፈው ፡ ቅዳሜና ፡ ሰኞ ፡ ለት ፡ ማርቆስ ፡ አውሮፕላን ፡ ቦምብ ፡ ጣለ ። ከጠላትም ፡ የጎዳው ፡ የቅዳሜ ፡ እለቱ ፡ ፲፯ ፡ ሰው ፡ የሰኞ ፡ ለታውም ፡ ስምንት ፡ ኢጣልያኖች ፡ ገደለ ፡ አለ ፤ ፪ኛ ፡ በማ ርቆስ ፡ ያለውም ፡ ጠላት ፡ ከተማውን ፡ ለቆ ፡ በማርቆስ ፡ አካባቢ ፡ ባለው ፡ አገር ፡ ዙሪያ ፡ በም ዕራብ ፡ በኩል ፡ የመቃ ፡ ከሚባለው ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ምሽግ፡ ሠርቶ ፡ መድፍ ፡ ጠምዷል፡ አለ ፤ በደቡብም ፡ በኩል ፡ በተራራው፡ ላይ ፡ ሰፍሯል ፤ በምሥራቅም ፡ እንድማጣ ፡ ላይ ፡ ሰፍሯል ፤ በሰሜንም ፡ ገጽ ፡ አብማ ፡ አንድ ፡ በጦሎኒ ፡ ሰፍሯል ፡ አሉ ፤ ፫ኛ ፡ ካማኑኤልም ፡ እስከ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ከሚሄደው ፡ ጎዳና ፡ በጠላት ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ለመ ጣል ፡ የሚመቹ ፡ ቦታዎች ፡ ፊታውራሪ ፡ አከለው ፡ አታንበሳ ፡ በሚባ ለው ፡ ሥፍራ ፡ ቀርቦ ፡ እንዲሠራ ፡ ይቻላል ፡ ፊታውራሪ ፡ ገበየሁ ፡ ግሞ ፡ በሚባለው ፡ አገር ፡ ቁልጭ ፡ ወንዝ ፡ ትልቅ ፡ ዱር ፡ አለበት ፡ ስለተባለ ፡ እዚያ ፡ ላይ ፡ ጦሩን ፡ አከቶ ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል ፤ በዚሁ ፡ ግምባር ፡ ከወደ ደቡብ ፤ በኩል ፡ የውላ ፡ የሚባለውን ፡ ዱር ፡ ይዞ ፡ ፊታውራሪ ፡ እጅጉ ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል ፡ አሉ ፤ ፊታውራሪ ፡ አቤቱም ፡ በግምባሩ ፡ የሚመቸው ፡ ዱር ፡ በደልማ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ በኩል ፡ ጫካው ፡ ለሥራ ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ አለ ፤ በጎዛንም ፡ በኩል ፡ ድጅል ፡ የሚባለው ፡ ወንዝ ፡ ቦታው ፡ ጫካ ፡



አለው ፡ በዚያ ፡ ቢቀርብ ፡ ለሥራ ፡ ይመቻል ፡ አለ ፤ ፬ኛ ፡ ራስ ፡ ኃይሉም ፡ ከማርቆስ ፡ በስተ ፡ ደቡብ ፡ በኩል ፡ ወዳለው ፡ አገር ፡ በጎዛምን ፡ አፈር ፡ የሸመንድ ፡ ከሚባለው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ቀን ፡ ቀን ፡ እየዋሉ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ማርቆስ ፡ ይገባሉ ፡ አሉ ፤ ፭ኛ ፡ ትላንት ፡ ማታ ፡ ፲፭ ፡ መጋቢት ፡ የኛ ፡ ሰዎች ፡ ከአማኑኤል ፡ ወዲህ ፡ የንጭ ፡ ከሚባለው ፡ ቦታ ፡ በሰፈረው ፡ ጠላት ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ሲወድቅበት ፡ እዚያው ፡ ከጠላት ፡ ዘንድ ፡ የነበ ረች ፡ አምልጣ ፡ የመጣች ፡ ኀለሚቱ ፡ በፈቃዱ ፡ የምትባል ፡ ሴት ፡ ያመ ጣችው ፡ ወሬ ፤ ከጠላት ፡ ወገን ፡ በትላንትናው ፡ ማታ ፡ ጦርነት ፡ ፩ ፡ ማብ ጣን ፡ ፩ ፡ ሰንጀርቴ ፡ ፳፰ ፡ የጥቁር ፡ ወታደር ፡ ሞተ ፡ ፲፱ ፡ የጥቁር ፡ ወታ ደር ፡ ቆሰለ ፡ ፲፫ ፡ የከምባታ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ ከነመሣሪያው ፡ ከድቶ ፡ ወጣ ፡ አማኑኤልም ፡ ከሠፈረው ፡ ጠላት ፡ ፫ ፡ በጦሎኒ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመለሰ ፡ ፩ ፡ ቦጦሎኒ ፡ እዚያው ፡ አለ ፡ ከአማኑኤል ፡ ወዲህ ፡ ትላንት ፡ ጦርነት ፡ ከተደረገበት ፡ ፫ ፡ በጦሎኒ ፡ አለ ፡ ከጠላትም ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ጥቁር ፡ የሸዋ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ አለች ። የኔም ፡ ባል ፡ የከምባታ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ ትላ ንት ፡ ቆሰለ ፡ ብላ ፡ ተናገረች ፡ ጦርነቱም ፡ ሲጀመር ፡ ኢጣልያ ፡ እሳቡን ፡ የጣለ ፡ መስሎ ፡ ከወታደሩ ፡ ጋር ፡ ኳስ ፡ ሲጫወት ፡ ነው ፡ አለች ፡ ደጃዝ ማች ፡ ማሞም ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሄደ ፡ አለች ።

እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ከፊታውራሪ ፡ ገበየሁ ፡ ወልዴ ፡ ማርያም ፡ የተ ገኘ ፡ ወሬ ፤ ፩ኛ ፡ ኰሎኔል ፡ ናታላ ፡ ከምዕራብ ፡ ጎጃም ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ ሸ ሽቶ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ የገባውን ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ እኛን ፡ ያመንክ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ሁን ፡ አይዞህ ፡ በተቀር ፡ አገር ፡ መግባት ፡ ያማረህ ፡ መሣሪያ ህን ፡ ፈቅደንልሀልና ፡ ይዘህ ፡ ሂድ ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ ቆርጦ ፡ ካስናበተው፡ በኋላ ፡ ጀኔራል ፡ ናዚ ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ መጥቶ ፡ ኰሎኔል ፡ ናታላና ፡ ማጆ ር፡ ደበበን ፡ ቡሬንና ፡ ደምበጫን፡ እየለቀቃችሁ፡ የመጣችሁት፡ ወዴት ፡ ልትደርሱ ፡ ነው ፡ ሮማ ፡ ከዚህ ፡ ከምታዩት ፡ ሰማይ ፡ ርቋል ፡ ምን ፡ መ ድረሻ ፡ አላችሁ ፡ ብሎ ፡ ፪ቱንም ፡ ሸሮ ፡ አሠራቸው ፡ አለ ፤ ስለዚህ ፡ ከ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ የሸሸውን ፡ ጦር ፡ እንደገና ፡ መልሶ ፡ በአማኑኤልና ፡ ከ አማኑኤልም ፡ ወዲህ ፡ የንጭ ፡ ከሚባለው ፡ ቦታ ፡ አሰፈረው ፡ አለ ።

፪ኛ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ የሚያስወሩት ፡ ወሬ ፡ የወሎ፡ ሕዝብ ፡ ጃንሆይን ፡ አይወድምና ፡ ከሸዋና ፡ ከያለበት ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ሊመጣ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ያስወራሉ ፡ አሉ ፤ ፫ኛ/ አብማ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ጠላት ፡ መጋቢት ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ሌሊት ፡ ገብተው ፡ ፩ኛ ፡ ሰዎች ፡ ቦምብ ፡ ጥለው ፡ ፫ ፡ ኢጣልያኖች ፡ ገደሉ ፡ አለ ፤ ፬ኛ/ ልጅ ፡ አያሌው ፡ ገሠሠ ፡ የሚባለው ፡ ከጠላት ፡ መለዮ ቱን ፡ የሚያስረዳ ፡ ደብዳቤ፡ አሳይቶኛል ፡ በቀጥታ፡ ከግርማዊነታቸውም፡ ደብዳቤ ፡ ቢጻፍለት ፡ ለማድረሱና ፡ የሱንም ፡ ሃሳብ ፡ አውቀዋለሁ ፡ ይወ ጣል ፡ አለ ፤ ፭ኛ/ ከፊታውራሪ፡ አከለው፡ ጋር ፡ ያለፈውን ፡ ጠባቸውን ፡ ትተው ፡ ተስማምተው ፡ ባንድ ፡ ሆነው ፡ ያቀረቡት ፡ ሃሳብ ፡ ከጠላት ፡

ስለሚለየው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሰው ፡ ከነመሳሪያው ፡ ሕይወቱን ፡ እየጠበ ቅን ፡ ወደሚፈልግበት ፡ ቦታ ፡ እንድናደርሰው ፡ የማዘገር ፡ ደብዳቤ ፡ ያስ ፈልገናል ። ከትእዛዝ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በሀገራችን ፡ ፩ ፡ ሰው ፡ መሣሪያውን ፡ ተቀምቶና ፡ ተገላልቶ ፡ ቢገኝ ፡ የጃንሆይን ፡ ትእዛዝ ፡ መጣስ ፡ ነውና ፡ ከፉ ፡ የተሠራበት ፡ አገር ፡ እንዲቀጣ ፡ እናደርጋለን ፡ ብለው ፡ እንታዘዝ ፡ ብለዋል ፤ ጠላትንም ፡ በአደጋም ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ለማጥቃት ፡ ባዘሁን ፡ እንሠራለን ፡ አሉ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ አታንበሳ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ከሚባለው ፡ ቦታ ፡ ሠፈር ፡ ሆነ ።

በማግሥቱም ፡ መጋቢት ፡ ፲፯ ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ ጉዞ ፡ እንደጀመርን ፡ ከፊታውራሪ ፡ ገበየሁ ፡ ጋር ፡ ተገናኝተን ፡ ከራስ ፡ ኃይሉ ፡ ከድተው ፡ የመጡ ፡ ሰዎች ፡ ባሻ ፡ አቦዘንና ፡ ባላምባራስ ፡ እልምነህ ፡ ከሚባሉት ፡ አርባ ፡ ሰባት ፡ ባለብረት ፡ ሆነው ፡ መጋቢት ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ መጥተው ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ አሉ ፡ ብሎ ፡ አቀረባቸው ፡ ወዲያው ፡ ጉዞአችንን ፡ ቀጥለን ፡ ገሞ ፡ መሬት ፡ ጎዶብ ፡ የሚባለውን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግረን ፡ ጥቂት ፡ አርፈን ፡ በ፰ ፡ ሰዓት ፡ በማርቆስ ፡ አቅራቢያ ፡ ካለው ፡ ዋናው ፡ ጦራችን ፡ እሠፈረበት ፡ ደረስን ። ከጦሩም ፡ ተገናኘን ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ኰሎኔል ፡ ዊን ጌት ፡ ወደ፡ደምበጫ ፡ ደርሰው ፡ በዚያ ፡ ክፍል፡ ካለው ፡ ጦር ፡ ተገናኝተው፡ ወዲያው ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ለመገናኘት ፡ መምጣታቸውን ፡ ስማሁ ፡ እኔም ፡ እዚህ ፡ ካሉት ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ጋር ፡ ሆኜ ፡ ወደፊት ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ተዘጋጅቼ ፡ እጠባበቃለሁ ። ልጅ ፡ ዓለማየሁ ፡ ቦጋለ ፡ የሚባለው ፡ ከኛ ፡ የተላከው ፡ ሰው ፡ እዚህ ፡ ደርሶ ፡ ልጅ ፡ ማሞ ፡ ኃይለ ፡ ሚካኤልን ፡ ስላላገኘው ፡ የጻፈልንን ፡ ቃልና ፡ ፊታውራሪ ፡ አበራ ፡ ተስ ፋዬ ፡ የሚባለው ፡ የደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ያንድ ፡ ክፍል ፡ የጦር ፡ ሹም ፡ የጻፈልኝን ፡ ደብዳቤ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ልኬዋለሁ ፡ ልጅ ፡ አያሌው ፡ ገሠ ሠን ፡ በቶሎ ፡ ለመገናኘት ፡ ፈልጌአለሁ ። ምክንያቱም ፡ በግንደበረት ፡ በኩል ፡ የሸዋን ፡ በር ፡ ለማገናኘት ፡ የሚቻል ፡ ስለመሰለኝ ፡ ነውና ፡ ለሱም ፡ ለግንደበረት ፡ ባላባቶችም ፡ ደብዳቤው ፡ በቶሎ ፡ ተጽፎ ፡ ይላ ከልኝ ፤ የግንደበረት ፡ ባላባቶች ፡ ወረቀት ፡ የሚጻፍላቸውን ፡ ስማቸውን ፡ ከዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ጋር ፡ ጽፌአለሁ ።

መጋቢት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
ያለሐኬት ፡ ባሬያም ፡
ከበደ ፡ ተሰማ ።

ይህ ፡ የኔ ፡ ራፖር ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ዘንድ ፡ ደርሶ ፡ ከታዩ ፡ በኋላ ፡ በመጋቢት ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ የተጻፈ ፡ የግርማዊነታቸው ፡ የሥራ ፡ መም ሪያ ፡ ደረሰኝ ፡ ቃሉም ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።



## የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጠቅላይ ፡ መሪ ፡ ማኅተም ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።
ይድረስ ፡ ከአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፤

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና ፡ ነን ፤ መጋቢት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ የጻፍከው ፡ ዝርዝር ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰን ። በዚያ ፡ በኩል ፡ ያለውንም ፡ አኳሆን ፡ በመልካም ፡ የሚያስረዳ ፡ በመ ሆኑ ፡ ደስ ፡ አለን ፤ እኛም፡ ወሬህ ፡ ስለዘገየብን ፡ ከበደ ፡ ሐጎስን ፡ ደብ ዳቤ ፡ አስይዘን ፡ ልከነው ፡ ነበር ፡ እስካሁን ፡ አልተመለሰም ፤ ደብዳቤ ህም፡ ከደረሰን፡ በኋላ ፡ ሳያገኝህ ፡ በመቅረቱ ፡ መሆኑን ፡ ተረዳን ፤ ፩ኛ ፡ የደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፡ ጦር ፡ በዚያ ፡ የማያስፈልግ ፡ በመሆኑ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ እንዲዘምት ፡ ላሳሰብኸው ፡ አሁን ፡ ወደዚያ ፡ ወደ ፡ ደንበጫ ፡ ለመምጣት ፡ ሰዎቹም ፡ ስለተነሱ ፡ እኛም ፡ ወደዚያው ፡ መም ጣታችን ፡ ስለሆነ ፡ በዚያው ፡ ብንነግረው ፡ ይሻላል ፡ ብለን ፡ አቆይተነ ዋል ፤ ፪ኛ ፡ ባንዳውም ፡ በየቀኑ ፡ እየከዳ ፡ የሚገባው ፡ እየበዛ ፡ መሄዱን ፡ ሰማን ። ይህም ፡ ለሥራችን ፡ በጣም ፡ የሚረዳ ፡ ነው ፤ ገበየሁ ፡ ወልደማ ርያም ፡ ደብዳቤ ፡ጽፎልን ፡ ደረሰን ፤ ባንዳውን ፡ ተፋላሚ ፡ ስለበዛበት ፡ ለመረጠው ፡ አርበኛ ፡ እንዲገባ ፡ በአዋጅ ፡ ይነገርለት ፡ ብሎ ፡ ስላስታ ወሰ ፡ አዋጁን ፡ በአምስት ፡ ላይ ፡ ጽፈን ፡ ልከናልና ፡ የጦር ፡ አለቆቻ ችን ፡ እንዲያስነግሩለት ። ለገበየሁ ፡ ሰጥተኸው ፡ ከጣላት ፡ ጋራ ፡ ያለ ውም ፡ ባንዳ ፡ እንዲያውቀው ፡ እንዲያደርግ ፡ አምስት ፡ ላይ ፡ ተጽፎ ፡ ተልኮልሃል ፤ ወደርሱም ፡ የተጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ ተልኮልሃልና ፡ እንዲ ደርሰው ፡ አድርግ ። ፫ኛ ፡ በመንገድህ ፡ ላይ ፡ ያገኘኸውንና ፡ ያደረግኸ ውን ፡ ስለጻፍክልን ፡ ተመልክተነዋል ፤ በመንገድ፡ እያደፈጡ፡ የወስላታ ነት ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩት ፡ ቅጣታቸውን ፡ ስላገኙ ፡ መልካም ፡ ሆኖአል ፤ ተፈራ ፡ ብሩ ፡ የተባለውም ፡ በአሰዋ ፡ ተፈልጎ ፡ እንዲያዝ ፡ አገሩ ፡ የበ ለቀ ፡ ደስታ ፡ ስለሆነ ፡ ነገሩም ፡ ብርቱ ፡ ጥፋት ፡ ነውና ፡ በኛ ፡ ቃል ፡አስ ታውቀኸው ፡ እንዲያስይዝ ፡ ይሁን ፤ ኰሎኔል ፡ ዊንጌትም ፡ ወደዚያ ፡ ለመምጣት ፡ ዛሬ ፡ ተነስተዋል ። መጋቢት ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም፡ በዋና ፡ ጦር ፡ ሠፈር ፡ ተጻፈ ።

ወደ ፡ ግንደ ፡ በረት ፡ የተጻፈ ፡ ፰ ፡ ደብዳቤ ፡ ለብቻው ፡ አንድ ፡ እንቦልጕ ፡ ሆኖ ፡ ተልኰልሃል ።

በመጋቢት ፡ ወር ፡ የተጻፈው ፡ የግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ደብዳቤ ፡ ከደረሰኝ ፡ በኋላ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ የሥራ ፡ መግለጫ ፡ ራፖር ፡ አስተ ላለፍሁ ።

ለግርማዊ ፡ ጌታዬ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ዕድሜ ፡ ከጤና ፡ አስተባብሮ ፡ ይስጥልኝ ፡ እያ ልኩ ፡ ባረያዎ ፡ መሬት ፡ እስማለሁ ።

በመጋቢት ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ የተጻፈ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ደብዳቤ ፡ በዚሁ ፡ ወር ፡ በ፳፩ ፡ ቀን ፡ ደረሰኝ ፤ ግርማዊ ፡ ሆይ ፡ እኔም ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ተለይቼ ፡ ከደምበጫ ፡ እስከ ፡ አለንበት ፡ ቦታ ፡ ያለውን ፡ አኳኋን ፡ መጋ ቢት ፡ ፲፰ ፡ ቀን፡በተጻፈ፡ ደብዳቤዬ፡ አመልክቻለሁ፡አሁን፡ ከዚያ፡ ወዲህ፡ በጦሩ ፡ አካባቢ ፡ እየዞርን ፡ በየለቱ ፡ አደጋ ፡ ከመጣል ፡ አልቦዘንም ፡ የጠላትም ፡ ጦር ፡ ከምሽጉ ፡ ወ ስጥ ፡ ሊወጣ ፡ አይችልም ፡ እኛም ፡በጣም ፡ እየቀረብን ፡ ስንመረምርና ፡ ስንገምት ፡ ነው ፡ ውሎና ፡ አዳራችን ። እንደ መረመርነውና ፡ እንዳገኘነውም ፡ በአማኑኤልና ፡ በጉሊት ፡ ያለው ፡ የጦር ፡ ብዛት ፡ ፬ ፡ ባታሎን ፡ ነው ፡ ይባላል ፡ እማርቆስ ፡ ግን ፡ ያለው ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ነው ፡ አሉን ፤ ይህንኑም ፡ ለማስረገጥ ፡ ጦር ፡ አለ ፡ በየተ ባለበት ፡ ሠፈር ፡ እማርቆስ ፡ ውስጥ፡ ሦላሳ ፡ ያህል ፡ ወታደሮች ፡ ገብ ተው ፡ አደጋ ፡ እንዲጥሉ ፡ አድርገን ፡ ነበር ፡ ገብተው ፡ አደጋ ፡ ሲጥሉ ፡ መትረየስም ፡ መድፍም ፡ አልተኩሱባቸውም ። የእጅ ፡ ጠመንጃና ፡የእጅ፡ ቦምብ ፡ ብቻ ፡ ተኰሱባቸው ። የኛም ፡ ሰዎች ፡ ከአደጋ ፡ ተጠብቀው ፡ በደህና ፡ ተመልሰው ፡ መጥተዋል ። አሁንም ፡ ወደፊት ፡ ልናደርገው ፡ ያሰብነው ፡ ጦርነት ፡ እንዲሁ ፡ በሽፍትነት ፡ አደጋ ፡ እየጣልን ፡ ለመሥ ራት ፡ ነው ።

ራስ ፡ ኃይሉም ፡ ያሉበትን ፡ ቦታ ፡ እያስመረመርኩ ፡ ከጠላት ፡ጋር ፡ ያለ፡ ሃሳባቸውን፡ ለውጠው ፡ ከእኛ ፡ የማይተባበሩ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ እን ደዚሁ ፡ አደጋ ፡ ላስጥልባቸው ፡ አስባለሁ ። ለዛሬም ፡ የማርቆስን ፡ አኳ ሆን ፡ ለመመርመርና ፡ አደጋ ፡ ለመጣል ፡ የኔን ፡ ሰዎች ፡ መሪ ፡ ጨምሬ ፡ ፲፫ ፡ ወታደሮች ፡ ልኬአለሁ ፡ በደህና ፡ ሠርተው ፡ እንዲመለሱ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ፡ ወደራስ ፡ ኃይሉም ፡ ልካቸውን ፡ ለማስገመት ፡ ከኔ ፡ ሰዎች ፡ መል ክተኛ ፡ አድርጌ ፡ ይኸው ፡ ዛሬ ፡ ልልክ ፡ ነውና ፡ መልክተኞቹ ፡ ደርሰው ፡ ሲመለሱ ፡ የተገኘውን ፡ ወሬ ፡ አጥርቼ ፡ እጽፋለሁ ፡ በአካባቢውም ፡ ያለው ፡ ባንዳ ፡ ከውስጥ ፡ ያለው ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ እየከዳ ፡ ለመውጣት ፡ ስለጠየቀ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ እረፍልኝ ፡ ስላሉኝ ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ መሄዴን ፡ አቁሜ ፡ ይኸን ፡ ለመሥራት ፡ አስቤአለሁ፤



በየቦታው ፡ ግን ፡ የኔን ፡ ሰዎች ፡ እየሰደድኩ ፡ አደጋ ፡ እንዲጥሉ ፡ ለማ ድረግ ፡ አልቦዘንም ፡ የረዳቶቻችን ፡ ጦር ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው ፤ እነዚ ህም ፡ ሌትም ፡ ቀንም ፡ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ ከመዘዋወር ፡ የተነሳ ፡ ሊደክሙ ፡ ነው ። እንዲያውም ፡ ብቻ ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሳ ፡ መበሳጨት ፡ ጀም ረው ፡ ነበር ። ለዚሁ ፡ ጉዳይና ፡ ከብርጋዴዮር ፡ ሳንድፎርድ ፡ ጋር ፡ በሥራ፡ አኳሆን ፡ ስላልተስማሙ ፡ ኰሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ ተግርማዊነትዎ ፡ እነጋግ ራለሁ ፡ ብለው ፡ ሄደዋል ፡ ብሎ ፡ አቶ ፡ መኰንን ፡ ደስታ ፡ ነገረኝ ፡ በእግ ዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ተጠብቋል ፡ እንጂ ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ቢከታተለን ፡ ለማምለጥ ፡ ወይም ፡ ለመመለስ ፡ እንደማምቱ ፡ የሚቻል ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ እንዲደፍሩ ፡ አላደረጋቸ ውም ፤

እደንበጫ ፡ ግን ፡ ከሰው ፡ እንዳገኘሁት ፡ ዱቄትና ፡ ሩዝ ፡ አለ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከኬንያ ፡ የመጡ ፡ የረዳቶቻችን ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ስለሆኑ ፡ የያዙት ፡ ዝርዝሩን ፡ ሊነግሩኝ ፡ አልቻሉም ። ከእኔ ፡ ጋር ፡ ስለማንተዋ ወቅ ፡ አስገድጄ ፡ ለማወቅ ፡ አልደፈርኩም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ለማወ ቅና ፡ ለሥራውም ፡ ተጨማሪ ፡ ሰው ፡ ለማድረግ ፡ ከብሪጋዴዮር ፡ ሳንድ ፎርድ ፡ በጉን ፡ ማስጠየቅ ፡ ይሻል ፡ ይመስለኛል ። እሳቸው ፡ ሁሉንም ፡ ሊነግሩ ፡ ይችላሉ ። እዚህ ፡ እንደደረስኩ ፡ ከግንደበረት ፡ የመጣ ፡ ሰው ፡ አግኝቼ ፡ እንደሰማሁት ፡ በግንደበረት ፡ ካሉት ፡ ሽፍቶች ፡ በውነት፡ የጃ ንሆይን ፡ መምጣት ፡ አጥርቶ ፡ ጠይቆ ፡ ለማስረዳት ፡ የመጣውን ፡ ሰው ፡ አግኝቼ ፡ እሱ ፡ ወደዚያ ፡ ቸኩሎ ፡ ስለሄደ ፡ አስፈላጊውን ፡ በማስታወሻ ፡ አቶ ፡ ገብሬ ፡ ይዞ ፡ መጥቷልና ፡ በቶሎ ፡ ተነጋግሮ ፡ መልሱን ፡ ይዞ ፡እን ዲመጣልኝ ፡ የሚቻል ፡ ቢሆን ፡ እኔም ፡ ለመቅረብ ፡ አስቤአለሁ ፡ የጠ ላት ፡ መድፍ ፡ የሚተኰሰው ፡ ግን ፡ የኛ ፡ ጦር ፡ እንዳይቀርበው ፡ በሩቅ ፡ ለመከላከል ፡ ነው ፤ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ያሉት ፡ ቀድሞ ፡ የኢጣልያ ፡ ቆንስል ፡ እነበረበት ፡ ቤት ፡ ነው ፡ ንዛቸውን ፡ ቀፈያ ፡ ወደምትባል ፡ አገር ፡ አሸሽ ተው ፡ በዋሻ ፡ አግብተዋል ። የመኳንንቱንም ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ በያገራችሁ ፡ ቆዩ ፡ እያሉ ፡ አሰናበቱት ፡ ይባላል ፤ በማርቆስ ፡ አካባቢ ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ አለበት ፡ ፩ ፡ ዳሊገው ፡ ፩ ፡ ጨሞጋ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ፩ ፡ አብማ ፡ እፊታ ውራረ ፡ ገበየሁ ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ ፩ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ የወትሮው ፡ ምሽግ ፤ አራት ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ማርቆስ ፡ እመጠጥ ፡ ቤት ፡ ወታ ደሮች ፡ ሲጫወቱ ፡ የተሰማ ፡ ወሬ ፤ የአዲስ ፡ አበባው ፡ ገገር ፡ እዚያው ፡ ተዋጉ ፡ እንጂ ፡ ወደዚህ ፡ እንመጣለን ፡ ለማለት ፡ እንዳታስቡ ፡ ወደዚህ ፡ እንመጣለን ፡ ብሎ ፡ ከማሰብ ፡ እሰማይ ፡ እወጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ማሰብ ፡ይቀ ላል ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ ተላልፎአል ፡ ቢለው ፡ ይህ ፡ ቅርናታም ፡ እኛን ፡ ሊያስፈጅ ፡ ነው ፡ መውጫ ፡ አጥተን ፡ ነበር ፡ ያደርገው፡እንጂ ፡ መሣሪያ ችንን ፡ ይዘን ፡ እንከዳለን ፡ እየተባባሉ ፡ ይነጋገሩ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ነገረኝ ።

የኰሎኔል ፡ ናታላን ፡ መሻር ፡ ባለፈው ፡ ማመልከቻ ፡ ጽፌአለሁ ፤ በሱም ፡ ሥራ ፡ የተሾመው ፡ ኰሎኔል ፡ ማራቢታኖ ፡ ያለበት ፡ አማኑኤል ፡ ምሽግ ፡ ነው ፡ አሉ ፤ ከልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀና ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ እንዲሠሩ ፡ ካዘዝናቸው፡ ሠራተኞች ፡ ዘንድ ፡ የደረሰኝን ፡ ደብዳቤ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ልኬአለሁ ።

መጋቢት ፡ ፳፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
ያለሐኬት ፡ ባሪያዎ ፡
ከበደ ፡ ሰተማ ።

ቀጥሎ ፡ ያለውም ፡ ደብዳቤ ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ወደኔ ፡ ልከ ውት ፡ የነበረ ፡ ከራፖሩ ፡ ጋር ፡ አያይዤ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ያስተ ላለፍሁት ፡ ነው ።

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ አባቴ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፤

የማክበር ፡ ሰላምታ ፡ አቀርባለሁ ፤ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡እኔ ፡ ደህና ፡ ነኝ ፡ ምንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይልና ፡ በግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ኀብት ፡ የተጀመረው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ . እየተስፋፋ ፡ ከላያችን ፡ የጠላትን ፡ ቀምበር ፡ ሊአበርልን ፡ ስለሆነ ፤ አሁን ፡ በመጋቢት ፡ ወር ፡ ካፒቴን ፡ ቴሰ ንጀርና ፡ ካፒቴን ፡ ፎሊ ፡ ሊፍተናንት ፡ ካላርክና ፡ ልጅ ፡ መርዕድ ፡ መን ገሻ ፡ ጭምር ፡ ወደኔ ፡ ለሥራ ፡ ታዘው ፡ ስለመጡ ፡ ደኅው ፡ እኔም ፡ጦሩን ፡ አስከትቼ ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ሥራዬን ፡ ልሠራ ፡ በዙሪያው ፡ ጠላት ፡ ያለበ ትን ፡ ሁሉ ፡ አስከብቤ ፡ እጠባበቃለሁ ። መድፍና ፡ መትረየስ ፡ ጥይት ፡ በያይነቱ ፡ ሆኖ ፡ መሣሪያ ፡ ጭምር ፡ ካፒቴን ፡ ቴሰንጀር ፡ ድረስ ፡ ቢመ ጣልኝ ፡ በዓባይ ፡ በረሃ ፡ ሁሉ ፡ ጦር ፡ እያዘጋጀሁ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ እችላለሁ ። በማዶ ፡ በቦረና ፡ ከነኃይሌ ፡ ሮባ ፡ ጋራም ፡ ተላልኬ ፡ መን ገድ ፡ እንዲከፈት ፡ ለማድረግ ፡ ታርቂ ፡ ብዙ ፡ የግርማዊ ፡ ጃንሆይን ፡ ጎጃም ፡ መሬት ፡ ስለመግባታቸው ፡ እሚያስረዳውን ፡ ደብዳቤ ፡ በያይ ነቱ ፡ ለነኃይሌ ፡ ሮባ ፡ ሰድጄ ፡ ቦረና ፡ ከነበረው ፡ ቲሊኒቲም ፡ ወረቀት ፡ ተላልኬአለሁ ፡ ሁሉንም ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ታዘው ፡ ወደኔ ፡ ከመ ጡት ፡ ካፒቴኖች ፡ ዘንድ ፡ ይሰሙታል ፤ ግን ፡ በጎጃም ፡ የቆዩ ፡ ባላባ ቶችና ፡ መኳንንቶች ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ ጠላት ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ለማድረግ ፡ ስለተቃወማቸው ፡ ለራሳቸው፡ መጠበቂያ፡ ብለው ፡ የሠሩትን፡ አሁን ፡ ላንድነትና ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ታሪክና ፡ ክብር ፡ እያደረጉ ፡ ቢያስወሩ ፡ ሁሉም ፡ የጠላት ፡ ሹም ፡ መሆኑን ፡ ሰምተውታል ፤ ስለዚህ ፡ እኔን ፡ በምቀኝነት ፡ ይጣሉኛል ፡ ብቻ ፡ የኔን ፡ ድካም ፡ እንዳይረሱት ፡ ለክቡርነትዎ ፡ አስታውሳለሁ ።

መጋቢት ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
በላይ ፡ ዘለቀ ፡



ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ የኔ ፡ ራፖርና ፡ የልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ደብዳቤ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ዘንድ ፡ ደርሶ ፡ ከታየ ፡ በኋላ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ መልስ ፡ ተጻፈልኝ ።

## የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ፤

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ፡ ከአባቸር ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፤

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና፡ ነን ፡ መጋቢት ፡ ፳፭ ፡ ቀን ፡ በነከበደ፡ ሐጎስ፡ እጅ ፡ የላክኸው ፡ ደብዳቤ፡ ደርሶአል ፡ ከበደ ፡ ሐጎስን ፡ የላክነው ፡ አስቀድሞ ፡ ወሬህ ፡ ስለጠፋብን ፡ ነው ፤ በዚህም ፡ ደብዳቤህ ፡ ስለ ፡ ጻፍከውና ፡ አብሮ ፡ ስለተላከው ፡ የበ ላይ ፡ ዘለቀ ፡ ወረቀት ፤ ከኃይሌ ፡ ሮባ ፡ መላላክ ፡ ከቻለ ፡ ለርሱ ፡ የተጻፈ ለትን ፡ ደብዳቤ ፡ ልከንልሃል ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ መላክተኛህ ፡ ገብሬ ፡ ለግንደበረትና ፡ ለሜጫ ፡ ለሜታ ፡ እንዲጻፍ ፡ ያስፈልጋል ፡ ብሎ ፡ በአ ንተ ፡ ስም ፡ ላመለከተው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተጽፎ ፡ ተልኮልሃል ።

መጋቢት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
በዋና ፡ ጦር ፡ ሠፈር ፡ ተጻፈ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፬ ።

## ስለ ፡ አገሩ ፡ ፍቅር ፡ ከኢጣሊያኖች ፡ ከድቶ ፡ የመጣ ፤ ባንዳ ፡ እንዳይጉላላ ፡ የተነገረ ፡ አዋጅ ፤

በኢጣልያኖች ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ ባንዳ ፡ ከካምፕ ፡ ሲመጣ ፡ አርበኞች ፡ እንደ ፡ ምርኮኛ ፡ በማድረግ ፡ መሣሪያውንም ፡ ገንዘቡንም ፡ መግፈፍና ፡ ማጉላላት ፡ ጀምረው ፡ ነበር ፤ ይህንንም ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ስለ ፡ ሰሙ ፡ ለአርበኞቻቸው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ትእዛዝ፡ እንዲደርስ፡ አደረጉ ።

### የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ።

ለኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡

ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ወይም ፡ ከያለበት ፡ ስለ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማው ፡ ክብር ፡ ስለ ፡ አገሩም ፡ ፍቅር ፡ የሚወጣው ፡ በኢጣልያ ፡ ውስጥ ፡ የነበረ ፡ ባንዳ ፡ እየወጣ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ እወደደበት ፡ አርበኛ ፡ ዘንድ ፡ እየገባ ፡ በየበኩልህ ፡ በመልካም ፡ እየተቀበልህ ፡ አቅርበው ፡ እንጂ ፡ እየተፋለምህ ፡ እንዳታጉላላው ፡ እንዳትገፈው ፡ ይሁን ። እየገፈፍህ ፡ መንገድ ፡ እያሳጣህ ፡ ያስቸገርህ ፡ እንደሆነ ፡ ከትእዛዝ ፡ መውጣት ፤ ለጠላት ፡ መርዳት ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠርብሃል ።

መጋቢት ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መጋቢት ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ሐሙስ ፡ ደንበጫ ፡ ገብተው ፡ የጦር ፡ ሠፈራቸውን ፡ ከዚያ ፡ አደረጉ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተላከው ፡ የሥራ ፡ መምሪያ ፡ ደብዳቤ ፡ ደረሰኝ ፡ ይኸውም ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።



## የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጠቅላይ ፡ መምሪያ ፡ ማኅተም ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡

ይድረስ ፡ ከአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፤

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና ፡ ነን ፤ እኛም ፡ አሁን ፡ ሐሙስ ፡ ከማታው ፡ ፫ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ደንበጫ ፡ ገብተናል ፤ ስለ ፡ ደብረማርቆስ ፡ በየጊዜው ፡ የሆነው ፡ መለዋወጥ ፡ አስገስግሶ ፡ አመጣን ፡ ስለዚህ ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ለማወቅ ፡ ቢቻልህ ፡ ራስህ ፡ ገሥግሰህ ፡ ባይቻልህ ፡ ሁነኛ ፡ ሰው ፡ ልከህ ፡ እርግጠኛውን ፡ አኳሆን ፡ እንድናውቀው ፤ ስለ ፡ ራስ ፡ ኃይሉም ፡ አኳሆን ፡ ነገሩ ፡ ገብቶህ ፡ የጻፍከውን ፡ ደብዳቤ ፡ ተመልክተነዋል ፤ ወይም ፡ ከነጦሩ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ለመግባት ፡ ወይም ፡ እንዳስብከው ፡ በማድረግ ፡ አንዳቸው ፡ እንዲፈጸም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፤ ከራሳችን ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ያለውን ፡ ሰውና ፡ ከነደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽና ፡ ሌሎቹም ፡ መኳንንቶች ፡ እንደምን፡ ደብረ ፡ ማርቆስን ፡ እንደሚከቡ ፡ ከፈረንጆችም ፡ እንዳገኘኸው ፡ ያንተንም፡ አሳብ ፡ ጨምረህ ፡ በዝርዝር ፡ እንድናውቀው ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፤ ለመሥራትም ፡ ለማሠራትም ፡ አስቀድሞ ፡ የነገሩን ፡ ሁናቴ ፡ ጠንቅቆ ፡ ማወቅ ፡ አስፈላጊነቱን ፡ ታውቀዋለህና ፡ ማናቸውንም ፡ ማስረጃ ፡ እንድናውቀው ፡ ነው ፤ ስለበላይ ፡ ዘለቀ ፡ አኳሆን ፡ የመጣ ፡ ሰው ፡ እንዳለ ፡ ማስረጃውን ፡ ከነሰው ፡ ብትልክልን ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ጥቂቱን ፡ ወታደር ፡ ኢጣልያኖች ፡ አስረከቡኝ ፡ ስላሉ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ የማይመጣ ፡ እርሳቸውን ፡ የሚከተል ፡ የባንዳ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ማነው ።

መጋቢት ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
በዋና ፡ ጦር ፡ ሠፈር ፡ ተጻፈ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አንድ ፡ የጦር ፡ ፕላን ፡ ተላከልን ፡ ይኸውም ፡ ፕላን ፡ የደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ከተማ ፡ እስኪወድቅ ፡ ድረስ ፡ ዙሪያውን ፡ ከበው ፡ የተቀመጡ ፡ አርበኞችና ፡ የሠለጠኑ ፡ ወታደሮች ፡ የሚጠባበቁባቸውን ፡ ቦታዎች ፡ የሚአሳይ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ የሥራ ፡ መምሪያ ፡ ደረሰኝ ።

## የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ፤

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።
ይድረስ ፡ ከአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፤

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና ፡ ነን ። ስለራስ ፡ ኃይሉ ፡ አኳሆን ፡ አንተም ፡ በጻፍክልን ፡ ደብዳቤ ፡ ከዚያም ፡ የሚመጣ ፡ ሰው ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ ስላስረዳን ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ላሉት አርበኞቻችን ፡ የጻፍነውን ፡ ደብዳቤ ፡ ግልባጭ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ልከንልሃል ።


አርበኞቻችን ፡ የሚጠባበቁበት ፡ ስፍራ ፡ እንደጻፍንላቸው ፡ ቃል ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ከአማኑኤል ፡ ጎን ፡ በመንገድ ፡ በስተቀኝ ፡ ከጉሊት ፡ ወዲህ ፤ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ከማርቆስ ፡ ጎን ፡ ከመንገድ ፡ ቀኝ ፡ ወገን ፡ ከጉሊት ፡ በታች ፤ ፊታውራሪ ፡ ኃይሉ ፡ ኢየሱስ ፡ ከአማኑኤል ፡ ግንባር ፡ በመንገዱ ፡ ግራ ፡ በአዲስ ፡ በኩል ፤ ፊታውራሪ ፡ ገበየሁ ፡ ባለበት ፡ በኩል፡ ጦሩን ፡ አስከትቶ ፤ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ እንደዚሁ ፡ በስተጀርባ ፡ ባለበት ፡ በኩል እንዲሆን ፡ አዘናቸዋል ። አንተና ፡ መኰንን ፡ ደስታ ፡ ከደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ወዲህ ፡ ከጉሊት ፡ በታች ፡ በመንገዱ ፡ በስተቀኝ ፡ ሆናችሁ ፡ ቦታ ፡ ይዛችሁ ፡ ተጠባበቁ ። እኛም ፡ ደንበጫ ፡ ገብተናልና ፡ ይህንንም ፡ ባለፈው ፡ ደብዳቤ ፡ ስለጻፍንልህ ፡ አሁን ፡ በቶሎ ፡ ወደዚያው ፡ መምጣታችን ፡ ነው ። ደግሞ ፡ በቃል ፡ እንዳገኘነው ፡ ወሬ ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ አሳባቸው ፡ ኢጣልያኖችን ፡ በጅበላና ፡ ሙተራ ፡ በኩል ፡ ለማሳለፍና ፡ እንዲያመልጡ ፡ ለማድረግ ፡ ያስባሉ ፡ ስለተባለ ፡ የሚቻል ፡ መሆኑን ፡ እዚያው ፡ ለመመዘንና ፡ አርበኞቻችንን ፡ ለማስጠንቀቅ ፡ ትችላለህ ።

መጋቢት ፡ ፳፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
በዋና ፡ ጦር ፡ ሠፈር ፡ ተጻፈ ።

## በደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ዙሪያ ፡ ከጠላት ፡ ጋር ፡ ስለመዋጋታችን ።

እኔም ፡ በማርቆስ ፡ አካባቢ ፡ ጉሊትና ፡ ሐዲስ ፡ ከተባለው ፡ ቦታ ፡ ስደርስ ፡ ኰሎኔል ፡ ፓውስትድንና ፡ ልጅ ፡ መኰንን ፡ ደስታን ፡ ጦሩን ፡ ወደኋላ ፡ ትተው ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ ግምትና ፡ ያለበትን ፡ ቦታ ፡ ሲአጠኑ ፡ አገኘኋቸው ፡ ሁለቱን ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ እያለዋወጥን ፡ የጠ





የትውልድ ፡ ሀገሩ ፡ ጐጃም ፡ በብቸና ፡ አውራጃ ፡ ማባት ፡ እነማይ ፡ በአርበኝነት ፡ ዘመን ፡ በቆላ ፡ ዳሞት ፡ ከደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህ ፡ ጋር ፡ የነበረ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ከሱዳን ፡ በበላያ ፡ በኩል ፡ ሲዘልቁ ፡ ከደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ እርዳታ ፡ የተላኩትን ፡ የኮርቻ ፡ በቅሎዎችና ፡ አጋሰሶች ፡ እስከመተከል ፡ ድረስ ፡ ወስዶ ፡ ያስረከበ ፡



ፊታውራሪ ፡ ወርቅነህ ፡ ንጉሤ ፡

በአርበኝነት ፡ ዘመኑም ፡ አርበኞች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እየተጋጩ ፡ ኅብረት ፡ በሚጠፋበት ፡ ጊዜ ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህን ፡ ኅብረትና ፡ አንድነት ፡ እንዳይጠፉ ፡ በመምከር ፡ ወደ መልካም ፡ ተግባር ፡ ይመራ ፡ የነበረ ፡ ሰው ፡ ነው ። እኔም ፡ ከደረስሁ ፡ በኋላ ፡ በዚሁ ፡ ሥራው ፡ ይረዳኝ ፡ ስለነበረ ፡ ቅንና ፡ ታማኝ ፡ ሠራተኛ ፡ መሆኑን ፡ ተረድቻለሁ ።



ላት ፡ ጦር ፡ በሠፈረባቸው ፡ ቦታዎች ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ሰው ፡ በየተራው ፡ እየላክን ፡ ስናስተኩስበት ፡ የጠላትም ፡ ጦር ፡ ተከበብኩ ፡ በማለት ፡ መድ ፉንም ፡ መትረየሱንም ፡ የተኩስ ፡ ድምፅ ፡ በሰማበት ፡ አቅጣጫ ፡ ሌሊ



አቶ ፡ መኰንን ፡ ደስታ ፡ ተድላ ፡ (ደጃዝማች) ።

ቱን ፡ ሙሉ ፡ ሲተኩስ ፡ ያድራል ። የእኛም ፡ ወታደሮች ፡ እስከ ፡ ተወሰ ነላቸው ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ የታዘዙትን ፡ ፈጽመው ፡ ሳይታዩና ፡ ግምታ ቸው ፡ ሳይታወቅ ፡ ጠፍተው ፡ ከእኛ ፡ ይቀላቀላሉ ። ይህም ፡ ታክቲክ ፡ ጠላትን ፡ ስለአስጨነቀው ፡ ቀን ፡ በእየቈጥቋጣችን ፡ ሥር ፡ ሆነን ፡ ስን መለከት ፡ እየተንቆራጠጠ ፡ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ በመለወጥ ፡ ጉድጓድ ፡ በመቆ ፈር ፡ ካብ ፡ በመካብ ፡ ቦታ ፡ ሲአበጅ ፡ እናያለን ፤ በበኩላችን ፡ እኛም ፡ ሁኔታውን ፡ እናጠናና ፡ ሌሊት ፡ የተቆጠሩ ፡ ወታደሮች ፡ እንልክና ፡ የተ ኩስ ፡ ድምፅ ፡ እያሰማን ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ሲተኩስ ፡ ያድራል ፡ እንደ ዚህ ፡ አድርገን ፡ ግምታችን ፡ ሳይታወቅ ፡ ከ፲፭ ፡ ሺህ ፡ በላይ ፡ የነበረውን፡

የጠላት ፡ ጦር ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ በማንሞላ ፡ ወታደሮች ፡ ሩቃ ፡ ነሳነውና ፡ ቢጨንቀው ፡ ደብረ ፡ ማርቆስን ፡ ከነባንዳው ፡ ወታደር ፡ ለራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አስረከበና ፡ እዚያ ፡ የነበረው ፡ የነጩ ፡ ጦር ፡ ደብረ ፡ ማርቆስን ፡ ለቆ ፡ ሊሄድ ፡ መቁረጡን ፡ ወሬ ፡ ደረሰን ፡ እኛም ፡ ተኩሎ ኔል ፡ ፓውስትድና ፡ ከአቶ ፡ መኰንን ፡ ደስታ ፡ ጋር ፡ ተመካክርንና ፡ ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ወደደጃን ፡ በሚአመራው ፡ መንገድ ፡ ቀድመን ፡ የደፈጣ ፡ አደጋ ፡ እንድናደርግ ፡ ተስማማን ።

ሜጀር ፡ ጆንሰን ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ የእንግሊዝ ፡ መኰንን ፡ አሥር ፡ ሱዳኖችና ፡ ፪ ፡ መትረየስ ፡ ይዞ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ እንዲቀድም ፡ ሆኖ ፡ ተጓ ዝን ፡ ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ በሚመጣውም ፡ ጦር ፡ አደጋ ፡ ለመጣል ፡ የሚ መች ፡ ቦታ ፡ እንዲአሳየን ፡ ፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡ ዓለሙ ፡ የሚባለውን ፡ አርበኛ ፡ ይዘን ፡ ቦታ ፡ አሳይቶን ፡ ስንዘጋጅ ፡ ሳናስበው ፡ እኛ ፡ የምንጠ ብቀው ፡ ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ የሚመጣውን ፡ ጦር ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ከወደ ኋላችን ፡ በደጀን ፡ በኩል ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ላለው ፡ ጦር ፡ ከአዲስ ፡ አ በባ ፡ የተላከ ፡ በሁለት ፡ ብረት ፡ ለበስ ፡ ኦቶብላንዲ ፡ የታጀበ ፡ በ፺፯ ፡ ካሚዎን ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ጦር ፡ በባንዳ ፡ ወታደሮች ፡ በነቀኛዝማች ፡ አያ ሌው ፡ ንጉሤና ፡ በነቀኛዝማች ፡ ምንውየለት ፡ ካሣ ፡ እየተረዳ ፡ በኋ ላችን ፡ ሳናስበው ፡ ደረሰብንና ፡ ወታደር ፡ ከመኪና ፡ እየወረደ ፡ በመኪና ፡ ላይ ፡ ያለውም ፡ በመትረየስ ፡ ጭምር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተኰሰብን ፡ እኛም ፡ ብትንትን ፡ አልንና ፡ በየቁጥቋጠው ፡ ውስጥ ፡ ገባን ፡ ደግሞም ፡ ቢተኩሱ ፡ ከእኛ ፡ በኩል ፡ መልስ ፡ ነሳናቸው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሩኖ ፡ ነው ፡ ሄደ ፡ አለና ፡ የወረደውም ፡ ወታደር ፡ ወደ ፡ ካሚዎኑ ፡ ተሳፈረ ፡ እኛም ፡ ዝም ፡ ብለን ፡ አደፈጥንና ፡ ካሚዎኑ ፡ እጠባብ ፡ ቦታ ፡ እስቲደርስ ፡ ጠበቅነውና ፡ በጣም ሲቀርብልን ፡ ያለነው ፡ ሁላችንም ፡ በዙሪያው ፡ ተበታተንና ፡ እንደተ ከበበ ፡ አድርገን ፡ ተኰስንበት ፤

እመኪናውም ፡ ላይ ፡ ቢሆን ፡ መቁሰልና ፡ መሞት ፡ ቢወርድም ፡ መሞት ፡ ሆነበት ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኦቶብላንዲው ፡ ብቻ ፡ ከኋላና ፡ ከፊት ፡ የነበረው ፡ በያለበት ፡ ቆሞ ፡ የመትረየስ ፡ ተኩሱን ፡ የጥይት ፡ ድምፅ ፡ ወደሰማበት ፡ ብቻ ፡ ሲተኩስ ፡ ሌላው ፡ ወታደር ፡ ከሞት ፡ የተረፈው ፡ በቀኛዝማች ፡ ምንውየለት ፡ በቀኛዝማች ፡ አያሌው ፡ ንጉሤ ፡ ተመርቶ ፡ በየውሽ ፡ በኩል ፡ አድርጐ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ካለው ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ሲቀላቀል ፡ ፺፯ ፡ ካሚዎንና ፡ ሁለት ፡ ኦቶብላንዲ ፡ ከነተጫነው ፡ ዕቃ ፡ በሚዳው ፡ ላይ ፡ ቀገኘ ፡ ምን ፡ ይደረግ ፡ ለጊዜው ፡ የእኛም ፡ አቅም ፡ የሚችለው ፡ ማበላሸት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ካሚዎኑም ፡ ሆነ ፡ ኦቶብ ላንዲው ፡ ለጠላት ፡ እንዳያገለግል ፡ ሞተሩን ፡ በአሜሪካን ፡ መውዜር ፡ እየተኰስን ፡ አበላሸነው ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ የተጫነውን ፡ ዕቃ ፡ ግን ፡ ድል ፡ የተመለከተው ፡ ባላገር ፡ ከያለበት ፡ መጣና ፡ ዘረፈው ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡



የሞተው ፡ ነጭ ፡ ፲፫ ፡ ሲሆን ፡ አንድ ፡ ነጭ ፡ ቆስሎ ፡ ተማርኮአል ፡ የጥ ቁሩ ፡ ወታደር ፡ ግን ፡ ከቁጥር ፡ የተረፈ ፡ ነው ።

## ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መላኩቱኛ ፡ ስለመላካቸው ፡

ከዚህ ፡ ድል ፡ በኋላ ፡ ከራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘንድ ፡ ደጃዝማች ፡ አላምረው ፡ ተልከው ፡ መጥተው ፡ ኖሮ ፡ ከጠላት ፡ ለመሁ ወረያ ፡ ከአዘጋጅነው ፡ ሥፈር ፡ አገኘናቸው ፡ ከራስ ፡ ኃይሉም ፡ የተላ ኩት ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ለቆ ፡ መሄዱ ፡ ነውና ፡ ሰው ፡ እንዳይሞት ፡ መንገ ዱን ፡ ልቀቁለት ፡ የሚል ፡ ነው ። ለዚህ ፡ መልስ ፡ እኛ ፡ የምንዋጋው ፡



ፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡ ዓለሙ ።

ከግርማዊ ፡ ጃንሆይም ፡ በየተቀበልነው ፡ ትእዛዝ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በሙሉ ፡ ነፃ ፡ ለማውጣት ፡ ስለሆነ ፡ ጎጃምን ፡ ብቻ ፡ ቢለቅ ፡ ሙሉ ፡ ነጻነት ፡ አይገኝም ፡ ስለዚህ ፡ የተቻለንን ፡ ያህል ፡ የጠላትን ፡ ኃይል ፡ መቀነስ ፡ አለብን ፤ ደግሞ ከዚህ ፡ ከሜዳው ፡ ላይ ፡ ለቀን ፡ ደጀንና ፡ የጎሐጽዮንን ፡ በር ፡ ይዞ ፡ እንዲ ከላከል ፡ ማድረግ ፡ ጥቅማችን ፡ አይደለም ፡ ብዬ ፡ መለስኩላቸው ።

ደጃዝማች ፡ አላምረው ፡ እንደ ፡ እኔስ ፡ ሃሳብ ፡ እንኳን ፡ ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ለቆ ፡ የሚሄደውን ፡ ይቅርና ፡ እኔ ፡ ደርሼ ፡ ቢሆን ፡ ቅድም ፡ የተዋጋችሁት ፡ ከአዲስ ፡ አበባም ፡ ጓዝ ፡ ለማንሳት ፡ የመጣውንም ፡ ቢሆን እንዳትወጉት ፡ አደርጋለሁ ፡ ብዬ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ከአንተ ፡ እንደ ተረዳሁት ፡ ቢለቅም ፡ ባይለቅም ፡ መዋጋት ፡ የማይቀር ፡ መሆኑን ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይህንኑ ፡ ሃሳብ ፡ ሄጄ ፡ ለራስ ፡ ኃይሉ ፡ እነግራለሁ ፡ ብለው ፡ ተሰ ነባብተን ፡ ተለያየን ።



ፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ ደስታ ።

እኛም ፡ ቦታ ፡ አዛውሮ ፡ ደፈጣ ፡ የምናደርግበትን ፡ በፊት ፡ የነበ ረው ፡ ፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡ ዓለሙና ፡ በኋላ ፡ ጦርነቱ ፡ አምልጦት ፡ ለዘረፋ ፡ የደረሰውን ፡ ፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ ደስታን ፡ ጨምረን፡ ስንመ ካከር ፡ ከራስ ፡ ኃይሉ ፡ ዘንድ ፡ ፈረሰኛ ፡ መላክተኛ ፡ ደረሰና ፡ ጠላት ፡ ደብረ ፡ ማርቆስን ፡ ለቋል ፡ በዙሪያው ፡ የሚገኝ ፡ አርበኛ ፡ ከተማውንም ፡



ግቢውንም ፡ ሊዘርፍ ፡ አቆብቁቧል ፡ እኔም ፡ ባላገርም ፡ ሆን ፡ አርበኛ ፡ አላስገባም ፡ ስለዚህ ፡ እገባለሁ ፡ አላስገባም ፡ በማለት ፡ እንታኰስና ፡ መተፋፈር ፡ እንዳያጨካክነን ፡ ከተማውንና ፡ ግቢውን ፡ አንተ ፡ የግር ማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አሽከር ፡ ስለሆንክ ፡ ብትመጣ ፡ ለአንተ ፡ አስረክባለሁ ። በተረፈ ፡ መታኰሳችን ፡ ነው ፡ ብለዋል ፡ ብሎ ፡ ነገረኝ ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ሃሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ ግድ ፡ ሆነና ፡ እዚያ ፡ የነበረውን ፡ እንግ ሊዛዊ ፡ መኰንን ፡ ከሙሬ ፡ ጋር ፡ አደጋ ፡ እንዲጥሉ ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ላክሁና ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ገሠገሥሁ ። ስደርስ ፡ ኰሎ ኔል ፡ ፓውስትድንና ፡ አቶ ፡ መኰንን ፡ ደስታን ፡ ሻለቃ ፡ ዮሐንስ ፡ አብ ዶን ፡ አገኘኋቸው ።



ፊታውራሪ ፡ ባየን ፡ ቢሻው ።



ፊታውራሪ ፡ ደምሴ ፡ ዓለማየሁ ።

## የደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ምሽግ ፡ በእኛ ፡ እጅ ፡ ስለመግባቱ ፡

ወዲያው ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ መጡና ፡ ተገናኘን ፡ ከአርበኛውም ፡ እነ ፊታውራሪ ፡ ዘለቀ ፡ ደስታ ፡ ከብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ጋር ፡ ደረሱ ፡ ጠቡ ፡ ቀረና ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ለአርበኛውም ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ በደርሀንና ፡ በበር ሚል ፡ የነበረውን ፡ ኮኛክና ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ማደል ፡ ጀመሩ ። ዱሮ ፡ እን ታኰሳለን ፡ የተባለውም ፡ ሃሳብ ፡ ቀረና ፡ የወገን ፡ ግንኙነት ፡ ይደረግ ፡ ጀመር ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ኃይሉን ፡ እንደሣቸው ፡ እንተዋቸው ፡ የሚል ፡ የዋለለ ፡ ሃሳብ ፡ ከእንግሊዛዊው ፡ መኰንን ፡ ዘንድ ፡ በምክር ፡ ዓይነት ፡ ቀረበ ፤ እኔም ፡ ለመያዝ ፡ ነገር ፡ ማደፍረስና ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ግጭትን ፡ የሚፈጥር ፡ መሆኑን ፡ ተገንዝቤው ፤ ብንተዋቸውም ፡ አንድነት ፡ ለመቀ መጥ ፡ አንስማማም ፡ እንዲያውም ፡ መገማመትን ፡ ያስከትላል ፡ በማለት ፡ አሰብኩና ፡ እስካሁን ፡ እዚሁ ፡ ከኢጣልያኖች ፡ ጋር ፡ አንድነት ፡ ኖሮ



ፊታውራሪ ፡ ዘለቀ ፡ ደስታ ፡

አል ፡ ወይ ፡ የተቀመጡት ፡ ስል ፡ ጠየቅኋቸው ። እሳቸውም ፡ እውጭ ፡ ቀድሞ ፡ የኢጣልያን ፡ ቆንስል ፡ እነበረበት ፡ ቤት ፡ ነው ፡ የተቀመጥኩት ፡ ዛሬ ፡ ነው ፡ እዚህ ፡ የገባሁት ፡ ሲሉ ፡ መለሱልኝ ፤ እኔም ፡ እዚህ ፡ ሰው ፡ ተቀላቅሎ ፡ ድንገት ፡ አንድ ፡ ግጭት ፡ ቢነሳ ፡ ደህና ፡ አይሆንምና ፡ እን ግዲያውስ ፡ እዚያ ፡ ቢሄዱ ፡ አይሻልም ፡ ወይ ፡ ስል ፡ ሃሳብ ፡ ሰጠኋቸው ። እሳቸወ ም ፡ ቀበል ፡ አድርገው ፡ እውነት ፡ ነው ፡ እዚህ ፡ ተፋፍገን ፡ ከምን ቀመጥ ፡ እዚያ ፡ ብሄድ ፡ ይሻላል ፡ አሉና ፡ ብድግ ፡ ብለው ፡ ጉዞ ፡ ሲጀ ምሩ ፡ ከተከተላቸው ፡ ባንዳ ፡ መኳንንት ፡ ውስጥ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ለቀን ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ የምንሄደው ፡ በማለት ፡ ጐራዴ ፡ እየጨበጠ ፡ ማን ገራበድ ፡ ሲጀምር ፡ አሁንም ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ቀበል ፡



አደረጉና ፡ ለቤቱ ፡ ጥበቃ ፡ እንደሆን ፡ እንማማጊቴ ፡ አሉ ፡ እኛ ፡ ግን ፡ እዚህ ፡ ተፋፍን ፡ ከመቀመጥ ፡ አንገት ፡ ለየት ፡ አድርጎ ፡ መቀመጥ ፡ አይሻልም ፡ ወይ ፡ አሉና ፡ ሄዱ ።

እሳቸው ፡ እንደሄዱ ፡ በምሽቱ ፡ ዙሪያ ፡ መድፍና ፡ መትረየስ ፡ እንደ ተጠመደ ፡ የባንዳ ፡ ወታደር ፡ እንደያዘው ፡ ይጠበቃል ። እኔም ፡ ከጥቂት ፡ ወታደሮች ፡ ጋር ፡ እየዞርኩ ፡ ስጎበኝ ፡ እነዚህ ፡ ወታደሮች ፡ እኮ ፡ ምሳቸ ውን ፡ አልበሉ ፡ ይሆናል ፡ አልኩና ፡ ስናገር ፡ እህል ፡ ከቀመሱን ፡ ዛሬ ፡ ሁለት ፡ ቀናችን ፡ ነው ፡ አሉና ፡ ተናገሩ ። እኔም ፡ ቀበል ፡ አደረግሁና ፡ ብርሃኔ ፡ ወታደር ፡ አምጣና ፡ እናንተ ፡ ስትጠብቁላቸው ፡ ቆዩ ፡ እነሱ ፡ በልተው ፡ ይምጡ ፡ አልኩና ፡ አዘዝኩ ፤ ብርሃኔ ፡ ወልደ ፡ ማርያምም ፡ እን ደታዘዘው ፡ ወታደሮቹን ፡ አመጣና ፡ መድፍና ፡ መትረየስ ፡ የተጠመደበ ትን ፡ ቦታ ፡ ተረከበና ፡ ሲአስጠብቅ ፡ እነዚያ ፡ ምሳ ፡ ሊበሉ ፡ ሄዱ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለብርሃኔ ፡ መትረየሱ ፡ ተነስቶ ፡ እናንተ ፡ መጋዘን ፡ ይግባ ፡ መድፉ ፡ ለመተኰስ ፡ የሚአገለግለውን ፡ መሣሪያ ፡ አውልቅና ፡ ወታደሮቹ ፡ ወደ ፡ ሠፈራቸው ፡ ይመለሱ ፡ ብዬ ፡ አዘዝኩና ፡ እንደትእዛዙ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ምሳ ፡ ሊበሉ ፡ የሄዱት  የጠላት ፡ ባንዳ ፡ ወታደሮች ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ያስልፏቸው ፡ እንደነበረ ፡ ሆነው ፡ ሊጠብቁ ፡ ቢመጡ ፡ መትረየሱን ፡ ከቦታው ፡ አጡት ። መድፉንም ፡ ቀፎውን ፡ ብቻ ፡ አገኙትና ምንም ፡ ሳይናገሩ  ዝም ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ሠፈራቸው ፡ ተመለሱ ፤ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ አሠራር ፡ ከጠላት ፡ ባንዳዎች ፡ ጋር ፡ ያለምንም ፡ ክርክር ፡ ምሽ ጉን ፡ በበዴ ፡ አስለቅቀን ፡ ያዝንና ፡ ባሉን ፡ ወታደሮች ፡ በሩን ፡ አስጠብ ቀን ፡ አደርን ። እኔም ፡ በማግሥቱ ፡ ወደ ፡ ደንበጫ ፡ ሄድኩና ፡ ደብረ ፡ ማርቆስን ፡ አስለቅቀን ፡ መያዛችንን ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ አስረዳሁ ። ግር ማዊነታቸውም ፡ በማግሥቱ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ የሚመጡ ፡ መሆ ናቸው  ተነገረኝና ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ተመልሼ ፡ ሄድኩ ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የሚገቡበት ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የኢጣሊያን ፡ ጦር ፡ የነበረበት ፡ ምሽግ ፡ ስለ ነበረ ፡ ስለአስፈላጊው ፡ ምርመራና ፡ ስለጸጥታውም ፡ አጠባበቅ ፡ ጠላት ፡ ከመግባቱ ፡ በፊት ፡ ገኑት ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጦር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተማሩ ፡ በአርበኝነትና ፡ በስደትም ፡ የሚፈለግባቸ ውን ፡ ግዳጅ ፡ የፈጸሙ ፡ ግርማዊነታቸውም ፡ ጦር ፡ አደራጅተው ፡ ጠላ ትን ፡ ለማጥቃት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመግባት ፡ ከለንደን ፡ ወደ ፡ ካር ቱም ፡ በመጡበት ፡ ጊዜ ፡ በካርቱም ፡ ሶባ ፡ በተባለው ፡ ጦር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ የጦር ፡ ታክቲክ ፡ ልምምድ ፡ ሲአደርጉ ፡ ቆይተው ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ጋር ፡ መጥተው ፡ ባጠገባቸው ፡ ከሚገኙት ፡ ግሚ ሶቹ ፡ ቀድመው ፡ እንዲአዘጋጁ ፡ ተልከው ፡ ሌሊቱን ፡ ገብተው ፡ አድ

ረው ፡ የተላኩበትን ፡ ተግባር ፡ በመፈጸም ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ መም ጣት ፡ ሲጠባበቁ ፡ ቆዩ ። የስም ፡ ዝርዝራቸውም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሚ ገኘው ፡ ነው ።


1. ሻለቃ ፡ ዓቢይ ፡ አበበ ፡ (ሌፍተናንት ፡ ጄኔራል) ፡
2. ሻለቃ ፡ ነጋ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ (ሌፍተናንት ፡ ጄኔራል) ፤
3. ሻለቃ ፡ ሙሉጌታ ፡ ቡሊ ፡ (ሌፍተናንት ፡ ጄኔራል) ፡
4. ሻምበል ፡ ከበደ ፡ ገብሬ ፡ (ሌፍተናንት ፡ ጄኔራል) ፡
5. ሻምበል ፡ ታምራት ፡ ይገዙ ፡ (ሌተና ፡ ኰሎኔል) ፡
6. ሻምበል ፡ ታምራት ፡ ዘገዬ ፡ (ኰሎኔል) ፡
7. ሻምበል ፡ ለገሠ ፡ ወልደ ፡ ሐና ፡ (ኰሎኔል) ፤
8. ሻምበል ፡ ዘውዴ ፡ ዘርፉ ፡ (ኰሎኔል) ፡
9. ወልደ ፡ ማርያም ፡ ኃይሌ ፡ (ኰሎኔል) ፡
10. ክፍሌ ፡ አደፍርሰው ፡ (ሻለቃ) ፡
11. ዘውዱ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ (ሌተና ፡ ኰሎኔል) ፡
12. » አማን ፡ አንዶም ፡ (ሜጀር ፡ ጄኔራል) ፡
13. » በቀለ ፡ መካ ፡
14. » በቀለ ፡ አበጋዝ ፡
15. » ብሥራት ፡ መሣይ ፡
16. የመቶ ፡ አለቃ ፡ ንጉሤ ፡ ብርቄ ፡ (ብርጋዲዬር ፡ ጄኔራል) ፤
17. » » ማሞ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ (ብርጋዲዬር ፡ ጄኔራል) ፡
18. » » ጋሞ ፡ ጉበቢ ፡ (ሌተና ፡ ኰሎኔል) ፡
19. » » ዘውዴ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ (ብርጋዲዬር ፡ ጄኔራል) ፤
20. የመቶ ፡ አለቃ ፡ ሽፈራው ፡ ተሰማ ፡ (ሜጀር ፡ ጄኔራል) ፡
21. » » ደግነህ ፡ ጉግሣ ፡ (ሜጀር ፡ ጄኔራል) ፡
22. » » ከተማ ፡ ተፈራ ፡ (ሻምበል) ፡
23. » » ተፈራ ፡ ፋንታ ፡ (ሻለቃ) ፤

ሌሎችም ፡ ነበሩ ፡ ለጊዜው ፡ ስማቸው ፡ ስላተዘነጋ ፡ አልጻፍኳ ቸውም ።




## ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ በታላቅ ፡ ሠልፍ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ስለ መግባታቸውና ፡ ባንዲራ ፡ ስለመስቀላቸው ።

ደብረ ፡ ማርቆስም ፡ እንደተቻለ ፡ ያህል ፡ ስለግርማዊነታቸው ፡ አቀ ባበል ፡ ሲዘጋጅ ፡ አመሸና ፡ በማግሥቱ ፡ ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ እስከ ፡ ወንቃ ፡ ሕዝቡ ፡ በሙሉ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ተሰልፎ ፡ ወንዱ ፡ በሆታ ፡ ሴቱ ፡ በእል ልታ ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ተቀበላቸው ፡ መጋቢት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡



ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

ዓ ፡ ም ፡ እሑድ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ገብተው ፡ ባንዲራ ፡ ሲሰቅሉ ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለ ፡ ሃይ ማኖትን ፡ ለሰልፍ ፡ እንዳይወጡ ፡ በቤታቸው ፡ እንዲቀመጡ ፡ አድርገ



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በደብረ ፡ ማርቆስ ።
፩ ከቀኝ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ መርዕድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ።
፪ ከግራ ፡ ልዑል ፡ መኰንን ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መስፍን ፡ ሐረር ።



ናቸው ፡ ስለነበረ ፡ ባንዲራው ፡ ሲሰቀል ፡ እንዲጠሩ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ፈቀዱና ፡ አዘዙ ። ወዲያው ፡ መጡና ፡ በአደባባዩ ፡ ላይ ፡ ወድቀው ፡ እጅ ፡ ሲነሱ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ምሕረት ፡ ተሰጣቸው ።

ባንዲራው ፡ እንደተሰቀለ ፡ የጨረቃ ፡ ተዋጊዎች ፡ አንዳንዶቹ ፡ የጅብዱ ፡ ሞያዎቻቸውን ፡ በሐገር ፡ ልማድ ፡ በቀረርቶና ፡ በፉከራ ፡ ይገልጡ ፡ ነበር ፤ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የሰልፉ ፡ ሥርዓት ፡ ተፈጸመና ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ለማረፊያ ፡ ወደ ፡ ተዘጋጀላቸው ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሲገቡ ፡ ሰልፍ ፡ መልስ ፡ ሆነ ፡ በማግሥቱ ፡ መጋቢት ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አደባባይ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ቦታ ፡ ተቀምጠው ፡ አርበኞችን ፡ በሰልፍ ፡ ሲቀበሉ ፡ አርበኞች ፡ ጠላትን ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ያጠቁበትን ፡ ሞያ ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ ባገር ፡ ባሕል ፡ በቀረርቶና ፡ በፉከራ ፡ ይገልጹ ፡ ነበር ፤ የጎጃም ፡ ባለጅብዱና ፡ ባለሞያ ፡ የሆኑት ፡ አርበኞች ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ተፈቅዶላቸው ፡ ሰልፍ ፡ ባሳዩበት ፡ ጊዜ ፡ ከራስ ፡ ኃይሉ ፡ ጋር ፡ የነበረው ፡ ባንዳ ፡ ወታደር ፡ ማንንም ፡ ሳያስፈቅድ ፡ በሰልፉ ፡ ውስጥ ፡ ተቀላቅሎ ፡ እንደ ፡ አርበኞችም ፡ ለመናገርና ፡ ጅብዱ ፡ ለመቁጠር ፡ በሥራው ፡ እያፈረ ፡ ቢቀርብትም ፡ ያለይሉኝታ ፡ በሰልፉ ፡ ተራ ፡ ገብቶ ፡ ሰልፍ ፡ ሲያሳይ ፡ ዋለ ። የባንዳው ፡ ወታደር ፡ በሰልፍ ፡ ተራ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ማሳየት ፡ እንዲያው ፡ በመኳለልና ፡ በመዳረቅ ፡ የተደረገ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በፈቃድ ፡ አለመሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።



ፊታውራሪ ፡ ዘውዴ ፡ መርዕድ ፡



ፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡ ደስታ ፡

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

# ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ስለመንዛቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ከተማ ፡ እንዳለን ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ለመግባት ፡ በሶስት ፡ በር ፡ በኩል ፡ ጦሩን ፡ መሥራት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ በሚል ፡ ሃሳብ ፡ ላይ ፡ አርፎ ፡ መሐሉን ፡ በደጀንና ፡ በጎሐጽዮን ፡ በኩል ፡ የሚያልፈው ፡ በቀጥታ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ጋር ፡ የሚገኘው ፡ ጦር ፡ እንዲሆን ፡ በደራ ፡ ተሻግሮ ፡ በመርሐቤቴ ፡ የሚዘልቅ ፡ በሻለቃ ፡ መስ



ልዑል ፡ መኰንን ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ለመሔድ ፡ በአውሮፕላን ፡ ሲሣፈሩ ።

ፍን ፡ ስለሺ ፡ የሚመራው ፡ ጦር ፡ እንዲሆን ፡ በግንደበረት ፡ በኩል ፡ ተሻግሮ ፡ በሜጫ ፡ በኩል ፡ የሚዘልቀው ፡ በአዛዥ ፡ ከበደ ፡ የሚመራው ፡ ጦር ፡ እንዲሆን ፡ ታስቦ ፡ በመደልደል ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ በሐ





ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ (ራስ ፡ ቢትወደድ) ።



ልጅ ፡ አስፋው ፡ ከበደ ፡ (ፊታውራሪ) ።

ረር ፡ በኩል ፡ የመጣው ፡ ጦር ፡ መያዙን ፡ በራዲዮ ፡ ሰማን ፤ አዲስ ፡ አበባን ፡ በቅድሚያ ፡ ለመያዝ ፡ የነበረው ፡ ምኞታችን ፡ በመጨናጎሉ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ መያዝ ፡ የነበረውን ፡ ደስታ ፡ ቅርታ ፡ ሳይቀላቀልበት ፡ አልቀረም ።

በዚሁም ፡ ቅርታ ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ሆኖ ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ ከያዙት ፡ እንግሊዞች ፡ የቀረበው ፡ ሃሳብ ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ፀጥታው ፡ እስቲረጋጋ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ በዚያው ፡ በደብረ ፡ ማርቆስ ፡ እንዲቆዩ ፡ የሚል ፡



ሻለቃ ፡ ዓቢይ ፡ አበበ ፡ (ሌፍትናንት ፡ ጄኔራል) ።

ነበር ፤ ይህ ፡ ጥቂት ፡ ማሳዘኑ ፡ ባይቀርም ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ሃሳቡን ፡ ተቀበሉና ፡ ለጊዜው ፡ የመግቢያውን ፡ ፕሮግራምና ፡ ግርማዊነታቸው ፡ የሚገቡበትን ፡ ቤት ፡ የሚአዘጋጁ ፡ ስለ ፡ ጸጥታ ው ፡ አጠባበቅ ፡ ሻለቃ ፡ ዓቢይ ፡ አበበንና ፡ ፊታውራሪ ፡ አስፋውን ፡ ሻለቃ ፡ ነጋ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፤ ሻለቃ ፡ ሙሉጌታ ፡ ቡሊን ፤ ሌሎችንም ፡ መኰንኖች ፡ ጭምር ፡ ይዘው ፡ እንዲቀድሙ ፡ ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ ታዘዙና ፡ ቀድመው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገቡ ።





ሻለቃ ፡ ነጋ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ (ሌፍትናንት ፡ ጄኔራል) ።



ሻለቃ ፡ ሙሉጌታ ፡ ቡሊ ፡ (ሜ/ጄኔራል) ።



ሻምበል ፡ ከበደ ፡ ገብሬ ፡
(ሌፍትናንት ፡ ጀኔራል) ።

ልጅ ፡ ወሰን ፡ ኃይሉ ፡
(ዋግሥዩም) ።





ግርማዊነታቸው ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ የሸሸውን ፡ ጦር ፡ የሚከታተል ፡ ጦር ፡ አዘዙ ፡ የሚሸሸው ፡ ጦር ፡ ጎሐ ፡ ጽዮንን ፡ ተሻግሮ ፡ ይቆማል ፡ ተብሎ ፡ የነበረው ፡ ቀርቶ ፡ ሽሽቱን ፡ ወደ ፡ ደራና ፡ ቦረና ፡ ስለአመራ ፡ ሸሺውም ፡ አባራሪውም ፡ በዚሁ ፡ እንደአመሩ ፡ ደግሞ ፡ ሞጣ ፡ ላይ ፡ ተቋርጦ ፡ የቀረ ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ስለነበረ ፡



ራስ ፡ እንዳርጋቸው ፡ መሳይ ፡

ልጅ ፡ እንዳርጋቸው ፡ መሣይና ፡ ልጅ ፡ ወሰን ፡ ኃይሉ ፡ ታዘው ፡ ሄደው ፡ በአገሩ ፡ ላይ ፡ ከሚገኙት ፡ አርበኞች ፡ ጋር ፡ ምሽጉን ፡ ሰበሩት ፡ እዚያ ፡ የነበረውንም ፡ ጦር ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ የጠላትን ፡ ምርኮኞችና ፡ ብዙ ፡ መትረየስ ፡ ይዘው ፡ ጎሐ ፡ ጽዮን ፡ ላይ ፡ ደረሱ ። ግርማዊነታቸውም ፡ ከ፳ ፡ ቀን ፡ በላይ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ቆይተው ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ጉዞ ፡ ተጀመረ ፡

እንልጅ ፡ አንዳርጋቸው ፡ መሣይ ፡ የኢጣልያኖችን ፡ ምርኮኞች ፡ ይዘው ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ጋር ፡ የተገናኙት ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ጎሐ ፡ ጽዮን ፡ ባደሩበት ፡ ቀን ፡ ነበር ።

## ፍቼ ፡ ከተማ ፡ ስለመግባታቸው ።

ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ በተነሳን ፡ በ፫ኛው ፡ ቀን ፡ ፍቼ ፡ ገባን ፡ ፍቼ ፡ እንደገባን ፡ ከጠላት ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡ መኳንንቶች ፡ ስለመጡ ፡ በዘበኛ ፡ በእሥር ፡ ስም ፡ ሆነው ፡ እንዲጠበቁ ፡ ሆኑ ። ከነዚህም ፡ ከተያዙት ፡ መኳ



ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ብሩ ፡

ንንቶች ፡ ጋር ፡ ራስ ፡ ጌታቸውና ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ነበሩ ። እነዚ ህን ፡ ወደ ፡ ፍቼ ፡ መጥተው ፡ የተገኙትንም ፡ መኳንንቶች ፡ እንድጠይ ቃቸው ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ስለታዘዝኩ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈውን ፡ ቃል ፡ ጠየ ቅኋቸው ። ኢጣልያኖች ፡ በመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ሃሳብ ፡ ነው ፡ የስ



ጧችሁ ፡ እኛ ፡ የሰማነው ፡ ከሶስት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ እንመለሳለን ፡ በማለት ፡ የሶስት ፡ ወር ፡ ቀለብና ፡ መከላከያ ፡ የሚሆን ፡ መሣሪያ ፡ ለናንተ ፡ መሰ ጠታቸውንና ፡ እናንተም ፡ መቀበላችሁን ፡ ስለሆነ ፡ ይህን ፡ እንድትገ ልጡ ፡ ነው ፡ አልኋቸው ።

ለዚህም ፡ ጥያቄ ፡ በሶስት ፡ ወር ፡ እንመለሳለን ፡ ብለዋል ፡ የተባ ለው ፡ ቃል ፡ እውነት ፡ ነው ። ገንዘቡንም ፡ ተቀብለናል ፡ መሣሪያም ፡ ለመከላከያ ፡ አይደለም ፡ እንጂ ፡ ለራስ ፡ መጠበቂያ ፡ ተሰጥቶናል ፡ ብለው ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ መለሱልኝ ። ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ግን ፡ ከሌሎቹ ፡ የተለየ ፡ ቃል ፡ በተጨማሪ ፡ ስለነገሩኝ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ጽፌዋለሁ ። «አሁን ፡ የምትጠይቁት ፡ ምን ፡ ለማድረግ ፡ ነው ? በኔ ፡ በኩል ፡ ለማ ሠር ፡ እንደሆነ ፡ እሥራት ፡ ሰልችቶኛልና ፡ እንዲገድሉኝ ፡ እንጂ ፡ በእ ሥራት ፡ እንዳይቀጡኝ ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የተገኘው ፡ ድል ፡ በናንተ ፡ ኃይል ፡ ሳይሆን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አጋዥነት ፡ የተፈጸመ ፡ ስለ ሆነ ፡ እበቀላለሁ ፡ እንዳይሉ ፡ ብለህ ፡ ንገር» ፡ ብለው ፡ መለሱልኝ ።

## ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ስለመግባታቸው ።

ፍቼ ፡ ከተማ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ፡ያህል ፡ እንደቆየን ፡ በሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሰኞ ፡ ከፍቼ ፡ ተነስተን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ስንገባ ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ የነበረው ፡ የናፍቆት ፡ አቀባበል ፡ እልልታውና ፡ ጭብ ጨባው ፡ ሆታው ፡ አለልክ ፡ ይቀልጣል ። ግርማዊነታቸው ፡ ባጠገቡ ፡ ሲደርሱ ፡ ደግሞ ፡ እንባው ፡ በፊቱ ፡ እንደጎርፍ ፡ ይወርዳል ። እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ርኅራኄና ፡ ደስታ ፡ በተሞላበት ፡ አቀባበል ፡ ሕዝቡ ፡ ከእንጦጦ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ትልቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ ተሰልፎ ፡ ነበር ። እንደዚሁም ፡ በእንግሊዞች ፡ የሚታዘዘው ፡ ወታደር ፡ ከሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ አደባባይ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ቤተመንግሥት ፡ ድረስ ፡ ተሰ ልፎ ፡ በብረት ፡ ሰላምታ ፡ ይሰጥ ፡ ነበር ።

ግርማዊነታቸው ፡ በዚህ ፡ ሰልፍ ፡ መሐከል ፡ ተጉዘው ፡ ከታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ደርሰው ፡ ከመኪና ፡ ወርደው ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ባልኮን ፡ ላይ ፡ ብቅ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ በአደባባዩ ፡ ላይ ፡ የተሰበሰበው ፡ካህኑ ፡ በሃሌታ ፡ ሕዝቡ ፡ በሆታ ፡ ሴቱ ፡ በእልልታ ፡ መኳንንቱ ፡ በጭብጨባና ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ እየወረደ ፡ እጅ ፡ በመንሳት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የአቀባበል ፡ ሥርዓት ፡ አሳየ ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የተነገረው ፡ የግርማዊነታቸው ፡ የዙ ፋን ፡ ንግግር ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ገጽ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

## ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ከመናገሻ ፡ ከተማቸው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ።

የሰማይ ፡ መላእክት ፡ የምድር ፡ ሠራዊት ፡ ሊያስቡትና ፡ ሊያውቁት ፡ ይቻላቸው ፡ ባልነበረ ፡ በዚህ ፡ በዛሬው ፡ ቀን ፡ ቸር ፡ እግዚአብሔር ፡ በመካከላችሁ ፡ ለመገኘት ፡ ስላበቃኝ ፡ በሰው ፡ አፍ ፡ የሚነገር ፡ ምስጋና ፡ የሚበቃ ፡ አይደለም ፡ ከማናቸውም ፡ አስቀድሞ ፡ ለሁላችሁ ፡ ልነግራችሁና ፡ ልትረዱት ፡ የምፈልገው ፡ ይህ ፡ ቀን ፡ ለአዲሲቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የአዲስ ፡ ታሪክ ፡ ዘመን ፡ መክፈቻ ፡ መሆኑን ፡ ነው ፤ በዚሁ ፡ በአዲሱ ፡ ዘመን ፡ ሁላችንም ፡ መፈጸም ፡ ያለብን ፡ አዲስ ፡ ሥራ ፡ ይጀመራል ።

በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ በአለፉት ፡ ዘመናት ፡ የደረሰባትን ፡ መከራ ፡ ለማስታወስ ፡ ስንፈልግ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ የተያያዘውን ፡ ታሪኳን ፡ ብቻ ፡ በአጭር ፡ እንናገራለን ፤ ከብዙ ፡ ሺህ ፡ ዓመታት ፡ የበለጠ ፡ ነጻነቷን ፡ ጠብቃ ፡ የምትኖር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ኢጣልያ ፡ ከጥንት ፤ ጀምሮ ፡ በነበራት ፡ አጥቂነት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነጻነት ፡ ለማጥፋት ፡ ስለተነሳች ፡ በ፲፰፻፹፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአድዋ ፡ ላይ ፡ ጀግኖችዋ ፡ ጦርነት ፡ አድርገው ፡ ነጻነቷዋን ፡ አዳኑ ። በአድዋ ፡ ላይ ፡ ለተደረገው ፡ ጦርነት ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ የውጫሌው ፡ ውል ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።


ነገር ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመግዛት ፡ ኢጣልያ ፡ የነበራት ፡ ያላቋረጠ ፡ ምኞት ፡ ስትጠብቅ ፡ የነበረው ፡ ምክንያት ፡ ያገኘሁ ፡ መስሎአት ፡ ነበር ፡ ኢጣልያ ፡ በአድዋ ፡ ድል ፡ ከሆነች ፡ በኋላ ፡ እውነት ፡ ለምን ፡ ድል ፡ አደረገኝ ፡ በማለት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ በአፍ ፡ ወዳጅ ፡ መስላ ፡ ስታዘጋጀው ፡ የነበረውን ፡ ምንም ፡ የአውሮፓ ፡ ያለፈው ፡ ታላቁ ፡ ጦርነት ፤ ቢያቋርጣት ፡ በአለፉት ፡ ዘመናት ፡ ገልማለች ፡ ኢጣልያ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የአጥቂነት ፡ ጦርነት ፡ በአደረገች ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ተወዳዳሪ ፡ አለመሆናችንን ፡ ብናውቀው ፡ በግፍ ፡ አገራችንን ፡ ለመንጠቅ ፡ የመጣብንን ፡ ጠላት ፡ መከላከል ፡ የተገባን ፡ ሥራ ፡ ስለሆነ ፡ በነበረን ፡ አቅም ፡ ተከላክለን ፡ የዓለም ፡ ሕግ ፡ በከለከለውም ፡ መሣሪያ ፡ በጋዝ ፡ ጭስ ፡ ሕዝባችንን ፡ የምትጨርስብን ፡ ቢሆን ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ለማሰማትና ፡ ፍርድ ፡ ለመቀበል ፡ ሄድን ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ኢጣልያን ፡ ያነሳችው ፡ ጠብ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ የሚዘረጋ ፡ ስለሆነ ፡ ዓለምን ፡ አሁን ፡ ከደረሰባት ፡ ጥፋት ፡ ለማዳን ፡ ለመንግሥታት ፡ መሪነት ፡ የተቀበሉ ፡



ሁሉ ፡ የሚጣጣሩበት ፡ ዘመን ፡ ስለነበረ ፡ ይህ ፡ እሳት ፡ እንዳይቃጠል ፡ በዓለም ፡ ስምምነት ፡ እንዲገኝ ፡ ሲያከሙበት ፡ ቆዩ ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ የልብ ፡ ወዳጆችን ፡ የሆነችው ፡ ታላቂቱ ፡ ብሪታንያ ፡ በመልካም ፡ ወዳጅነት ፡ ተቀብላን ፡ ቆየች ፡ በዚያም ፡ አለፍርድና ፡ ያለርህራሄ ፡ በከንቱ ፡ ደማቸው ፡ በኢጣልያ ፡ እጅ ፡ የሚፈሰውን ፡ ሰዎችና ፡ በከንቱ ፡ የሚቃጠሉትን ፡ አድባራትና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በሰው ፡ አገር ፡ ተሰደው ፡ ባገራቸው ፡ በዱር ፡ በገደልና ፡ በጫካ ፡ መከራና ፡ ስቃይ ፡ ያዩ ፡ የነበሩትን ፡ በአሳብ ፡ ሳንለያቸው ፡ በሥራ ፡ ቆየን ።

በነዚህ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ኢጣልያ ፡ በጭካኔ ፡ የፈጀቻቸው ፡ ወጣቶችና ፡ ሴቶች ፡ ካህናትና ፡ መነኮሳት ፡ ስንት ፡ ናቸው? በ፲፱፻፳፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የየካቲት ፡ ሚካኤል ፡ ዕለት ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ብቻ ፡ ? በብዙ ፡ ሺህ ፡ የሚቆጠሩ ፡ ሰዎች ፡ በሶስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ማለቃቸውን ፡ ታውቃላችሁ ፡ በአካፋና ፡ በዶማ ፡ በምሳርና ፡ በመዶሻ ፡ የተፈለጡት ፡ በሳንጃ ፡ የተወጉት ፡ በዱላና ፡ በድንጋይ ፡ የተወገሩት ፡ በቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ እንዳሉ ፡ ከሕጻናት ፡ ልጆቻቸው ፡ ጋር ፡ በእሳት ፡ የተቃጠሉት ፡ ታሥረውም ፡ በረሃብና ፡ በውሃ ፡ ጥም ፡ ያለቁት ፡ ደማቸውና ፡ እጥንታቸው ፡ እቢቱታቸውን ፡ ሲያቀርብ ፡ ቆየ ፤ ይህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ የአረመኔና ፡ የጨካኝነት ፡ ሥራ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የባሰውን ፡ የቀሩት ፡ በሌሎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ሲሠራ ፡ እንደነበረ ፡ ማንም ፡ የሚያውቀው ፡ ነው ፤ ተይዞ ፡ ያልተደበደበ ፡ ያልተረገጠና ፡ ያልተዋረደ ፡ ያልታሠረ ፡ አይገኝም ።

አሁን ፡ በፊታችን ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ አዲሱ ፡ ታሪክ ፡ እንተላለፋለን ፤ የዛሬ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ልክ ፡ በዛሬይቱ ፡ ቀን ፡ የፋሽስት ፡ ወታደር ፡ ከዋናው ፡ ከተማችን ፡ ገባ ፤ ቀጥሎም ፡ ሙሶሊኒ ፡ በኛ ፡ አገር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሮማን ፡ አምፐር ፡ አቋሚአለሁ ፡ ብሎ ፡ ለዓለም ፡ አስታወቀ ፤ አቀናሁላችሁ ፡ ብሎ ፡ ያስታወቀውም ፡ አገር ፡ ለዘለዓለም ፡ በጁ ፡ የሚኖር ፡ መስሎት ፡ አምኖ ፡ ነበር ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጀግንነት ፡ በታሪክ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለሕዝባችን ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የዘመኑን ፡ መሣሪያ ፡ የምናገባበት ፡ ጠረፍ ፡ ባለመኖሩ ፡ ምክንያት ፡ ለማግኘት ፡ ሳይቻለን ፡ ቀረ ፤ ሙሶሊኒ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ፶፪ ፡ መንግሥታት ፡ ፈረዱበት ። እርሱ ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ የግፍ ፡ ሥራውን ፡ ተመካበት ። ፍርዳቸውን ፡ ከምንም ፡ አልቆጠረውም ፡ ያለፉት ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ ለናንተ ፡ ለሕዝቦቼ ፡ የጨለማ ፡ ጊዜያቶች ፡ ነበሩ ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ተስፋ ፡ ሳትቆርጡ ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ እየጀመራችሁ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኮረብቶች ፡ ላይ ፡ ተሰማራችሁ ፡ በነዚህ ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ እናንተ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ማናቸውንም ፡ መከራና ፡ ጭንቀት ፡ ችላችሁ ፡ ነጻነታችሁን ፡ ጠብቃችሁ ፡ ወደ ፡ ተሰማራችሁባቸው ፡ ተራሮች ፡ ለመምጣት ፡ ጠላታ



ይህ ፡ ሥዕል ፡ የሚያሳየው ፡ በአዲሱ ፡ ዘመን ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በ፳፫ኛው ፡ የድል ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ በተሻሻለው ፡ በአዲሱ ፡ የጦር ፡ ልብስ ፡ የተነሱት ፡ ሲሆን ፤ ከቀኝ ፡ ልዑል ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋወራሽ ፡ መርዕድ ፡ አዝማች ፡ አስፋወሰን ፡ በግራ ፡ የመከላከያ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሌ/ጄኔራል ፡ መርዕድ ፡ መንገሻ ፡ ናቸው ።

በዚህ ፡ ሥዕል ፡ ላይ ፡ የሚታዩት ፡ የሴት ፡ አርበኞች ፡ ስደተኞች ፤ እነርሱም ፡ ጠላት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በግፍ ፡ በወረረበት ፡ ጊዜ ፡ ከወንዶቹ ፡ ጋር ፡ ተሰማርተው ፡ ብዙ ፡ የጀግንነት ፡ ሞያና ፡ አገልግሎት ፡ የፈጸሙት ፤ በ፳፫ኛው ፡ ዓመት ፡ የድል ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ ከጀግኖቹ ፡ ጋር ፡ ተሰልፈው ፡ በዓሉን ፡ ሲአከብሩ ፡ ነው ። ➞

ጠላት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በግፍ ፡ ወሮ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ አምስቱንም ፡ ዘመን ፡ በአርበኝነት ፡ ሲጋደሉ ፡ የነበሩት ፡ ወንድ ፡ አርበኞች ፡ ፳፫ኛው ፡ ዓመት ፡ የድል ፡ በዓል ፡ በተከበረበት ፡ ቀን ፡ በድል ፡ አድራጊው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ በአምስት ፡ ዓመት ፡ የሠሩትን ፡ ሞያ ፡ በአገሩ ፡ ባህል ፡ ሲገልጹ ፡ ነው ። ➞







ችን ፡ ከቶ ፡ ሊደፍር ፡ አልቻለም ፤ ምንም ፡ እንኳን ፡ አገሩን ፡ ለማቅናት ፡ ባይቻል ፡ የያዘውን ፡ አስለጥናለሁ ፡ በማለት ፡ ብዙ ፡ ሺህ ፡ ሚሊዮን ፡ ሊሬ ፡ አፈሰሰ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ ማውጣቱ ፡ የተጠቃውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ሁኔታ ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ የሠራውን ፡ ግፍ ፡ ለማሻሻል ፡ አልነበረም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በቅድስት ፡ አገራችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፋሽስት ፡ ኰሎኒ ፡ ለማቆም ፡ እሱ ፡ እንዳሰበው ፡ ያለ ፡ የጭካኔ ፡ አገዛዝ ፡ ለመትከል ፡ ነበር ። የኢትዮጵያን ፡ ዘር ፡ ለመጨረስ ፡ ተጣጣረ ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ላንድ ፡ ነጻ ፡ መንግሥት ፡ ከባድ ፡ ቀንበር ፡ ሆኖ ፡ የሚቆጠር ፡ ቢሆን ፡ የማንዳ ፡ ወይም ፡ የፕሮቴክተራ ፡ አስተዳደር ፡ እንኳ ፡ አላሰበላትም ።

ነገር ፡ ግን ፡ በብዙ ፡ ሺህ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚቆጠር ፡ ገንዘብና ፡ የተዘጋጀው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ሁሉ ፡ ሙሶሊኒ ፡ ላሰበው ፡ መንገድ ፡ መዋሉ ፡ ቀርቶ ፡ በፍጹም ፡ ላላሰበው ፡ ጉዳይ ፡ ሆነ ፡ ኢጣልያ ፡ ድል ፡ ከሆነችው ፡ ከፈረንሳይ ፡ ላይ ፡ የተቻላትን ፡ ያህል ፡ ለመንጠቅ ፡ አስባ ፡ ጦርነት ፡ ለማድረግ ፡ መቁረጧን ፡ በገለጠች ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያጓዘችው ፡ ሰው ፡ የላከችው ፡ ገንዘብና ፡ መሣሪያ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ነበር ።

የሰበሰበችው ፡ ደንበኛ ፡ ጦር ፡ ቁጥር ፡ ከመቶ ፡ ሃምሳ ፡ ሺህ ፡ አያንስም ፡ የተከበብሁም ፡ እንደሆነ ፡ ብላ ፡ የብዙ ፡ ዓመት ፡ ስንቅ ፡ አከማችታ ፡ ነበር ፤ በዚሁ ፡ ባዘጋጀችው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ በመተማመን ፡ ማንም ፡ ሊያሸንፈኝ ፡ አይችልም ፡ ብላ ፡ ስለተመካች ፡ የፋሽስት ፡ መንግሥት ፡ የቶታሊታሪያን ፡ አገዛዝ ፡ ባገራችን ፡ ውስጥ ፡ ጀምራ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የፋሽስት ፡ መንግሥት ፡ ያላሰበው ፡ ነገር ፡ መጣ ፡ ለዛሬው ፡ ዘመን ፡ ጦርነት ፡ ዋና ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ የተዋጊነት ፡ መንፈስ ፡ በናንተ ፡ ተገለጠ ።

ጀግንነትና ፡ ርህራኄ ፡ ያለው ፡ የአንድ ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ ከመሆናችሁ ፡ ጋር ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ በመረዳዳታችሁና ፡ የጦር ፡ አቅድ ፡ በማወቃችሁ ፡ በመሣሪያና ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ከናንተ ፡ እጅ ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ጠላት ፡ ለማጥፋት ፡ በቃችሁ ። ለሰው ፡ ልጅ ፡ ነጻነት ፡ መብት ፡ ሲሉ ፡ በሌላ ፡ ክፍል ፡ ይዋጉ ፡ የነበሩት ፡ የእንግሊዝ ፡ ወታደሮች ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመርዳትና ፡ ነጻ ፡ ለማውጣት ፡ እስኪዘጋጁና ፡ እስኪታጠቁ ፡ ድረስ ፡ ጊዜ ፡ አስፈልጓቸው ፡ ነበር ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ግን ፡ በመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ መገናኛ ፡ እየቆረጣችሁ ፡ ጠላታችንን ፡ እያስጨነቃችሁ ፡ ከየምሽጉ ፡ እንዳይወጣ ፡ አደረጋችሁት ። ምንም ፡ እንኳ ፡ የተማመነበት ፡ ቁጥሩ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ቢሆን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እነሱንና ፡ አገዛዙን ፡ ከዳር ፡ እስከዳር ፡ እንደ ፡ ጠላው ፡ በቶሎ ፡ ተረድቶ ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ አገርና ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ መኖር ፡ የማይቻል ፡ መሆኑ ፡ ታወቀው ። እንደልማ



ዱም ፡ የመርዝ ፡ ጋዝ ፡ ቦንቡን ፡ እየጣለ ፡ የአረመኔነትና ፡ የጭካኔ ፡ ሥራውን ፡ እየሠራ ፡ ውስጡ ፡ በመነመነ ፡ በላይነት ፡ እኖራለሁ ፡ ብሎ ፡ ለማሰብ ፡ የማይቻል ፡ ሆነበት ። በያለበት ፡ ከቦ ፡ የያዘው ፡ ወታደር ፡ ከርሱ ፡ የበለጠ ፡ ኃይለኛ ፡ ባላጋራ ፡ መሆኑን ፡ ተረዳው ፡ ይህንንም ፡ ባላጋራውን ፡ ለመግጠም ፡ ያችኑ ፡ ተርፋ ፡ የነበረችውን ፡ ድፍረትና ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ አጠፋ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የምጠጋበት ፡ ደህና ፡ ቦታ ፡ አገኝ ፡ እንደሆነ ፡ በማለት ፡ ሞከረ ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድም ፡ የሚጠጋበት ፡ ቦታ ፡ አላገኘም ፡ ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ረዳታችን ፡ ታላቁ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ጠላታችንን ፡ በሚገባ ፡ ለመውጋት ፡ ተደራጀ ፡ እኔም ፡ ይህን ፡ እንዳወቅሁ ፡ ወታደሮቼን ፡ ይዤ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ከሚዋሰነን ፡ እኅት ፡ ከሆነው ፡ አገር ፡ ከሱዳን ፡ ተነስቼ ፡ ወደ ፡ መሐል ፡ ጎጃም ፡ ገባሁ ፤ ጠላታችን ፡ በጎጃም ፡ መሬት ፡ ብርቱ ፡ ምሽጎችና ፡ ኃይለኞች ፡ ወታደሮች ፡ ኤሮፕላኖችና ፡ መድፎችም ፡ ነበሩት ፡ የእኛንና ፡ የጠላታችንን ፡ ወታደሮች ፡ ቁጥር ፡ ስንገምተው ፡ የብልጫው ፡ ከፍተኛነት ፡ የኛ ፡ አንድ ፡ የርሱ ፡ ሃያ ፡ ይሆን ፡ ነበር ፤ ከዚህ ፡ በቀር ፡ ደግሞ ፡ እንደፈቃዳችን ፡ የምናዝዝበት ፡ መድፍና ፡ ኤሮፕላን ፡ አልነበረንም ፡ የኔ ፡ በአርበኞቼ ፡ መካከል ፡ መገኘት ፡ ብቻ ፡ ብዙ ፡ ሺህ ፡ ሰው ፡ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሳበ ። የጠላታችንም ፡ ፍርሃቱና ፡ መጨነቁ ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ እየበዛ ፡ ሄደ ፤ ወታደሮቼ ፡ እየገሰገሱ ፡ የጠላታችንን ፡ መገናኛ ፡ መንገድ ፡ እየቆረጡ ፡ ወታደሮቼንም ፡ እያባረሩ ፡ ከዓባይ ፡ ወዲያ ፡ ማዶ ፡ አሻግረው ፡ ወደ ፡ ሸዋና ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ ሲከታተሉት ፡ ሳሉ ፡ የእንግሊዝ ፡ እምፔሪያል ፡ ወታደሮች ፡ ማንም ፡ ሊተካከለው ፡ በማይቻል ፡ ሁኔታ ፡ እየገሰገሱ ፡ ዋና ፡ ከተማችንን ፡ መያዛቸውንና ፡ በስተሰሜን ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ደሴ ፡ በስተደቡብ ፡ ወደ ፡ ጅማ ፡ የመግፋታቸውን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ወሬ ፡ ሰማሁ ፤

እንደዚሁም ፡ ከሱዳን ፡ የዘመቱት ፡ ወታደሮች ፡ እጅግ ፡ በሚያስደንቅ ፡ ኃይል ፡ የከረንን ፡ ምሽግ ፡ አፍርሰው ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ በፍጹም ፡ ድል ፡ አደረጉት ።

እኔም ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ከተማዬ ፡ የምገባበት ፡ ጊዜ ፡ ስለደረሰ ፡ ጠላታችንን ፡ ለማባረር ፡ በየቦታው ፡ ተበታትነው ፡ የነበሩትን፡ ወታደሮቼን፡ እየመራሁ ፡ በመንገዴ ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ጠላት ፡ ድል ፡ እየሆነ ፡ እስከ ዚህ ፡ በመድረሴና ፡ የጋራ ፡ ጠላታችንን ፡ ኃይል ፡ በመስበሬ ፡ ደስታዬ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ይመነጫል ፤ የፋሽስት ፡ መንግሥት ፡ ጥሎት ፡ በሸሸው ፡ ቤተ ፡ መንግሥቴ ፡ ውስጥ ፡ ዛሬ ፡ በመካከላችሁ ፡ በመገኘቴ ፡ ሁሉን ፡ ቻይ ፡ ለሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ የማቀርብለት ፡ የልብ ፡ ምስጋና ፡ ሊወሰን ፡ አይቻልም ።

## ያገሬ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ።

ዛሬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እጆችዋን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘርግታ ፡ እልል ፡ እያለች ፡ ምስጋናዋን ፡ የምታቀርብበት ፡ ደስታዋን ፡ ለልጆቿ ፡ የምትገልጽበት ፡ ቀን ፡ ነው ።


የኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ ከባዕድ ፡ የመከራ ፡ ቀምበርና ፡ ከዘለዓለም ፡ ባርነት ፡ ነጻ ፡ የወጡበት ፡ ቀንና ፡ እኛም ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ተሊይተነው ፡ ከነበርነው ፡ ከምንወደውና ፡ ከምንናፍቀው ፡ ሕዝባችን ፡ ጋራ ፡ ለመቀላቀል ፡ የበቃንበት ፡ ቀን ፡ ስለሆነ ፡ ይፀ ፡ ቀን ፡ የተከበረና ፡ የተቀደሰ ፡ በያመቱም ፡ ታላቁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ በዓል ፡ የሚውልበት ፡ ነው ። በዚህም ፡ ቀን ፡ ለሚወዷት ፡ ላገራቸው ፡ ነጻነት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ ለሰንደቅ ፡ ዓላማቸው ፡ ክብር ፡ ከአባቶቻቸው ፡ የተላለፈውን ፡ ጥብቅ ፡ አደራ ፡ እናስወስድም ፡ በማለት ፡ መሥዋዕት ፡ ሆነው ፡ ደማቸውን ፡ ያፈሰሱትን ፡ አጥንታቸውን ፡ የከሰከሱትን ፡ ጀግኖቻችንን ፡ እናስታውሳለን ፤ ለነዚህም ፡ ለጀግኖቻችን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ምስክር ፡ ይሆናል ።

ባለፉት ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ ተነግረውና ፡ ተቆጥረው ፡ የማያልቁ ፡ ያገኘናቸው ፡ መከራና ፡ ስቃይ ፡ ትምህርት ፡ ሆነውን ፡ ሠራተኞነት ፡ አንድነት ፡ ኅብረትና ፡ ፍቅር ፡ በልባችሁ ፡ ተፈጽመው ፡ ለምናስበው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ጉዳይ ፡ ረዳቶች ፡ ለመሆን ፡ ዋና ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጣችሁ ፡ ነው ፡ በአዲሷ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ የማትነጣጠሉ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ትክክልነትና ፡ ነጻነት ፡ ያላችሁ ፡ ሕዝቦች ፡ እንድትሆኑ ፡ እንፈልጋለን ። አገር ፡ የሚለማበትን ፡ ሕዝብ ፡ የሚበለጽግበትን ፡ እርሻ ፡ ንግድ ፡ ትምህርትና ፡ ጥበብ ፡ የሚስፋፋበትን ፡ የሕዝባችን ፡ ሕይወቱና ፡ ሀብቱ ፡ የሚጠበቅበትን ፡ ያገር ፡ አስተዳደርም ፡ ባዲስ ፡ ሥልጣኔ ፡ ተለውጦ ፡ ፍጹም ፡ የሚሆንበትን ፡ ይህን ፡ ለመሰለው ፡ ለምንደክምበት ፡ ሥራ ፡ አብሮ ፡ ደካሚ ፡ መሆን ፡ አለባችሁ ።

ይህንን ፡ እግዚአብሔር ፡ በቸርነቱ ፡ የሠራልንን ፡ ሥራ ፡ መጀመሪያ ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ረዳታችን ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ያደረገልንን ፡ ውለታ ፡ ለመመለስ ፡ ኢምፔሪያል ፡ ትሩፕ ፡ የተባሉት ፡ ወታደሮች ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ የጦር ፡ ግምባር ፡ ተዛውረው ፡ የጋራ ፡ ጠላታችንን ፡ ለማጥቃት ፡ እንዲችሉ ፡ ማድረግና ፡ በጦር ፡ ሠራዊትም ፡ እንድናግዝ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በመርዳት ፤ ሁለተኛም ፡ በአገራችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሃይማኖትን ፡ የሚያስከብርና ፡ የሚጠብቅ ፡ መንግሥት ፡ በማቋቋም ፡ የሕዝብንና ፡ የሕሊናን ፡ ነጻነት ፡ በመፍቀድ ፡ ለሕዝብና ፡ ላገር ፡ የሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ብርቱ ፡ ምኞታችንና ፡ አሳባችን ፡ ነው ።



አሁን ፡ በመጨረሻ ፡ ለናንተ ፡ ለሕዝቤ ፡ የማስታውቃችሁ ፡ ዛሬ ፡ የሁላችን ፡ የደስታ ፡ ቀን ፡ መሆኑን ፡ ነው ፤ ዛሬ ፡ ጠላታችንን ፡ ድል ፡ የመታንበት ፡ ቀን ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ በሙሉ ፡ ልባችን ፡ ደስ ፡ ይበለን ፤ ስንል ፡ ደስታችን ፡ በክርስቶስ ፡ መንፈስ ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ አይሁን ፡ ለክፉ ፡ ክፉ ፡ አትመልሱ ፡ ጠላት ፡ እንደወትሮው ፡ ልማድ ፡ እስከዚህ ፡ መጨረሻ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ እንደሠራው ፡ የጭካኔና ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ አትሥሩ ። ጠላታችን ፡ መውቀሻ ፡ በሚሆነው ፡ ነገር ፡ የኢትዮጵያን ፡ መልካም ፡ ስም ፡ እንዳታሳድፉ ፡ ተጠንቀቁ ። ጠላቶቻችን ፡ በእጃቸው ፡ ያለውን ፡ መሣሪያ ፡ እንዲያስረክቡና ፡ በመጡበት ፡ መንገድ ፡ ተመልሰው ፡ እንዲሄዱ ፡ እናደርጋለን ። ደራጎንን ፡ የገደለ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የኛም ፡ የባለቃል ፡ ኪዳን ፡ ረዳቶቻችንም ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ባልደረባ ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ አዲስ ፡ የተነሳውን ፡ የሰውን ፡ ልጅች ፡ የሚያስጨንቀውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የማያምን ፡ ጨካኝ ፡ ዘንዶ ፡ ለመቃወም ፡ እንድንችል ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ በሚኖር ፡ ወዳጅነትና ፡ ዝምድና ፡ ከባለ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ረዳቶቻችን ፡ ጋር ፡ እንተባበር ፡ እነርሱንም ፡ እንደዘመድና ፡ ወዳጅ ፡ ተመልክተን ፡ ደግነትና ፡ ቸርነት ፡ እንድታሳዩዋቸው ፡ አደራ ፡ እንላችኋለን ።



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ጉብኝት ፡ ሲያደርጉ ። (አስጐብኚዎች ፡ ሻለቃ ፡ ዓቢይ ፡ አበበና ፡ ሻለቃ ፡ ሙሉጌታ ፡ ቡሊ) ።